አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኽኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና

በ

መኮንን አስማማው

የአርት ማስተር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ

መኮንን አስማማው

አዲስ አበባ
2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ትንተና

በ

መኮንን አስማማው

የአርት ማስተር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

2007 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ረ/ፕሮፌሰር ሰላማዊት መካ | ______________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| አቶ ደረጀ ገብሬ | ______________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| አቶ ተስፋዬ ገብረ ማሪያም | ______________ |

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዋና ትኩረቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው የትኩረት ነጥብ በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች እንዴትና መቼ እንደሚከወኑ ማሳየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይዘታቸውን መተንተን ነው። ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ቦታና ጊዜ በመገኘት ለዚህ ጥናት የሚጠቅሙ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ነው። በምልከታና በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና የተሟላ መረጃ ለማግኘት የቡድን ውይይት ተደርጓል። ጥናቱ የሰባት በዓላትን የቃል ግጥሞች ክዋኔ ተመልክቷል።

የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች መከወኛ አጋጣሚ ክብረ በዓላት ናቸው። በጥናቱ ህዳር 21 ቀን የማሪያም ታቦትን ንግሥ አስመልክቶ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች እንደሚጀምሩና እስከ ፋሲካ በዓል ድረስ በሚከበሩ ዓውደ ዓመቶችና የንግስ በዓላት እንደሚቀጥሉ ተረጋግጧል።

ቃል ግጥሞቹ በፆታ ልዩነት ላይ ተመሥርተው የሚገጠሙ ናቸው። የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ሴቶችን ብቻ ለማወደስና ለመሳደብ የሚገጠሙ ሲሆን የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ደግሞ ሴቶችን በማወደስ ብቻ ሲያልፏቸው በአብዛኛው ወንዶችን የሚሳደቡ በጥቂቱ የሚያሞግሱ ናቸው። በሁለቱ ቃል ግጥሞች መካከል የአከዋወን ሂደት ልዩነትም እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል። የአበሹቴና የኧኸይቦሌ የቃል ግጥሞች አከዋወን የተለያየ ቢሆንም የሁለቱም ቃል ግጥሞች አጠቃላይ ይዘት የደላንታ ወረዳን ህብረተሰብ ባህል መጠበቅና ማንነቱን ማንጸባረቅ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

ጥናቱ የቃል ግጥሞቹ የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች ድግግሞሽ እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል። ለዘመናት በዓመት አንድ ጊዜ በፋሲካ በዓል ብቻ ይከወኑ የነበሩት እነዚህ ቃል ግጥሞች አንድ ትውልድ ሳያልፍ በአንድ ቀበሌ ውስጥ በዓመት ከስድስት ጊዜ በላይ በመከወን ላይ መሆናቸውን ጥናቱ ያስረዳል። በገና፣ በጥምቀት እና በፋሲካ በዓላት ጨዋታዎቹ በሚከወኑባቸው ሁሉም ቀበሌዎች ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑ ሲሆን በንግስ በዓላት ግን በተወሰኑ የታቦት ንግስ ባለባቸው ቀበሌዎች ብቻ የሚከወኑ መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል። ከክዋኔው ጋር ተያይዞ ድግግሞሹ (የሚከወኑበት አጋጣሚ) የጨመረ ቢሆንም በከተማ እና በከተማ ዙሪያ በሚገኙ ቅርብ ቀበሌዎች ጨዋታዎቹ እየቀሩ መሆኑን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል።

# ምስጋና

ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ምሁራዊ ምክራቸውን በመለገስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጥናታዊ ጽሑፉን ላረሙልኝ መምህሬና አማካሪዬ ሰላማዊት መካ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

በቀና መንፈስ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ ምስጋና ይድረሳቸው። ሳይሰለቹ ጠቃሚ መረጃ በማቀበልና መረጃ ሰጪዎችን በማገናኘት የመስክ ሥራዬ የተሳካ እንዲሆን ጥረት ላደረጉልኝ ደስታው አስማማው እና ሀብታሙ ፍስሃ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ለደላንታ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልኝ ከልብ የሆነ ማበረታታትና ድጋፍ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። መረጃ ለመሰብሰብ በቆየሁባቸው ቀናት የዘወትር ድጋፋቸው ያልተለየኝ ወይዘሮ ብርዘገን ዘገየ እንዲሁም አጠቃላይ ቤተሰቡን አመሰግናለሁ፤ እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጣቸው። ሁሉንም የክፍል ጓደኞቼን አመሰግናለሁ። በተለይ ለሀብታም ግዛት ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።

ዘግይቶም ቢሆን የድኅረ ምረቃ ትምህርት እንድማር ሙሉ ወጪውን የሸፈነልኝና ለዚህ ጥናት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ መሥሪያ ቤቴ ምስጋና ይገባዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም በተቋም ደረጃና በተጨማሪም ለመምህራኑ ተመሳሳይ ምስጋና ይድረሳቸው።

ሁሉንም የሥራ ባልደረቦቼን አመሰግናለሁ። በተለይ አቶ ዳንኤል አበበ፣ አቶ ዘለዓለም አላጋው፣ አቶ ጥላሁን በየነ እና ወይዘሮ ወሰን በየነ ላደረጉልኝ ማበረታታትና ድጋፍ እግዚአብሔር ይስጥልኝ። በመጨረሻም ዘወትር ለሚያበረታቱኝ ቤተሰቦቼ በተለይም ወይዘሮ አዳነች ለገሰ እና ሲስተር ብዙዬ አስማማው ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

## ሙዳዬ ቃላት

1 መሰቅሰቂት= እንጀራ ወይም ዳቦ ከምጣድ አልወጣ ሲል ለማስለቀቅ የሚያገለግል ስንጥር እንጨት

2 መታረሪያ= ለጥጥ መንደፊያ የሚያገለግል ቀጭን እንጨት

3 መንጋላ= መንቃራ፣ አረማመዱ ወይም አካሄዱ እርጋታ የተለየው

4 ምንሽርሽር= ብትንትን፣ የጨዋታ መበታተን፣ የጨዋታ መፍረስ

5 ሰላሱት = የአተር ወይም የሽንብራ ክክ

6 ሰጋጋ = ቀጭን ረጅም ሰው

7 ማዱላ = ልጃገረድ፣ ያላገባች ወጣት (ጸጉሯን ደፍና ያልተሠራች)

8 ራሂሎ= ዛር፣ የዛር ዓይነት

9 ሽለሽል= በጨሌ ወቅት ከብቶች ጥለውት የደረቀ እበት፣ ስስ፣ ቀላል (ልጥፍ ያለ)

10 ቁንጮጮ= ቁንጮ፣ ዙሪያውን ተላጭቶ ግንባር አጠገብ የሚቀር

11 ቃርሚያ = ሰብል ከታጨደ በኋላ ማሳ ላይ ተዝረክርኮ የሚቀረው እህል

12 ቡንኝ = በአጭር ጊዜ የምትደርስ የጤፍ ዝርያ

13 ናስ = የድንጋይ ካብ፣ በጭቃ እየተለሰነ የሚገነባ

14 አምባር = እጅ ላይ የሚደረግ ጌጥ፣ (ሸዋሊያ)

15 አሞናሞኗት = አሽሞነሞኗት፣ ተንከባከቧት

16 አደስ = የባለጥሩ መዓዛ ተክል መጠሪያ፣ ተወቅጦ ከቅቤ ጋር የሚቀቡት

17 እንመዳመድ= እንፋለም፣ እንፎካከር፣ እንወዳደር

18 እከሊት= የስም ምትክ (እንትና እንደ ማለት) ስሟን ከነአባት ለማመልከት እከሊት አበሉ ይባላል። ለወንድ እከሌ ይባላል።

19 ወተርታራ = መራመድ እንደሚለማመድ ህጻን የሚንገዳገድ፣

20 ዛርጤ= ፈሪ


21 ድሪ = አንገት ላይ የሚደረግ የሴቶች ጌጥ

22 ጅሪ = የዝንጀሮ መንጋ

23 ጉስጉሻ = ከጭቃ የሚሠራ ከጎተራ የሚያንስ የእህል ማስቀመጫ፣ ድብኝት

24 ጎባን = ጣውንት

**<u>ካርታ</u>፡-ጥናቱ የተካሄደበት የደላንታ ወረዳ የሚገኝበት የአማራ ክልል**







የደላንታ ወረዳ ካርታ (ከደላንታ ወረዳ የንግድና ኢንቨስትመንት መመሪያ የተወሰደ)

# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| አጠቃሎ | i. |
| ምስጋና | ii. |
| ሙዳዩ ቃላት | iii. |
| ካርታ | iv. |
| 1. መግቢያ | 1 |
| 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት | 1 |
| 1.2. የጥናቱ ዳራ | 2 |
| 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | 3 |
| 1.4. የጥናቱ ዓላማ | 4 |
| 1.4.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ | 4 |
| 1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች | 4 |
| 1.5. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች | 5 |
| 1.6. ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ | 5 |
| 1.7. የጥናቱ ወሰን | 5 |
| 1.8. የጥናቱ ዘዴዎች | 6 |
| 1.8.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች | 6 |
| 1.8.1.1. ምልከታ | 7 |
| 1.8.1.2. ቃለ መጠየቅ | 8 |
| 1.8.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ | 9 |
| 1.8.3. የናሙና አመራረጥ | 10 |
| 1.8.4. የጥናቱ አከዋወን ሂደት | 10 |
| 1.9. የመስክ ቆይታ ዘገባ | 11 |
| 1.10. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች | 16 |
| 2. ክለሳ ድርሳናት | 18 |
| 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት | 18 |
| 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት | 21 |
| 2.2.1. የክብረ በዓላት ዘፈኖች | 21 |
| 2.2.2. ክዋኔ | 22 |

2.2.3. አውድ 26

2.2.4. የቃል ግጥም ድረሳ 27

2.2.5. ተስተላልፎ 28

2.2.6. የቃል ግጥም ፋይዳ 29

**3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ** 31

3.1. መልክአምድራዊ ገጽታ 31

3.2. ኢኮኖሚያዊ ገጽታ 31

3.3. ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታዎች 32

**4. የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ፣ አከዋወን፣ ተስተላልፎና ፋይዳ** 35

4.1. የቃል ግጥሞች አደራረስ 36

4.1.1. የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ 36

4.1.2. የአበሹቴ ቃል ግጥሞች አደራረስ 37

4.2. የኽኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች አከዋወን 41

4.2.1. የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አከዋወን 43

4.2.2. የአበሹቴ ቃል ግጥሞች አከዋወን 44

4.3. በታቦት ንግሥና በዐበይት የክርስቲያን በዓላት የጨዋታዎቹ አውድ 48

4.3.1. በታቦት ንግሥ የኽኸይቦሌና የአበሹቴ ጨዋታዎች አውድ 48

4.3.1.1. በታቦት ንግሥ የኽኸይቦሌ ጨዋታ አውድ 49

4.3.1.2. በታቦት ንግሥ የአበሹቴ ጨዋታ አውድ 51

4.3.2.በዐበይት ክርስቲያን በዓላት የኽኸይቦሌና አበሹቴ ጨዋታዎች አውድ 52

4.3.2.1. በፋሲካ በዓል የኽኸይቦሌ ጨዋታ አውድ 52

4.3.2.2. በፋሲካ በዓል የአበሹቴ ጨዋታ አውድ 54

4.4. የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ተስተላልፎ 55

4.5. የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ፋይዳ 56

**5. የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ትንተና** 58

5.1. የአበሹቴ ግጥሞች ትንተና 59

5.1.1. የውዳሴ ቃል ግጥሞች በአበሹቴ ጨዋታ 60

5.1.1.1. ባለሞያነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 60

5.1.1.2. ለጋስነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 63

5.1.1.3. ውበትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 65
5.1.1.4. ወዳጅነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 67
5.1.2.በአበሹቴ ጨዋታ የስድብ ቃል ግጥሞች 69
5.1.2.1. ሞያ የሌላትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 70
5.1.2.2. አመንዝራነትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 72
5.1.2.3. ሌብነትን የሚያወግዙ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 74
5.1.2.4. መልከ ጥፉን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 75
5.1.2.5. የጽዳት ጉድለትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 77
5.1.2.6. ሆዳምነትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች 79
5.2. የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ትንተና 81
5.2.1. የውዳሴ ቃል ግጥሞች በኧኸይቦሌ ጨዋታ 81
5.2.1.1. የጓደኛ ፍቅር መግለጫ የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች 81
5.2.1.2. ፍቅርን /ፍቅረኛን የሚያወድሱ የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች 83
5.2.1.3. የተቃራኒ ፆታ ፍቅር መግለጫ የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች 85
5.2.1.4. በወጣትነት መዝናናትን የሚያወድሱ 87
5.2.1.5. ዋዛ ፈዛዛ መቅረቱንና ቁም ነገረኛነትን የሚያወድሱ 88
5.2.1.6. መለያያትን በመፍራት አብሮነትን የሚያወድሱ 89
5.2.2. በኧኸይቦሌ ጨዋታ የስድብ ቃል ግጥሞች 91
5.2.2.1. የወንዶችን ፍርሃት የሚያጋልጡ የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች 91
5.2.2.2. ሰነፍና ሥራ ፈትን የሚሰድቡ ቃል ግጥሞች 93
6. ማጠቃለያ 95
ዋቢ ጽሑፎች 97
የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ (ፕሮፋይል)
አባሪዎች
አባሪ 1 የቃል ግጥሞች ስብስብ
አባሪ 2 ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች
አባሪ 3 ፎቶዎች

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

የደላንታ ህዝብ ባህሉን፣ ታሪኩን፣ እምነቱን፣ ወጉንና ልማዱን እንዲሁም ስሜቱን፣ ፍላጎቱንና አመለካከቱን የሚያንጸባርቅባቸው የተለያዩ የስነቃል ሀብቶች አሉት። ከነዚህ የስነቃል ዓይነቶች መካከል ከፊሎቹ እንቆቅልሾች፣ አፈታሪኮች፣ ተረቶች፣ የስራ ላይ ግጥሞች፣ የባህል ዘፈኖች የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ ጥናት በደላንታ ወረዳ የሚገኙ ሴቶች በክብረ በበዓላት ቀን ከሚያዜሟቸውና ከሚከውኗቸው ዓለማዊ ይዘት ካላቸው የባህል ዘፈኖች መካከል በአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ላይ የሚያተኩር ነው። ጥናቱ የአካባቢው ሴቶች በቃል ግጥሞቻቸው ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ፣ ግጥሞቹን እንዴት እንደሚደርሱና ተስተላልፎው ምን እንደሚመስል ይዳስሳል። በመሆኑም በዚህ ጥናት የደላንታ ህዝብ ቃላዊ ሀብቶች በሆኑት የአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አከዋወን፣ አደራረስ፣ ተስተላልፎና እና የይዘት ትንተና ላይ ትኩረት ተደርጓል።

### 1.1. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች፣ ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴዎችና የመስክ ቆይታ ዘገባ በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት የተዳሰሰበት ክፍል ነው። በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ ርዕሰ ጉዳዩን የሚመለከቱ ጥናቶች ባያጋጥሙም በሌላ አካባቢ የተደረጉ ለርዕሰ ጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ጥናቶች ተዳሰዋል። በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ስር ለፎክሎር ጥናት የሚያገለግሉ እንደ ድረሳ፣ ተስተላልፎ፣ ክዋኔ፣ አውድ፣ ፋይዳ እና የክብረ በዓላት ዘፈኖች ምንነት ተቃኝተዋል።

በሦስተኛው ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ መልክአ ምድራዊ ገጽታ፣ ኢኮኖሚያዊ መሠረቶችና ባህላዊ ሁኔታዎች በአጭሩ ተዳሰዋል።

በአራተኛው ምዕራፍ የደላንታ ወረዳ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ፣ አከዋወንና ተስተላልፎ ምን እንደሚመስሉ በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች አንጻር ተቃኝተዋል። በአምስተኛው ምዕራፍ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች የስድብ እና የውዳሴ ተብለው በሁለት ዐበይት ክፍሎች እና በበርካታ ንዑሳን ዘርፎች ተመድበው ተተንትነዋል።

በመጨረሻም የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር፣ የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ (ፕሮፋይል)፣ ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን በተጨማሪም በመስክ ቆይታ በክዋኔ ወቅት የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞችና ፎቶ ግራፎች በአባሪነት ተካተዋል።

## 1.2. የጥናቱ ዳራ

አንድ ተመራማሪ አንድን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት ሲነሳ ስለሚያጠናው ጉዳይ ምንነት ማወቅ ይገባዋል። እኔም በደላንታ ወረዳ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን ለማጥናት ስነሳ ስለ ቃል ግጥም ምንነት ለመረዳትና ምሁራን የሰጡትን ድንጋጌ ለማወቅ ጥረት አድርጌያለሁ። በዚህም ሙከራዬ ከምሁራኑ መረዳት የቻልኩት የቃል ግጥም ከፎክሎር የጥናት መስኮች መካከል አንዱ በሆነው በስነቃል ስር የሚካተት መሆኑን ነው። "የቃል ግጥም ምንነትን አስመልክቶ ድንጋጌ ለመስጠት በርካታ ምሁራን ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች ነው።" (ፈቃደ አዘዘ፣ 1991፣ 84) በተለይ የቃል ግጥም ቃላዊነቱን መሠረት በማድረግና እንዲሁም አደራረሱን፣ አከዋወኑንና ተስተላልፎውን አስመልክቶ ብያኔ መስጠት ከቶውንም የሚቻል አለመሆኑን Finnegan በአንድ መጣጥፍ ላይ Lord የተባሉ ፀሐፊ ለቃል ግጥም የሰጡትን ብያኔ ለአብነት ጠቅሰው እንደሚከተለው አብራርተውታል።

> The term oral poetry sounds fairly simple and clear cut. This is also the impression one gets from some statements about it. Oral poetry is described in one authoritative encyclopedia article as 'poetry composed in oral performance by people who cannot read or write. It is synonymous with traditional and folk poetry'… (1977, 7)

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ለቃል ግጥም ብያኔ ለመስጠት ቃሉ በራሱ ቀላልና ግልጽ መስሎ ይታያል። ከቃሉ ቀጥተኛነት ተነስተን ብያኔ ለመስጠት የሚያስችል ስሜት

ያሳድራል። በመሆኑም Finnegan በጠቀሱት ፀሐፊ እንደተገለጸው የቃል ግጥም ማንበብና መጻፍ በማይችሉ ሰዎች በቃል ተደርሶ የሚከወን ነው የሚል አሳሳችና ደፋር ብያኔ እስከመሰጠት ተደርሷል።

ምሁራን ለቃል ግጥም አንድ ወጥ ብያኔ ባይሰጡም ተግባሩን፣ ዘመን ተሻጋሪነቱንና ቃላዊነቱን መሠረት አድርገው የተለያዩ ገለጻዎችን ሰጥተዋል። ፈቃደ አዘዘ የቃል ግጥምን በተመለከተ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸው "ቃል ግጥም ማለት፣ አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርጾች ውስጥ የሚገኝ ሕዝባዊ ግጥም ነው።" (1991፣ 81) የሚል ተግባራዊ ድንጋጌ እድንጠቀም በመምከር ወደፊት ቀስ በቀስ በምርምር ላይ በመደገፍ ማሻሻል እንደሚቻል ይመክራሉ።

ስለሆነም ይህ ጥናት ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ድንጋጌ እንደመነሻ በመያዝ የአካባቢውንም የሥነቃል ዕውቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት በደላንታ ወረዳ የሚከወኑ የአበሹቴና የኸኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ላይ ያተኩራል። ማንኛውም ማህበረሰብ* ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚለየው እንዲሁም ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚጋራው ወግና ልማድ ይኖረዋል። የደላንታ ወረዳ ማህበረሰብም ከሌሎች ማህበረሰቦች የሚጋራቸውና የራሱ ብቻ የሆኑ ሀዘኑንና ደስታውን የሚገልጽባቸው፣ ክብረበዓላትን የሚያደምቅባቸው ቃላዊ ግጥሞች አሉት። ቃላዊ ግጥሞቹ የአካባቢውን ህብረተሰብ ሀዘን፣ ደስታ፣ ቁጭትና ምሬት እንዲሁም የህብረተሰቡን ማንነት የሚያንጸባርቁ ጥልቅ ስሜቶችን የተሸከሙ ናቸው።

ይህ የቃል ግጥም ጥናት ከዋና ዋና አውራ መንገዶች ርቀው በመገኘታቸው ምክንያት "ኪስ ወረዳዎች" ተብለው ከሚታወቁት የአማራ ክልል ወረዳዎች መካከል አንዱ በሆነው በደላንታ ወረዳ ላይ የተደረገ ነው። ወረዳው ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ ወይም ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር ከሚሄዱት አውራ መንገዶች ራቅ ብሎ የሚገኝ ስለሆነ የፎክሎር ጥናት በወጉ ካልዳሰሳቸው አካባቢዎች አንዱ ነው።

---

* <u>ማህበረሰብ</u> በዚህ ጥናት ማህበረሰብ የሚለው ቃል በአንድ መልክአ ምድራዊ አካባቢ የሚኖሩ አንድ ወይም በርካታ ጉዳዮች የሚያገናኟቸው የሰዎች ስብስብ (ጥብቅ ትስስር ያለው ሰፊ የሰዎች ቡድን) የሚል ትርጉም አለው።

በአካባቢው ከዚህ በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም። አንድ ለዲግሪ ማሟያ የተሠራ ጽሑፍ ቢያጋጥመኝም ጥናቱ በወረዳው ዋና ከተማ በሆነችው ወገልጤና ከተማ በሚገኙ አዝማሪዎች በሚዜሙ የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና ላይ የሚያተኩር ነው። ክዋኔና አውድን አልተመለከተም።

በመሆኑም የአካባቢው ፎክሎር አለመዳሰሱና የእኔ ፍላጎት ተጨምሮበት የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በወረዳው ሴቶች የሚገጠሙ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ገለጻና ይዘት ትንተና ላይ ነው።

## 1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የሥነቃል ጥናት አንድ ማህበረሰብ ምን እንዳለው፣ ምን እንደሚፈልግ ለመረዳት ይጠቅማል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ "ቃል ግጥም"፣ "ፎክሎር" እና "የፎክሎር የመስክ ጥናት ዘዴዎች" የመሳሰሉትን ኮርሶች በመማሬና በተለያዩ ተመራማሪዎች የተሰበሰቡ የቃል ግጥሞችን ለማንበብ እድሉን በስፋት በማግኘቴ ቃላዊ ግጥሞችን ይበልጥ ወደ ምንጫቸው ተጠግቼ ለመመርመር ፍላጎቱ አደረብኝ። ከዚህ በፊት በደላንታ ወረዳ አካባቢ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን በተመለከተ የተደረገ ጥናት ባለማጋጠሙ ይበልጥ ቃል ግጥሞቹን ለመመርመር አነሳሽ ምክንያት ሆኗል።

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

ይህ በደላንታ ወረዳ የአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ላይ የሚያተኩረው ጥናት ዋና ዓላማ ግጥሞቹን ከአውዳቸው በመሰብሰብ ክዋኔያቸውና ይዘታቸው ምን እንደሚመስል በመተንተን ማሳየት ነው።

### 1.4.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- በአብሹቴና ኧኸይቦሌ የቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮች እንደሚያነሱ በመለየት መተንተን፣
- ቃል ግጥሞቹን መቼ፣ የትና እንዴት እንደሚያዜሟቸውና እንደሚከውኗቸው ማሳየት/መግለጽ/፣

- የአብሹቴና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞችን ክዋኔ በመግለጽና ይዘታቸውን በመተንተን ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ ፋይዳቸውን መጠቆም ናቸው።

## 1.5 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

- በአበሹቴና በኧኽይቦሌ የቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮች ይነሳሉ?
- ቃል ግጥሞቹ መቼ፣ የትና እንዴት ይዜማሉ ወይም ይከወናሉ?
- የአብሹቴና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ማህበራዊም ሆነ ባህላዊ ፋይዳቸው ምንድን ነው?

## 1.6 ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

ይህ በአበሹቴና በኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል።

- ጥናቱ በመስኩ ቀጣይና ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ ሊሆናቸው ይችላል። በተለይም የቃል ግጥሞች በባህሪያቸው በዘመንና በቦታ ምክንያት የመለዋወጥ ባህርይ ስላላቸው ወደፊት ባህልን ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች የአሁኑን ዘመን የአበሹቴና የኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ከራሳቸው ዘመን ቃል ግጥሞች ጋር አነፃፅረው ለማጥናት ይጠቅማቸዋል።
- ተጠኚዎቹ ስለ አካባቢያቸውና ስለ ራሳቸው ያላቸውን አመለካከትና የህይወት ፍልስፍና ለማወቅ ለሚፈልጉ ተማራማሪዎችና የሴቶችን ጉዳይ ለሚከተታተሉ የተለያዩ አካላት የተወሰነ ፍንጭ ይሠጣል።
- በጊዜ ሂደት ባህሉ የመጥፋት ወይም በተወሰነ ደረጃ የመለወጥ እድል ቢያጋጥመው በቅርስነት መዝግቦ ለተከታዩ ትውልድ ለማስቀመጥ ይረዳል።

## 1.7 የጥናቱ ወሰን

በደላንታ ወረዳ የተለያዩ ዓውዶችን መሠረት በማድረግ የሚከወኑ እጅግ በርካታ የቃል ግጥሞች ይገኛሉ። ለምሳሌ፣ የሥራ ላይ ግጥሞች፣ የሠርግ ግጥሞች፣ የአበሹቴና የኧኽይቦሌ ግጥሞች የምርቃት ግጥሞች፣ የሙሾ ግጥሞች፣ የእረኛ ግጥሞች፣ ወዘተ፣ ጥቂቶቹ ናቸው። በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው በአበሹቴና በኧኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው።

በሌላ በኩል በወረዳው ከሚገኙ ሰላሳ አምስት ቀበሌዎች መካከል ጥናቱ ያተኮረው በአራት ቀበሌዎች ላይ ብቻ ነው። ቀበሌዎቹም ቄዳ ምስትንክር፣ ጎሸሜዳ፣ ዲማ እና አሲም ናቸው። በየቀበሌዎቹ ከአንድ በላይ ቤተክርስቲያኖች ስለሚገኙ ምልከታ የተደረገው በጥር ወር የታቦት ንግሥ ያላቸው አራት ቤተክርስቲያኖች (በየቀበሌዎቹ አንድ) እና ጨዋታዎቹ የሚከወኑባቸው የገና፣ የጥምቀትና የፋሲካ በዓላት ናቸው።

አራቱ ቀበሌዎች የተመረጡት በመጀመሪያ ደረጃ ቀደም ብዬ ቃል ግጥሞቹ በአካባቢው የሚዘወተሩ መሆናቸውን ስለማውቅና በተጨማሪም በተመረጡት ቀበሌዎች መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎችን እንደማገኝ እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። ጥናቱ ከከዋኞች አንጻር በዋናነት አበሹቴና ኸኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን በሚጫወቱ ወጣት ሴቶች ላይ ቢያተኩርም በልጅነት፣ በጎልማሳነትና በአረጋዊነት እድሜ ላይ ያሉ ሴቶችንም ያጠቃልላል። ሌሎች የቃል ግጥም ዓይነቶችን አያካትትም። በአካባቢው ጨዋታዎቹ የሚከወኑት በክርስትና ዕምነት ተከታዮች ብቻ በመሆኑ ጥናቱም በዕምነቱ ተከታዮች ላይ ብቻ ያተኩራል።

## 1.8 የጥናቱ ዘዴዎች

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ መረጃዎች እንዴትና በምን ዘዴ እንደተሰበሰቡና እንደተመረጡ እንዲሁም የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ዘዴና የጥናቱ አከዋወን ሂደት ቀርበዋል።

### 1.8.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በመስክ ምርምር የመረጃ አሰባሰብ ሥራ በሦስት ልዩ ልዩ መልኮች ሊካሄድ ይችላል። እነሱም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በመጠይቅ ናቸው። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ለፎክሎር ጥናት የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቢሆኑም ለዚህ ጥናት የተመረጡት ዘዴዎች ቃለ መጠይቅና ምልከታ ናቸው። በቃለ መጠይቅ መረጃ በማሰባሰቡ ሂደት በተናጠል ከተደረገ ቃለ መጠይቅ በተጨማሪ የቡድን ውይይት በመጠቀም የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል።

ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ ምንጮች ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ለቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የአበሹቴና የኸኸይቦሌ

ቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸው ዓውዶች፣ በክዋኔ ላይ የተሳተፉ ከዋኞችና ታዳሚዎች በተጨማሪም ለክዋኔዎቹ መንስኤ የሆኑ የክዋኔ አጋጣሚዎች ናቸው። ቀዳማይ መረጃዎቹን የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ቦታ በመገኘት በዓውዱ የተገኙትን ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ በመመልከትና በመጠየቅ የቃል ግጥሞቹን የተመለከቱ መረጃዎች በተፈጥሯዊ መቼት ሰብስቤያለሁ። በተጨማሪም የወረዳው የባህል ቡድን ያዘጋጀውን ሙሉ ትርኢት በመከታተል በተለይም የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎችን ክዋኔ በትኩረት በመከታተል አርቴፊሻል መቼት በተፈጠረው አጋጣሚ ተጠቅሜ መረጃ ሰብስቤያለሁ።

በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት መጻሕፍትና መጣጥፎች ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃ ምንጮቹ ከቤተ መጻሕፍት፣ ከኢንተርኔትና ከግለሰቦች የተሰበሰቡ ናቸው።

ከተፈጥሯዊ መቼት መረጃ መሰብሰቤ የቃል ግጥሞቹን የአከዋወን ሂደት ለመረዳት አስችሎኛል። "If the collector is able to observe a natural context, he can learn a great deal about folklore process." በማለት (Goldstein, 1964, 82) ተፈጥሯዊ መቼትን የተጠቀመ የፎክሎር ተመራማሪ ስለፎክሎሩ ብዙ እውቀት ማግኘት እንደሚችል ገልጸዋል። እኔም ቃል ግጥሞቹን ለመሰብሰብና ለመረዳት ሰባት ጊዜ የተፈጥሯዊ መቼት ምልከታ አድርጌያለሁ።

#### 1.8.1.1 ምልከታ

መረጃ ለማግኘት ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል አንዱ ምልከታ ነው። " methods used by the field worker in obtaining data by direct observation" በማለት (Goldstein, 1964, 77) የመስክ ተመራማሪ በቀጥታ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ምልከታ መሆኑን ያስረዳሉ። ከጥቅሱ እንደምንረዳው ምልከታ በአካል ተገኝቶ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ነው። ምልከታ በዋናነት ተሳትፏዊና ኢተሳትፏዊ ተብሎ ለሁለት ይከፈላል። ኢተሳትፏዊ ምልከታ ጽሞናዊና ህቡዕ በሚባሉ ለሁለት ክፍሎች ይከፈላል። ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው ከኢተሳትፏዊ ምልከታ አንዱ የሆነው ፅሞናዊ ዘዴ ነው። ህቡዕ ምልከታ ድብቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ስለሆነ ለዚህ ጥናት አልተጠቀምኩበትም።

የአበሹቴና የኸኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ጾታ ተኮር በመሆናቸው ተሳትፏዊ ምልከታ ማድረግ አልተቻለም። በሌላ በኩል ለዚህ ጥናት በህቡዕ ወይም በድብቅ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም የጽሞናዊ ምልከታ ዘዴን በመጠቀም የጨዋታዎቹን ክዋኔዎች ሂደት ዳር ሆኜ በትኩረት በመከታተል ማስታወሻ በመያዝና በካሜራ በመቅረጽ መረጃው ተሰብስቧል።

### 1.8.1.2 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ከዋሉ ዘዴዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው። በምልከታ ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና ለማዳበር እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል። በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በክዋኔ ወቅት ከተገኙ ታዳሚዎች መካከል የዕድሜና የጾታ ስብጥር በማድረግ ነው። የቃል ግጥሞቹን የሚከውኑት ሴቶች ብቻ ቢሆኑም ከከዋኝና ተሳታፊ ሴቶች በተጨማሪ ወጣትና አዋቂ ወንዶችን፣ የማይጫወቱ ሴቶችን፣ ታዳጊዎችን በመጠየቅ መረጃውን የተሟላ ለማድረግ ተሞክሯል። ስብጥሩ የተለያየ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያላቸው ሰዎች መሆኑ ሰፊና ጥልቅ መረጃ ለማግኘት ይጠቅማል ከሚል እምነት የተደረገ ነው።

መረጃ አቀባዮች በሁለት መንገድ በተቀናበረ የቃለ መጠይቅ ስልት በመጠቀም መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል። ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡት ጥያቄዎች ክፍት እና ዝግ የጥያቄ ዓይነቶች ናቸው። ክፍት ጥያቄዎች ለመረጃ አቀባዩም ሆነ ለመረጃ ሰብሳቢው ነጻነት የሚሰጡ በመሆኑ በጥያቄ ላይ ጥያቄ በመጨመር ዘና ባለ ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ጠቅሟል። አጭር መልስ ለሚያስፈልጋቸውና ማብራሪያ ለማይሹ ጉዳዮች ዝግ ጥያቄ በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል።

በቃለ መጠይቅ ወቅት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች በመጠየቅ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ውሏል።

**የቡድን ውይይት፡-**ለቡድን ውይይት የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች ዘጠኝ ሲሆኑ አምስቱ ቁልፍ መረጃ እንዲያቀብሉ ቀደም ሲል ከተመረጡት መካከል የተወሰዱና ቀሪዎቹ ከተራ መረጃ አቀባዮች መካከል የተመረጡ ናቸው።

መረጃ አቀባዮች በቡድን ውይይት ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉት በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ዘጠኙ መረጃ አቀባዮች መረጃውን ከተሰበሰበባቸው ከሁሉም ቀበሌዎች የመጡ በመሆኑ የተሟላ መረጃ ይገኛል ከሚል እምነት ነው። ሁለተኛው ምክንያት ሌሎች ሰዎችን (መረጃ አቀባዮች ያልሆኑ ሰዎችን) ለቡድን ውይይት መጠቀሙ ጊዜንና ጉልበትን የሚያባክን በመሆኑ ነው። በመረጃ ስብሰባ ወይም በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኘው ተቀባይነትና መግባባት ለቡድን ውይይት ጠቅሟል።

ለቡድን ውይይቱ የተመረጡት ሁሉም ሴቶች ናቸው። እንደ ቃለ መጠይቁ ወንዶች አልተካተቱም። ወንዶች ያልተካተቱበት ዋናው ምክንያት ርዕሰ ጉዳዩን (የአበሹቴና ኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞችን) የሚያውቁት ወይም የሚከውኑት ሴቶች በመሆናቸው ነው። የቡድን ውይይቱ የተካሄደው ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም በቄዳ ምስትንክር ቀበሌ ወገላት በተባለች መንደር ነው። የቡድን ውይይቱ በአራትና አምስት አባላት በተዋቀሩ ሁለት ቡድኖች የተካሄደ ሲሆን የሁለቱም ቡድኖች ውይይት ከጧቱ 3፡30 ሰዓት እስከ 5፡45 ሰዓት ድረስ ለሁለት ሰዓት ከ15 ደቂቃ ያህል ጊዜ በመውሰድ ተጠናቋል።

በውይይቱ ወቅት የአበሹቴና የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞች ምን ምን ጉዳይ ላይ እንደሚያተኩሩ፣ የአበሹቴና የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞችን እንዴት እንደሚደርሱና እንደሚያስተላልፉ፣ ጨዋታዎቹ እንዴት እንደሚለመዱና የጨዋታዎቹ ጥቅም ምን እንደሆነ ውይይት ተደርጓል።

### 1.8.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ክዋኔ ተኮር /Performance centered/ ንድፈ ሃሳብ ነው። Sims እና Stephen ክዋኔ ለአንድ የፎክሎር አጥኚ ጠቃሚ መሆኑን ለመግለጽ "Analyzing performance enables folklorist to see how and why groups shape and share their traditional forms of expression" በማለት የፎክሎር ተመራማሪ ለክዋኔ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠናውን ፎክሎር ከመረመረ ተጠኝዎቹ እንዴትና ለምን ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን እንደሚቀምሩና እንደሚግባቡ ማስተዋል እንደሚችል ገልጸዋል።

ክዋኔ በአንድ በተወሰነ አውድ ወይም ቡድን የሚቀርብን ጥበባዊ ገለጻ ለማጥናት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሃሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ

ድርጊት በመሆኑ ለዚህ ጥናት መቀንበቢያነት በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ነው። በተጨማሪም ጥናቱ ይዟቸው ከተነሳው የምርምር ጥያቄዎች አንጻር ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት በተወሰነ ደረጃ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብም ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህ ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብን መጠቀሙ ሴቶች የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ጊዜ ክዋኔዎቹ ያላቸውን ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ጠቀሜታና አገልግሎት ለማጥናት ያስችላል።

### 1.8.3 የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው። በደላንታ ወረዳ ከሚገኙ 35 ቀበሌዎች መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡት አራት ቀበሌዎች ናቸው። እነሱም ቄዳ ምስትንክር፣ ጎሽሜዳ፣ ዲማ እና አሲም የተሰኙ ቀበሌዎች ናቸው። እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ቀደም ሲል ከበርካታ ዓመታት በፊት አካባቢዎቹን ስለማውቃቸውና የቃል ግጥሞቹ አሁንም በእነዚሁ ቀበሌዎች እንደሚከወኑ በ2000 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና አስተባባሪ ሆኜ በሄድኩበት ወቅት ከአካባቢው ሰዎች መረጃ ስላገኘሁና መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት (በጥር ወር)የየራሳቸው የሆነ የታቦት ንግሥ እንደሚከበርባቸው በማወቄ ነው።

ቃል ግጥሞቹ የሚከወኑበት ገና እና ጥምቀት እንዲሁም በየቀበሌዎቹ የሚገኙ ታቦታት የሚነግሡበት ወቅት ጥር ወር በመሆኑ የመጀመሪያው ዙር የመስክ ጉዞ ለማድረግ ተመርጧል። ሁለተኛው ዙር የመስክ ጉዞ በሚያዝያ ወር (ለፋሲካ በዓል) ተደርጓል። በሁለቱ ዙሮች የመስክ ቆይታውም በአራት የታቦት ንግሥና በሦስት የዓውደ ዓመት ክብረ በዓላት በድምሩ በሰባት በዓላት ላይ በመገኘት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎችን ክዋኔ ለመታደም ተችሏል። በቀበሌዎቹ የሚኖሩ ከ11 ዓመት እስከ 75 ዓመት በሚሆን የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሴትና ወንድ 22 መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። መረጃ አቀባዮቹ ሁሉም የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው።

### 1.8.4 የጥናቱ አከዋወን ሂደት

ጥናቱ የሚከተሉትን የአጠናን ቅደም ተከተል ያለው የአከዋወን ሂደት ተከትሏል።

- በመጀመሪያ ርዕሱንና የጥናት ቦታውን በሚመለከት የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ተካሂዷል።
- ቀጣዩ ተግባር ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ እንደ ካሜራ፣ ባትሪ፣ ብዕር፣ ማስታወሻ ደብተር፣ እርሳስ፣ ባትሪ ድንጋይ ወዘተ የመሳሰሉትን የመስክ መሣሪያዎችን በመግዛት ጥናቱ ወደ'ሚደረግበት ቦታ ጉዞ ተደርጓል።
- ባህላዊ ጨዋታዎቹ የሚካሄድባቸውን ቀናት ወይም አጋጣሚዎችን በመለየትና መርሐ ግብር በማውጣት በሚከናወኑባቸው ቦታዎች በመዘዋወር መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተከናውኗል።
- የአካባቢውን ታሪክና የሚጠኑትን ጨዋታዎች በሚመለከት ለሃይማኖት አባቶች፣ ለአገር ሽማግሌዎችና በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ለሚገኙ ሴቶች ቃለ መጠይቅ ተደርጓል።
- በቃለ መጠይቅና በጨዋታዎቹ ክዋኔዎች ወቅት የተሰባሰቡትን መረጃዎች ወደ ጽሑፍ የመመለስ ሥራ ተሠርቷል።
- በመጨረሻም በመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በየርዕሰ ጉዳያቸው በመመደብ፣ ከ258 የቃል ግጥሞች መካከል 94 የቃል ግጥሞችን ከክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ጋር በማጣጣም ትንተና ተደርጓል።

## 1.9 የመስክ ቆይታ ዘገባ

ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ሁለት ጊዜ ወደ ደላንታ ወረዳ በመሄድ ለ43 ቀናት ያህል ቆይታ አድርጌያለሁ። በእነዚህ የአርባ ሦስት ቀናት የመስክ ቆይታ ጊዜ ምን እንዳደረኩና ምን እንዳጋጠመኝ፣ በአጠቃላይ በመስክ ቆይታዬ ምን እንዳስተዋልኩ ለጀማሪ የፎክሎር አጥኝዎች ልምድ ለማካፈል ያህል እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ለዚህ ጥናት በግብአትነት ያገለገሉኝን መረጃዎች ለመሰብሰብ ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተነስቼ የደቡብ ወሎ ዞን ዋና ከተማ የሆነችው ደሴ ከተማ ገብቼ አደርኩ። በማግስቱ ጠዋት ተነስቼ ወደ ደላንታ ለመሄድ ደሴ አውቶቡስ ተራ ስገባ ለገና በዓል ወደ ወረዳው በሚሄዱ መንገደኞችና የጉዞ ትኬት ደላሎች ቦታው በሰልፍ ተጥለቅልቆ አገኘሁት። በዕለቱ መጓዝ እንደማልችል ስለተረዳሁ ወደ ሆቴል ተመልሼ

ሻንጣዬን አስቀምጬ ቁርሴን ከበላሁ በኋላ በቀጣዩ ቀን እንዴት መጓዝ እንደምችል እያውጠነጠንኩ ወደ አውቶብስ ተራው ተመለስኩ።

አውቶብስ ተራ ከገባሁ በኋላ መረጃ ሳሰባስብ ተሰልፎ የጉዞ ትኬት ማግኘት ከባድ መሆኑን ይልቁንም ከሦስት እጥፍ በላይ በመክፈል ከትኬት ደላሎች በቀላሉ ማግኘት እንደምችል ተረዳሁ። በመሆኑም ሳልወድ በግድ ከመደበኛ ዋጋው ከሦስት እጥፍ በላይ ከፍዬ የጉዞ ትኬቱን ለመግዛት ተስማምቼ ወደ ወረዳው ለመሄድ ወሰንኩ።

ታህሳስ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ከደላሎች ያገኘሁትን የጉዞ ትኬት ተጠቅሜ በጧት የሚነሳውን የመጀመሪያውን አውቶብስ ተሳፍሬ የደላንታ ወረዳ ዋና ከተማ ወገልጤና ከጧቱ ሦስት  ሰዓት ደረስኩ። በመጀመሪያ ወደ ወረዳው አስተዳደር በመሄድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በማሳየትና በቃል በማስረዳት የትብብር ደብዳቤ አ'ፃፍኩ። በዕለቱ ከሰዓት በኋላ ወደ ወረዳው ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤትና ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በመሄድ የትብብር ደብዳቤዎቹን በማሳየት ከተዋወቅኩ በኋላ አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን ሰበሰብኩ። በተለይ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኀላፊ ለጥናቱ እገዛ እንደሚያደርጉልኝ ቃል ገብተው፣ አቶ ሠለሞን ቸኮል እና አቶ አለምነህ ዋሴ ከተባሉ ወጣት የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች ጋር በማስተዋወቅ ለጥናቱ መረጃ ስሰበስብ እንዲረዱኝ መደቡልኝ።

ታህሳስ 28 ቀን 2006 ዓ.ም ከወገልጤና ከተማ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ 15 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዤ ቄዳ ምስትንክር ቀበሌ በማደር በገና በዓል የሚደረገውን የአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ለመከታተል ዝግጅት አደረኩ። በማግስቱ ታህሳስ 29 ቀን 2006 ዓ.ም "ወገላት" በተባለች መንደር ከመስክ ረዳቴ ደስታው አስማማው ጋር ተገኝተን መረጃ ስንሰበስብ ዋልን። ደስታው በካሜራ ሲቀርፅ እኔ በጥሞና ስከታተል ቆይቼ ጨዋታው ሲጠናነቅ ወደ ማደሪያችን ተመልሰናል።

ጥር 3 ቀን 2006 ዓ.ም ወደ ገበያ ከሚሄዱ ሰዎች ጋር ወደ ወገልጤና ከተማ በመሄድ በአካባቢው ከታወቁ የአገር ሽማግሌዎች ጋር ቀጠሮ ለመያዝ ሙከራ አደረኩ። አቶ ሥጦታዬ አስማሜ ጥር 4 ቀን 2006 ዓ.ም መረጃ ሊሰጡኝ ሲስማሙ ሌሎቹን ተፈላጊ ሰዎች በወቅቱ ለማግኘትና ቀጠሮ ለመያዝ አልቻልኩም። በማግስቱ ጥር 4 ቀን ከአቶ ሥጦታዬ ጋር በመገናኘት አስፈላጊውን መረጃ ሰበሰብኩ።

ጥር 5 ቀን 2006 ዓ.ም ከወገልጤና ከተማ ወደ ደሴ በሚሄደው አውቶብስ ተሳፍሬ ጎሸ ሜዳ ቀበሌ ከሄድኩ በኋላ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አራት ኪሎ ሜትር ያህል በእግር በመጓዝ ድንግሎት በምትባል ጎጥ ወ/ሮ አታሉ አስሜ መኖሪያ ቤት በመሄድ ስለጨዋታዎቹ መረጃ ሰብስቢያለሁ። ወ/ሮ አታሉ ጥር 7 ቀን ቁዳ ለሚከበረው የሥላሴ በዓል እንደሚጫወቱና እዛው ተገኝቼ ሲጫወቱ እንዳያቸው ጋብዘውኝ ጥር 21 ቀንም በጎጣቸው የምትገኘው ድንግሎት ማሪያም ፅበል እንድቀምስና ጨዋታውን እንድመለከት በድጋሚ ጋብዘውኝ ተለያየን። በዕለቱ ወ/ሮ ደስታ በሪሁንና ወ/ሮ አስረበብ ዘገዬ ከተባሉ የወ/ሮ መረጃ ሰጪዎቼ ጋር ለጥር 15 ቀን ቀጠሮ ይዤ ወደ ማደሪያ ቦታዬ ተመለስኩ።

ጥር 6 ቀን 2006 ዓ.ም ከመስክ ረዳቴ ደስታው አስማማው ጋር በመሆን ወደ ጠቅላዲ ሄድን። ወደ ጠቅላዲ ስንጓዝ የዳገቱና የቁልቁለቱ ርዝመት የመንገዱ ወጣ ገባነት በእጅጉ ተፈታትኖናል። ጉዞአችንን የጀመርነው በጧት አንድ ሰዓት ላይ ቢሆንም አምስት ኪሎ ሜትር ያህል እንደተጓዝኩ ደከመኝ። በየመቶ ሜትሩ ቁጥቋጦ ስር እያረፍን 15 ኪሎ ሜትር ለማጠናቀቅ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ተጉዘን አሲም ቀበሌ ደረስን። በማግስቱ የስላሴ በዓል ላይ መገኘት ስላለብኝ ቢደክመኝም ማደር አልቻልኩም። ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ እና ወ/ሮ የሺወርቅ አለሙ የተባሉ በአካባቢው የታወቁ ሰዎችን ለማነጋገር ለጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም ቀጠሮ ይዤ ተመለስኩ። በቀጠሮው መሰረት ጥር 9 ቀን ወደ መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ መረጃ ሰበሰብኩ። በዚህ ቀን ያደረኩት ጉዞ እንደመጀመሪያው አልከበደኝም። ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ በጣም ተግባቢና ጨዋታ ወዳድ ሴት ከመሆናቸውም በላይ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው በመሆኑ በርካታ መረጃዎችን ሰጥተውኛል።

ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም በቁዳ ምስትንክር ቀበሌ የቁዳ ሥላሴ ክብረ በዓል ላይ በመገኘት የጨዋታዎቹን ክዋኔ በአካል በመገኘት መረጃ ሰበሰብኩ። ጥር 11 ቀን 2006 ዓ.ም የጥምቀት በዓል ሲከበር በዚሁ ቀበሌ በሚገኘው ቁዳ ሥላሴ በአካል በመገኘት መረጃ ሰበሰብኩ።

ጥር 12 ቀን ዲማ ቀበሌ በመሄድ የሚካኤል ታቦት ንግስ ዕለት ልዩ ስሟ ሎሚ ከተማ በተባለች ጎጥ ተገኝቼ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎችን ክዋኔ ተመልክቻለሁ።

አስፈላጊውን መረጃ በፎቶ እና በቪዲዮ ካሜራ ቀርጬ ወደ ማደሪያ ቦታዬ ተመልሻለሁ።

ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየን ቃለ መጠይቅ ያደረኩበት ቀን ነው። እንደ ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ ሁሉ እሳቸውም በርካታ መረጃ ሰጥተውኛል። ወ/ሮ ብርዘገን የቃል ግጥሞቹን ማስታወስ ብቻ ሳይሆን የቃል ግጥሞቹን ታሪክ ጭምር ማን ለምንና እንዴት እንደደረሳቸው በዝርዝር ከነዜማው አሰምተውኛል።

ጥር 15 ቀን ከቁዳ ምስትንክር ቀበሌ ተነስቼ ወደ ጎሸሜዳ ቀበሌ አመራሁ። ጎሸሜዳ ቀበሌ ድንግሎት ጎጥ ከሁለት ሴቶች የምፈልገውን መረጃ ከሰበሰብኩ በኋላም ወደ ማደሪያዬ ተመለስኩ።

ጥር 18 ቀን ጠቅላዲ በሚሄድ የሰባር አፅሙ ጊዮርጊስ የታቦት ንግሥ ከረዳቴ እመቤት ያረጋል ጋር በመሆን በአካል ተገኝቼ የጨዋታዎቹን ክዋኔ በመመልከት መረጃ ሰበሰብን። ቀደም ሲል በየሄድኩበት እየተከተለ ሲረዳኝ የነበረው ደስታው የተባለው ረዳቴ የሰርግ ጥሪ ስለነበረው አብሮኝ ሊሂድ አልቻለም። በዕለቱ ከእመቤት ጋር ጨዋታን ስከታተል ውዬ እዛው ቀበሌ በማደር አቶ መራጊያው ከቤ ከተባሉ ሰው መረጃ ሰብስቤ በማግስቱ ዲማ ቀበሌ ለያዝኩት ቀጠሮ ዝግጅት ለማድረግ ተመለስኩ።

ጥር 21 ቀን 2006 ዓ.ም ጎሸሜዳ ቀበሌ ድንግሎት ጎጥ የድንግሎት ማርያም በአካል በመገኘት መረጃ እየሰበሰብኩ እያለሁ ወገልጤና ከተማ የተዋወቅኩት የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ወጣት ሠለሞን ቸኮል ደውሎ መጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ ሊያነጋግሩኝ እንደሚችሉና ቀጠሮ ያስያዘልኝ መሆኑን ነገረኝ። ጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም በጧት ተነስቼ ጎሸሜዳ በሚሄድ ከደሴ የሚመጣውን አውቶብስ ተሳፍሬ ሦስት ሰዓት ወገልጤና ከተማ ደረስኩ። ወዲያውኑ ከወጣት ሠለሞን ጋር በመሆን "በባጃጅ" ተሳፍረን ከከተማው ዳር ወዳለው የመጋቢ ቢሮ ሄደን መረጃ ሰበሰብኩ።

ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ መኖሪያ ቤት ከአራት ቀበሌዎች የተወጣጡ ሴቶች ጋር የቡድን ውይይት አደረኩ። ከእያንዳንዱ ቀበሌ 3 ሴቶችን በድምሩ 12 ሴቶችን ለማወያየት ቀጠሮ የያዝኩ ቢሆንም የተገኙት 9 ሴቶች ብቻ ናቸው። ዘጠኙን ሴቶች በሁለት ቡድን በመክፈል ውይይቱን እየመራሁ መረጃ ሰበሰብኩ።

ጥር 28 ቀን 2006 ዓ.ም ከወገልጤና ከተማ በአውቶብስ ተሳፍሬ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርኩ። በዕለቱ ደሴ ከተማ አድሬ በማግስቱ እንደቀድሞው የጉዞ ትኬት ችግር ሳያጋጥመኝ አውቶብስ አማርጬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ከመስክ ተመልሼ መረጃዎቼን ቀደም ብዬ ከመጻሕፍት ካገኘኋቸው ንድፈ ሃሳቦች ጋር እያመሳከርኩ በመሥራት ላይ እያለሁ በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ መሥሪያ ቤት ተጠርቼ አስቸኳይ ሥራ ስላለ ጎን በጎን እገዛ ብታደርግልን የሚል ጥያቄ ቀረበልኝ። የተሰጠኝ ስራ ግን ጎን ለጎን ጥናቴን ለመሥራት የሚያመች ባለመሆኑ ከአንድ ወር በላይ በሥራው ላይ ተጠመድኩ። የትምህርት ክፍላችን የመጨረሻውን ረቂቅ ሚያዝያ 30 ቀን 2006 ዓ.ም ለትምህርት ክፍሉ እንድናስገባ ማስታወቂያ ስላወጣ በወቅቱ ጥናቴ ሊደርስልኝ እንደማይችል ተገነዘብኩ።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች በአሁኑ ጊዜ በየአመቱ ለመጨረሻ ጊዜ የሚከወኑት በፋሲካ በዓል ነው። ቀደም ሲል ግን የሚከናወኑት በፋሲካ በዓል ብቻ ነበር። 'ታዲያ ለምን ወደ ወረዳው ተመልሼ በዕለቱ ያለውን አውድ አልመለከትም?' ብዬ ራሴን በመጠየቅ እንደገና ወደ ወረዳው ለመሄድና ክዋኔውን ለመመልከት ወሰንኩ። በዚህም ምክንያት ከሚያዝያ 7 ቀን ጀምሮ ቄዳ ምስትንክር ቀበሌ በመገኘት እስከ ሚያዝያ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ለ 9 ቀናት ቆይቼ ተጨማሪ መረጃ በመሰብሰብ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ። ከመስክ መልስም በመቅረፀ ድምፅ ወምስል የተሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ ማስታወሻ ደብተር በመገልበጥ በተሰበሰቡበት አውድ መሠረት በርዕሰ ጉዳይ ምደባ አደረኩ። ምደባውን ከጨረስኩ በኋላ ለሁለት የክፍል ጓደኞቼ በማሳየት ምደባዬን የሚያጸና አስተያየት ተቀበልኩ።

በአጠቃላይ በመስክ ቆይታዬ ከክዋኔ አንጻር የተከታተልኳቸው የክዋኔ አጋጣሚዎችና ከከዋኞችና ከታዳሚያን አንጻር ያስተዋልኳቸው አንዳንድ ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ክዋኔዎች**:- ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ በተደረገው የሁለት ጊዜ ጉዞና የ43 ቀናት የመስክ ቆይታ የመጀመሪያው ዙር ከታህሳስ 25 እስከ ጥር 28 ቀን 2006 ዓ.ም ሲሆን ሁለተኛው ዙር ከሚያዝያ 7 እስከ 15 /2006 ዓ.ም ለዘጠኝ ቀናት ነበር። በመስክ ቆይታውም በአራት የታቦት ንግሥና በሦስት የዓውደ ዓመት ክብረ በዓላት በድምሩ በሰባት በዓላት ላይ በመገኘት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎችን ክዋኔ ለመታደም

ተችሏል። በቦታው በመገኘት በአራቱ ቀበሌዎች በተለያየ መንደር፣ በቄዳ ስላሴ፣ በዲማ ሚካኤል፣ በጠቅላዲ ጊዮርጊስና በድንግሎት ማሪያም የታቦታት ንግሥ እንዲሁም የገና፣ የጥምቀትና የፋሲካ ክብረ በዓላት ክዋኔዎችን ለመከታተል ተችሏል።

**ከዋኞች**:- የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች በሴቶች ብቻ የሚከወኑ ጾታ ተኮር ስለሆኑ ከዋኞቹ በአብዛኛው በእድሜ ወጣት የሆኑ ሴቶች ናቸው። አልፎ አልፎ እናቶችም በከዋኝነት ይሳተፋሉ። ሁሉም ሴቶች ተራ በተራ ከዋኝ የመሆን እኩል ዕድል ያላቸው ቢሆንም ይበልጥ በከዋኝነት የሚሳተፉት ማራኪ ድምፅ ያላቸውና ብዙ የቃል ግጥሞችን የሚያውቁ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎችን  የመጫወት ፍላጎት ያላቸው ሴቶች እየተሰባሰቡ ቡድን በመመስረት መጫወት የሚችሉ በመሆኑ ገደብ የሌላቸውና ሁሉም ሴቶች ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ጨዋታዎች ናቸው። በጨዋታው ጥሩ ድምጽ ያላቸው አቀንቃኞች ያሉባቸው ቡድኖች በዙሪያቸው በርካታ ተመልካቾችን ያሰባስባሉ። በጨዋታው ሂደት ተመልካች የነበሩት ወደ ከዋኝነት ከዋኝ የነበሩም በተራቸው ወደ ታዳሚነት መሸጋገር የተለመደ ነው።

**ታዳሚዎች**:- በአበሹቴና በኧኸይቦሌ ጨዋታዎች የሚገኙ ታዳሚዎች ብዛት እንደ ክብረ በዓሉ ዓይነት የተለያየ ነው። በገናና በፋሲካ በዓላት የታቦት ንግሥ ስለማይኖር ጨዋታው የሚከናወነው በየመንደሩ ወይም በየጎጡ በሚሰባሰቡ ሰዎች ብቻ ነው። በአማቶቻቸው የመልስ ጥሪ ምክንያት ወይም በሌላ አጋጣሚ ወደ መንደሩ ከመጡ እንግዶች በስተቀር የመንደሩ ሰዎች ብቻ ተሳታፊዎች የሚሆኑበት ጨዋታ ነው።

የታቦት ንግሥ በሚኖርበት ወቅት ግን የታዳሚዎች ብዛት ይጨምራል። ለምሳሌ የዲማ ሚካኤል በሚነግሥበት ዕለት ከአካባቢው ነዋሪ በተጨማሪ በቀበሌው ዙሪያና ራቅ ካሉ ቦታዎች በሚሰባሰብ የሰው ብዛት ምክንያት የታዳሚዎች ቁጥር በእጅጉ ጨምሯል።

## 1.10 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

ይህ ጥናት ሲደረግ አብዛኛው ሥራ በመስክ ስራ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን የተወሰኑ ችግሮችን መጋፈጥ የግድ ነበር። ካጋጠሙ ችግሮች መካከል በገጠር መንደሮች የመብራት አለመኖር (ለቀረጻ የሚሆን የባትሪ ቻርጅ ማለቅ) በዋናነት

የሚጠቀስ ነው። ለዚህም ትርፍ የሚሞሉ ባትሪዎችን በመግዛትና በቅርብ ርቀት በሚገኙ ወገልጤና እና ጎሽሜዳ ከተማዎች በመላክ ሀይል በማስሞላት ችግሩን ለማቃለል ተችሏል።

አንዳንድ የመረጃ ሰጪዎች በቀጠሮ ቀን አለመገኘትና ቢገኙም መረጃ ለመስጠት ዳተኛ የመሆን ችግርም አጋጥሟል። ችግሩን ለመፍታት ስለጥናቱ ዓላማ በተደጋጋሚ በማስረዳትና በአካባቢው በቀላሉ የማይገኙ ቢገኙም በአንጻራዊነት ከሌላው አካባቢ ውድ የሆኑ እንደ ቡና እና ስኳር የመሳሰሉ ስጦታዎችን በማድረግ የመረጃ ሰጭዎቹ ፈቃድ ተገኝቷል።

ሌላው ያጋጠመ ችግር የትራንስፖርት ችግር ነው። ሁለቱም የመስክ ጉዞዎች የተደረጉት በዓበይት የክርስቲያን በዓላት መዳረሻ ላይ ስለነበር (ገናና ፋሲካ) የከፋ የትራንስፖርት እጥረት ነበር። ለዚህም ችግር ከታሪፉ ውጭ ተጨማሪ ብር በመክፈል ችግሩን በማቃለል በወቅቱ ወደታሰበበት ለመድረስ ተችሏል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ቀርበዋል። የመጀመሪያው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ሲሆን ሁለተኛው የኧኸይቦሌና አበሹቴ ቃል ግጥሞች የሚታዩበት ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ነው። በዚህም ቃል ግጥሞቹን ለመተንተን ጥቅም ላይ የሚውለው ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ (Performance Center theory) በዋናነት ለምን እንደተመረጠ፣ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዲሁም በቃል ግጥም ክዋኔ ዙሪያ ምሁራን የሰጧቸው ብያኔዎችና ሃሳቦች ቀርበዋል።

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ባደረኩት ዳሰሳና ምርምር የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞችን በተመለከተ በሌሎች አጥኝዎች የተደረገ ጥናት አላገኘሁም። ሆኖም ግን በአካባቢው ባይሆንም በርዕሰ ጉዳዩ በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይነት ያለው በብርሃን አሰፋ አርጋው በ1997 ዓ.ም ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ "የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔና የግጥሞቹ ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ አግኝቻለሁ። ከዚህ ጥናት በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም ተመሳሳይነት ያለው በአፀደ ተፈራ "በሰቆጣ ከተማ የክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ አግኝቻለሁ።

በአፀደ ተፈራ በቀረበው ጥናት በሰቆጣ ከተማ የፍልሰታ፣ የመስቀልና የጥምቀት ክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች በዝርዝር ተቃኝቷል።

በጥናቱ በፍልሰታ ክብረ በዓል ላይ አሸንዳ ወይም ሻደይ በሚባል ስያሜ የሚታወቅ የሴቶች ጨዋታ እንደሚከወን ተገልጿል። ጨዋታው በከተማ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ከነሐሴ 16 እስከ ነሐሴ 18 የሚከወን ሲሆን በገጠር ደግሞ ለስድስት ቀናት ከነሐሴ 16 እስከ ነሐሴ 21 እንደሚከወን ተብራርቷል። የሻደይ ጨዋታ የድንግል ማሪያምን ዕርገት ምክንያት በማድረግ የሚከወን በመሆኑ ሃይማኖታዊ መሠረት እንዳለው በጥናቱ ተመልክቷል።

በጥናቱ የሻደይ ጨዋታ በቡድን በየቤቱ እየዞሩ በመጨፈር ገንዘብ የማሰባሰብ ዓላማ ያለው መሆኑ ተገልጾ ቃል ግጥሞቹ የሙገሳና የስድብ ይዘት እንዳላቸው ተብራርቷል።

በሁለተኛነት በተገለጸው የመስቀል ክብረ በዓል ተሲነነ እና ዋርዳ ሆይ የሚሰኙ ሁለት ጨዋታዎች እንደሚከወኑ በጥናት ጽሑፉ ተገልጿል። ሁለቱም ጨዋታዎች በተመሳሳይ ወቅት ከመስከረም አንድ እስከ መስከረም አስራስድስት በምሽት ወቅት የሚከወኑ ናቸው። ልዩነታቸው በሚከወኑበት ዓላማና በከዋኞቹ ማንነት ነው።

ተሲነነ የተሰኘው ጨዋታ በዲያቆናትና በመሪጌታዎች የሚከወን ሲሆን ዋርዳ ሆይ የተሰኘው ጨዋታ ደግሞ እድሜያቸው ከ15 እስከ 20 ዓመት በሚሆናቸው ወጣቶች የሚከወን መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል። ሌላው የሁለቱ ጨዋታዎች ልዩነት በተሲነነ ዲያቆናቱና መሪጌታዎቹ በቡድን ሆነው ከበሮ እየመቱ በየቤቱ በመዞር በቃል ግጥሞቻቸው እያወደሱ ገንዘብ ያሰባስባሉ። ገንዘቡንም ለቤተክርስቲያን እንደሚሰጡ ተገልጿል። ዋርዳ ሆዬ የተሰኘው የወጣቶች ጨዋታ ግን ገንዘብ የመሰብሰብ ዓላማ የሌለው ለመዝናናት አገልግሎት ብቻ የሚውል መሆኑ ተመልክቷል።

በጥናቱ በሦስተኛነት የተጠቀሰው የጥምቀት ጨዋታ በሰቆጣ ከተማ ለሦስት ቀናት የሚከበር ሲሆን በሦስት ቡድኖች የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞች ይከወናሉ። በሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተደራጀው ቡድን ሃይማኖታዊ መዝሙር ሲዘምር የልጃገረዶችና የእናቶች ቡድን ታቦት እስኪገባ ሃይማኖታዊ ግጥሞችን ይጫወታል። ታቦት ከገባ በኋላ ግን ቡድኑ ዓለማዊ ግጥሞችን ይዘፍናል። ሦስተኛው በወጣት ወንዶች የተደራጀው ቡድን በማንኛውም የደስታ ጊዜ የሚዜሙ ጨዋታዎችን ይከውናል በማለት ጥናቱ ያጠቃልላል።

ይህን ጥናት ከኔ ጥናት ጋር በመጠኑም ቢሆን የሚያመሳስለው ሻደይ ወይም አሸንዳ የተሰኘው የሴቶች ጨዋታ አከዋወንና የይዘት ትንተና ነው። የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ጨዋታዎችም ሆኑ የሻደይ ጨዋታ ሃይማኖታዊ መሠረት ያላቸው መሆኑና በሴቶች መከወናቸው ጥናቶቹን በተወሰኑ ደረጃዎችም ቢሆን የሚያመሳስላቸው ነጥቦች ናቸው።

ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳዮች ቢኖሩትም በርካታ ልዩነቶችም አሉት። የእኔ ጥናት የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ክዋኔና የይዘት ትንተና ላይ ሲያተኩር የአፀደ ተፈራ ጥናት ግን ይበልጥ ትኩረቱን ያደረገው በሻደይ በመስቀልና በጥምቀት በዓላት አከባበር ላይ ነው። ሌላው ልዩነት በእኔ ጥናት የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ብቻ የተሰበሰቡ ሲሆን በተጠቀሰው ጥናት ግን በርከት ያሉ የቃል ግጥም ዓይነቶች ተሰብስበዋል። በጥናቱ የሻደይ፣ የተሲነነ፣ የ"ዋርዳ ሆይ"

የዘፈን ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል። በተጨማሪ የሚከወኑባቸው መልክአምድራዊና የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎችም ልዩነት አለ። የሻደይና ተሲነነ ቃል ግጥሞች የሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች በክረምትና በመስቀል ሲሆን የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ግን በበጋ ወራት ብቻ ነው።

ብርሃን አሰፋ የአሆላሌ ጨዋታ ምንነትና አመጣጥን የባህሉ ባለቤቶች የሰጡትን መረጃ አብራርቶ አቅርቧል። "አሆላሌ" የዘፈኑ አዝማች መሆኑን ገልጾ ጨዋታው በአንዲት አቀንቃኝ (አውራጅ) እና በበርካታ ተቀባዮች የሚከወን መሆኑን አስፍሯል። የጨዋታው አመጣጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ጋር ተያይዞ እንደሆነና ሀይማኖታዊ መሠረት እንዳለው አስረድቷል።

ጨዋታው የሚከወነው ዐበይት የክርስቲያን በዓላት (ገና፣ ጥምቀት፣ ጥር ሚካኤል። የጥር አስተርዕዮ ማሪያም) እንዲሁም በሙስሊም በዓላት በሆኑት አረፋ እና አሹራ በተጨማሪም ሠርግ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን በእንጨት ለቀማና በከብት ጥበቃ ጊዜም እንደሚከወን አብራርቷል።

የአሆላሌ ግጥሞች የይዘት ትንተና በሚለው ርዕስ ሥር አጥኝው ግጥሞቹን በስምንት ዓይነት በመመደብ ይዘታቸውን ተንትኖ አቅርቧል። በዋናነት ልጃገረዶች ወዳጆቻቸውን እንዲሁም ወጣት ወንዶች በተራቸው ልጃገረዶቹን የሚያሞግሱባቸውና የሚያንኳስሱባቸው ቃል ግጥሞች ተመርጠው የሚያስተላልፉት መልእክት ምን እንደሆነ ለማሳየት ይዘታቸው ተተንትኗል።

የአሆላሌ ጨዋታ ከኧኸይቦሌና ከአበሹቴ የሚመሳሰልበትና የሚለያይበት ገፅታዎች አሉት። ከተመሳሰሏቸው ብንጀምር ሁለቱም ጨዋታዎች በግጥም ይዘቶቻቸው፣ እንዲሁም በመከሰቻ አጋጣሚዎቻቸው በመጠኑ ይመሳሰላሉ። በይዘቶቻቸው ሁለቱም ማሞገስና ማንኳሰስ የሚታይባቸው ሲሆን በመከሰቻ አጋጣሚዎቻቸው ሁለቱም በበዓላት ወቅት የሚከወኑ መሆናቸው ነው።

በአንፃሩ ልዩነቱን ስናይ አሆላሌ ጨዋታ በክርስቲያንና በሙስሊም በዓላት እንዲሁም በሰርግ የሚከውን ሲሆን የኧኸይቦሌና አበሹቴ ጨዋታዎች ግን በክርስቲያን በዓላት ብቻ የሚከወኑ ናቸው። በሌላ በኩል የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔ ክብ በመስራት ብቻ የሚከወን ሲሆን በኧኸይቦሌና በአበሹቴ ግን የክብ መሥራት ክዋኔ ያለው በኧኸይቦሌ

ሲሆን በቀጣይ ጨዋታ በአበሹቴ ግን ሁለት ተቃራኒ ቡድን በመስራት የየቡድኑ አባላት በመተቃቀፍ መስመር ሰርቶ ወደፊት በመጠጋትና ወደኋላ በማፈግፈግ የሚከወን ነው።

በአሆላሌ ጨዋታ ወንዶች በራሳቸው ዜማ ቢሆንም ግጥም የመደርደርና የመጫወት እድል አላቸው። በኧኸይቦሌና በአበሹቴ ግን ዳር ሆኖ ከመመልከትና ታዳሚ ብቻ ሆነው ግጥምና ዜማውን እየሰሙ በሳቅና በግርምት ከማጀብ ያለፈ ሌላ ተሳትፎ የላቸውም።

በአሆላሌ ጨዋታ መጨረሻ ወጣቶች የመሳሳም ሥርዓት ሲኖራቸው በኧኸይቦሌና በአበሹቴ ግን የመሳሳም ባህል የለም። በመሆኑም በሁለቱ ጨዋታዎች መካከል የተወሰኑ ተመሳስሎዎች ቢኖሯቸውም በርካታ ልዩነቶችም አሏቸው።

ይህን ጥናት ከተጠቀሱት ጥናቶች በዋናነት የሚለየው ጉዳይ ጥናቱን ለማድረግ የተመረጠበት የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፍ ነው። በዚህ ጥናት በዋናነት ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብን በመጠቀም የኧኸይቦሌና አበሹቴ ቃል ግጥሞችን ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። ቃል ግጥሞቹን በተናጠል ወስዶ ከመተንተን ይልቅ ከክዋኔያቸው ጋር በማስተሳሰር ማየት መቻሉ ይህን ጥናት የተለየ ያደርገዋል። በሁለቱም ጥናቶች የቃል ግጥሞቹን ይዘት ከመተንተን ውጪ የተጠቀሙበትን የንድፈሃሳብ ማዕቀፍ አይገልጹም።

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

አንድን የፎክሎር ዘርፍ ለማጥናት በቅድሚያ ለፎክሎር ዘርፉ ተስማሚ የሆነውን ወይም የሆኑትን የንድፈ ሃሳብ ዓይነቶች ለይቶ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው። የቃል ግጥም ከሚጠናባቸው ንድፈ ሃሳቦች መካከል በአሁኑ ጊዜ በዋናነት ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ በስፋት የሚሠራበት ሲሆን በተጨማሪም ሌሎች ንድፈ ሃሳቦችም አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ጥናቱ የሚቃኝባቸው ንድፈ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን በውስጡም የክብረ በዓላት ዘፈኖች ምንነት፣ ክዋኔ፣ አውድ፣ ድረሳ፣ ተስተላልፎና የቃል ግጥም ጠቀሜታ በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

### 2.2.1. የክብረ በዓላት ዘፈኖች

የክብረ በዓላት ዘፈኖችን ምንነት ከመገለጹ በፊት የክብረበዓል ምንነትን መግለጹ ተገቢነት አለው። በቀጣይ የክብረ በዓላት ዘፈኖችን ምንነት ለመረዳት መንገድ

ይከፍታል። ደስታ ተክለወልድ የክብረበዓልን ምንነት "የበዓል ክብር፣ ገናን፣ ጥምቀትን፣ ትንሳኤን፣ ጰራቅሊጦስን፣ መስቀልን፣ ፍልሰታን፣ ኅዳር ሚካኤል፣ ማዚያ ጊዮርጊስን፣ ለመሰለ በዓል የሚደረግ ማሕሌት፣ ዘፈን፣ ንግስ፣ እልልታና ደስታ፣ ሥራ አለመስራት፣ መንገድ አለመሄድ።" (1950፣ 636) በማለት ይገልጹታል። ክብረ በዓል ሲባል በዓላቱ የሚታሰቡበት ቀናት ብቻ ሳይሆኑ ከበዓላቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑትንም ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለምሳሌ ማህሌት፣ ዘፈንና እልልታ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

Sims እና Stephen ክብረ በዓልን አስመልክተው "Rituals are repeated, habitual actions, highly organized and controlled…bring together many types of folklore." (2005,95) በማለት ክብረ በዓላት በአንድ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ የሚያከብራቸውና በርካታ የፎክሎር ዓይነቶች የሚከወንባቸው መሆናቸውን ይገልጻሉ።

"አንዳንዶቹ ክብረ በዓላት በእምነት ላይ የተመሠረቱ ሀይማኖታዊና መንፈሳዊ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ አለማዊ ናቸው።" (ዘሪሁን አስፋው፣ 1992፣ 54) ክብረ በዓላቱ ሀይማኖታዊ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ እንደሆኑ ሁሉ በየክብረ በዓላቱ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችም መንፈሳዊና ዓለማዊ ሊሆኑ ይችላሉ። አበሹቴና ኾኽይቦሌም በሀይማኖታዊ በዓላት የሚከወኑ ዓለማዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ናቸው።

የክብረ በዓላት ዘፈኖች አንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን በበዓላት ቀናት የሚከውናቸው ወይም የሚያቀነቅናቸው ቃል ግጥሞች ናቸው። የበዓሉ ተሳታፊዎች በዓሉን በዘፈንና በጭፈራ ማሳለፋቸው የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ያጠናክርላቸዋል፤ ማህበራዊ ህይወታቸው ይበልጥ የተሳሰረ እንዲሆን ያደርግላቸዋል።

### 2.2.2. ክዋኔ

ክዋኔ ለቃል ግጥም ህልውናው ነው። የቃል ግጥም መልእክት ከነሙሉ ለዛው ከቦታ ወደ ቦታ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ክዋኔ ወሳኙን ድርሻ ይይዛል። የቃል ግጥም ክዋኔ ሲነሳ ከዋኙን፣ በክዋኔ ወቅት የሚሳተፉትን ታዳሚያንን፣ በክዋኔ ወቅት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት፣ እንዲሁም ቃል ግጥሙ የሚከወንበትን መቼት አጣምሮ መመልከት ይገባል። እነዚህ የተጠቀሱ ጉዳዮችን አጣምሮ ለማጥናት

ደግሞ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ተመራጭ ነው። በመሆኑም ለዚህ የቃል ግጥም ጥናት የተመረጠው የንድፈ ሃሳብ ዓይነት ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ነው።

ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ፣ ጉዳይን /text/ ብቻ ነጥሎ የሚያይ ሳይሆን የአጥኚውን ግለሰብ እውቀትና ግንዛቤ እንዲሁም የሚጠናውን ማህበረሰብ እውቀት የሚያስተሳስር ነው። በመሆኑ ለአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃላዊ ግጥሞች ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል። Bauman የፎክሎር ጥናት ከጉዳይ ተኮር /text centered/ ወደ ክዋኔ ተኮር የተሸጋገረ መሆኑን ከቲያትር ጥበብ ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ይገልፀዋል።

> …theater people, for example, have long been interested in the relationship between play script and performance and the process of moving from the former to the latter. Folklorists, to take another example, contrast text centered perspective, which focus on disembodied, abstract folklore items, with performance centered perspectives, which are concerned with the actual use of folklore forms. (Richard Bauman, 1992, 42)

ከጥቅሱ እንደምንረዳው የቲያትር ጥበብ ባለሙያዎች ተውኔቱን ከማጥናት ይልቅ ክዋኔውን ለማጥናት ይበልጥ ትኩረታቸውን እንደሳበው ሁሉ በፎክሎር ጥናትም ክዋኔ ተኮር ጥናት ይበልጥ የተሻለ ሆኖ ታይቷል።

የፎክሎር ተመራማሪዎች፣ ክዋኔ የተለየውን የፎክሎር ጥሬ መረጃ ማጥናት፣ ተጨባጭነት የሌለውና ነፍሱ የተለየው በመሆኑ ትኩረታቸውን ክዋኔ ተኮር የፎክሎር ጥናት ላይ አድርገዋል።

እነ Sims ለፎክሎር ጥናት ክዋኔ ትልቅ ሚና እንዳለውና ይህ ንድፈ ሃሳብም በዚህ ዘመን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ አጠንክረው ይገልፃሉ። "The performance approach helped to establish expression in groups and specific contexts. (2005, 26) ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ በቡድንም ይሁን በውስን አውዶች የሚታየውን ሥነ ፅሁፋዊ ጥበብ ለማጥናት ለአጥኚው እገዛ ያደርጋል በማለት ያብራራሉ።

"ክዋኔ ጥበባዊ ድርጊት ነው።" (Deborah A. 1995, 479) "ክዋኔ በተግባር የሚገለፅና ተሳትፎን የሚሻ ተግባር ነው። ተሳታፊዎች እንዳላቸው ልምድና ክሂል ተሳትፎ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣል። ክዋኔ በትክክል እንዲከወን መቼት፣ ተሳታፊ

እና ከዋኝ መገኘት ይኖርባቸዋል።" (Sims and Stephens, 2005, 128-129) በማለት ክዋኔ ጥበብ መሆኑን ከዚያም ባሻገር ክዋኔ ለሁሉም ተሳታፊዎች እንደ አቅማቸውና እንደፍላጎታቸው እንዲሳተፉ እድል እንደሚሰጥ ያስረዳሉ።

የቃል ግጥም ዓይነቶች በርካታ እንደመሆናቸው መጠን አከዋወናቸውም እንደየባህርያቸው የተለያየ ነው። እያንዳንዱ የቃል ግጥም ዓይነት የሚከወንበት የራሱ የሆነ መቼት፣ ታዳሚ እንዲሁም ከዋኝ አለው። ይህንን አስመልክቶ Finnegan እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> …an oral poem is an essentially ephemeral work of art, and has no existence or continuity apart from its performance. The skill and personality of the performer, the nature and reaction of the audience the context, the purpose- these are essential aspects of the artistry and meaning of an oral poem. (1977, 28)

ቃል ግጥም ያለ ክዋኔ ህልውና የለውም፤ ቀጣይነትም አይኖረውም። እንደሳቸው አገላለጽ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከቦታ ወደ ቦታ የመሸጋገር እድሉ ያለው በክዋኔ ላይ ተንጠልጥሎ ነው። ለቃል ግጥም ኪናዊ ውበትና ትርጉም ሰጪነት፣ የከዋኙ ችሎታ፣ የታዳሚው የተሳትፎ ብቃት እና አውዱ ወሳኝነት አላቸው። በአጠቃላይ ለቃል ግጥም መኖር ክዋኔ ወሳኝ ነው በማለት ገልጸዋል።

አንድ የቃል ግጥም ክዋኔ የተሳካ እንዲሆን ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ መቼት /አጋጣሚና አውድ የጠበቀ ቁርኝት ሊኖራቸው ይገባል።

Sims እና Stephens "ክዋኔ በተግባር የሚገለፅ ሥራ ነው። ክዋኔ ተሳታፊዎች እንደ ችሎታቸውና እንደ ልምዳቸው መሳተፍ እንዲችሉ እድል ይፈጥራል። ክዋኔ ዓላማውን እንዲያሳካ ከተፈለገ ክዋኔው የሚከወንበት መቼት፣ ታዳሚዎችና ከዋኞች ሊገኙ ይገባል" (2005፣ 129) ይላሉ።

ክዋኔ እንዲኖር ሰበብ ወይም ምክንያት ያስፈልጋል። ሥነ ቃልም ሆነ ሌላ የፎክሎር ዘርፍ የሚከወነበት ምክንያት ሊኖረው ይገባል Jan Vansina ክዋኔ ሰበብ የሚያስፈልገው መሆኑን ለመግለፅ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> Performances are not produced at random times. The occasions for performances are littered and can be observed in the field. ...

> Each sort of tradition has its appropriate occasions for performance, and that also determines the frequency of performance (1985, 39-40).

ለክዋኔ የተወሰነ ጊዜና ቦታ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የመከወኛ ምክንያትና ወቅትም ያስፈልገዋል። የመከወኛ ምክንያትና ወቅት የክዋኔውን ድግግሞሽ ይወስነዋል። የፎክሎር ተመራማሪ በክዋኔ ወቅት ሊያተኩርባቸው ከሚገባው የክዋኔ አላባውያን መካከል አንዱ ከዋኝ ነው። ከዋኝ የተማረውን ወይም በተሳትፎ ብዛት ያካበተውን ፎክሎራዊ እውቀት ጥበባዊ በሆነ ድርጊት የሚያስተላልፍ ባለሙያ ነው። የቃል ግጥም ከዋኝ፣ የቃል ግጥሙን በመሪነት የሚያቀነቅን ወይም የሚያቀርብ ነው። ቃል ግጥሙ ከቦታ ወደ ቦታ ብሎም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ትልቁን ድርሻ ይጫወታል።

Ruth Finnegan ለስነቃል ኪናዊነት ወሳኙን ቦታ የሚይዘው ከዋኝ መሆኑን ለመግለፅ "Oral literature is by definition dependent on a performer who formulates in words on a specific occasion- there is no other way in which it can be realized as a literary product."(2012, 4) ሲሉ በቃል ግጥም ከዋኙ ማዕከላዊውን ቦታ እንደሚይዝ ያብራራሉ። ለአውዱ የሚሆነውን ሥነ ቃል ከመቀመር አንስቶ ጥበባዊ እሴቱን የሚያስጠብቀው ከዋኙ ነው። እንደ Ruth አገላለፅ በጽሑፍ የተዘጋጁ ድርሰቶች እንኳ በቃል በሚከወኑበት ወቅት ከዋኙ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ የተለያዩ ችሎታ ባላቸው ከዋኞች ቢከወን ለተለያዩ ታዳሚዎች የሚሰጠው ስሜት የተለያየ ይሆናል። መቼቱ፣ የታሪኩ መዋቅርና ገፀባህሪያቱ ተመሳሳይ ቢሆኑም በከዋኙ ችሎታ ምክንያት ልዩነት ሊመጣ ይችላል።

ከዋኞች በሙያው የሰለጠኑ ወይም በልምድ ያገኙት ሊሆኑ ይችላሉ። "performance would be specialists or not, indeed, some persons were specialized in one particular type of tradition…" (Jan Vansina 1985, 36) በሀገራችን ከሚገኙ የቃል ግጥሞች፣ ከዋኞች ሙያውን በሥልጠና ከሚከውኗቸው መካከል ቅኔን መጥቀስ ይቻላል።

በክዋኔ ወቅት የመስክ ተመራማሪ ትኩረት ከሚቸራቸው አላባውያን መካከል ታዳሚያንም ይጠቀሳሉ። ታዲሚያን የቃል ግጥምም ሆነ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት አፍ ተልብ ሆነው የሚከታተሉና የፎክሎሩ ዓይነት በሚፈቅደው

መሠረት ከዋኙን የሚያግዙ እንዲሁም ለክዋኔው መሳካት የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ ናቸው። (Finnegan 1977, 176, 177, Sims እና Stephen 2005, 128-129)

ታዳሚዎች የከዋኙን ብቃትና ክህሎት መሰረት አድርገው ክዋኔውን ይለካሉ፤ ይገመግማሉ። ክዋኔውን ከተረዱት ምላሽ ይሰጣሉ። ታዳሚዎች ክዋኔውን መረዳትና መተርጎም ካልቻሉ ክዋኔው ተሳክቷል ለማለት ያስቸግራል።

### 2.2.3. አውድ

አውድ የክዋኔ ገፅታ ወይም ድባብ ነው። የክዋኔውን መቼት፣ በክዋኔ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሶችን፣ አጠቃላይ የክዋኔውን ሁኔታ እንዲሁም የከዋኙንና የታዳሚውን ግንኙነት የሚያጠቃልል ነው።

Dan Ben Amos የአንድ ፎክሎር ክዋኔ ሲነሳ ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ዐብይ ጉዳይ አውድ መሆኑን ይገልፃሉ። "The meaning of a text is its meaning in context." (1993, 210) የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ /text/ መልእክት ለመረዳት አውድን መረዳት አስፈላጊ ነው። አንድ የፎክሎር አጥኚ የሚያጠናውን ጉዳይ በምልዓት ለመተርጎም የሚችለው አውዱን በሚገባ ሲረዳ ብቻ ነው። የአውዱን አጠቃላይ ድባብ ሳይረዱ የፎክሎሩን መልዕክት ማወቅና መተርጎም ያስቸግራል።

> Increase emphasis on the relevance of context for interpretations (Ben Amos 1972) encouraged scholars of verbal arts to reconceived their subjects of study, moving form an item centered perspective to one that emphasized cultural "enactments" (Abrahams, 1977) and "events" (Bauman, 1977).

ከላይ የቀረበው ጥቅስ Deborah እውቅ የፎክሎር ተመራማሪዎችን እማኝ በመጥቀስ አውድ የብዙዎችን ቀልብ መሳቡንና የምርምር አቅጣጫውን የቀየረ መሆኑን ለማስረዳት የተጠቀሙበት ሃሳብ ነው። አውድ አንድ የማህበረሰብ ቡድን ወይም አባል የቃል ግጥም በሚከውንበት ወቅት የሚፈጠረውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት እንዲሁም ማህበረሰቡ ህዝባዊ ጥበቡን የሚለዋወጥበትና ተራክቦ የሚፈጥርበት ማህበራዊ ሁኔታና ተፈጥሯዊ ቦታ ነው።

እንደ Sims እና Stephen አገላለፅ አውድ ተጨባጭና ማህበራዊ አውድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ተጨባጭ አውድ ሲባል የቃል ግጥም (የፎክሎር ዘርፍ) መቼት (መልክአ ምድራዊና አካባቢያዊ ሁኔታ) የት እንደሆነ፣ በክዋኔው የተገኙ ከዋኝና ታዳሚዎች እነማን እንደሆኑ በክዋኔ ወቅት የከዋኞቹ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የድምፅ ቅላፄ በአጠቃላይ የአካባቢው ድባብን የሚመለከት ነው። (Sims እና Stephen 2005, 128-129)

ማህበራዊ ዐውድ በክዋኔ ወቅት በቡድንም ይሁን በግለሰብ ደረጃ ወይም በአጠቃላይ በባህሉ ውስጥ የሚታየውን አጠቃላይ ድባብ የሚመለከት ነው። በክዋኔው ወቅት የሚንፀባረቀውን የከዋኙንና የታዳሚውን ማህበራዊ ደረጃ፣ ሥራ፣ ፆታ፣ ዘር፣ ቋንቋ ወዘተ ሁሉ ያጠቃልላል። (Finnegan, 1977, 214) Sims እና Stephen 2005, 139-146)

### 2.2.4. የቃል ግጥም ድረሳ

የቃል ግጥም ድረሳ ስንል ከዋኙ ቃል ግጥሞቹን የሚያፈልቅበትን ወይም የሚፈጥርበትን ዘዴ ነው። የቃል ግጥም በተለያየ መንገድ ይደረሳል። የቃል ግጥም በዋናነት በማስታወስ፣ እዚያው በዚያው አጋጣሚውን ተጠቅሞና አውዱን ተከትሎ ወዲያውኑ በመፍጠር እና በተመስጦ ሊደረስ ይችላል። በማስታወስ መከወንን አስመልክተው Finnegan ሲያስረዱ "He is repeating from memory a piece which has been composed prior to the performance, either by himself or, more likely by others, perhaps years or generation earlier" (1977, 52) ይላሉ። ከጥቅሱ እንደምንረዳው የቃል ግጥም ከዋኙ ከክዋኔው እለት በፊት በራሱ የተደረሰ ወይም በሌሎች የተደረሰ ቃል ግጥም አስታውሶ ሊያቀርብ ይችላል። በአብዛኛው በሌሎች የቃል ግጥም ደራሲያን ከአመት ወይም ከትውልድ በፊት የተደረሰውን አስታውሶ ሊከውን ይችላል።

እዚያው በዚያ የአደራረስ ስልት ከሆነ ግን ከዋኙ በወቅቱ የክዋኔው ድባብ በሚያሳድርበት ስሜት ተነሳስቶ ነባሩን ቃል ግጥም ከወቅቱ ጋር እንዲስማማ አድርጎ አዳዲስ ወቅታዊ ሃሳቦችን በመጨመር አሻሽሎ የሚያቀርብበት ነው። ከዋኙ ነባሩን ስነቃል የዜማ አወራረድ ስልት ሳይለውጥ ያንኑ ስልት በመከተል የራሱን አዳዲስ ሃሳቦች በመጨማመር ሊፈጥር ይችላል።

በተመስጦ የአደራረስ ስልት ግን ከዋኙ ነባሩን የቃል ግጥም እንዳለ ሙሉ ለሙሉ ወይም ሽራርፎ ሳይሆን አዲስ ቃል ግጥም የሚፈጥርበት አጋጣሚ ነው። ከዋኙ አውዱ በፈጠረለት አነሳሽ ሁኔታ ተነቃቅቶ የሚፈጥራቸውን ቃል ግጥሞች የሚመለከት ነው (Finnegan 1977, 52-87)

የቃል ግጥም ድረሳ በክዋኔ ወቅት የመደጋገምና የተለዋዋጭነት ባህርያት ይታይበታል። ቃል ግጥም ከክዋኔ ውጭ በሚነገሩ የመደጋገም ባህርይ ቢኖራቸውም ድግግሞሹ ጎልቶ የሚታየው በክዋኔ ወቅት ነው። ድግግሞሹ በቃል፣ በሀረግ፣ በስንኝ እንዲሁም በይዘት ደረጃ ሊሆን ይችላል። የቃል ግጥም ድግግሞሽ ለከዋኙና ለታዳሚው የሚያስገኘው ጠቀሜታዎች አሉት። "ለከዋኙ በራስ የመተማመን ስሜት ይሰጠዋል፤ ለተሳታፊዎች ደግሞ የቃል ግጥሙን መልዕክት በቀላሉ ለመያዝና ከከዋኙ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር ያስችላቸዋል። "(Finnegan 1977፣ 129) ከዋኙ ቀጣዩን ስንኝ ለማስታወስ ፋታ ያገኝበታል። የታዳሚዎችን ትኩረት ለመሳብም ያስችላል። በተጨማሪም "ክዋኔውን ለማርዘም ዋና ዋና ለሆኑ ጉዳዮች አጽንኦት ለመስጠት፣ የግጥሙን መዋቅር ወይም ምት ለማስጠበቅ ይጠቅማል።" ( Okpewho፣ 1992፣ 9)

### 2.2.5.ተስተላልፎ

የቃል ግጥም ህልውና የተመሰረተው በቃል በሚደረግ ተስተላልፎ ነው። ተስተላልፎ ስንል ቃል ግጥሙ ተደርሶ ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ፣ ከትውልድ ትውልድ ከባህል ባህል የሚተላለፍበትን ዘዴ ነው። የቃል ግጥም ተስተላልፎ ቀድሞ የነበረውን በመሸምደድ በክዋኔ ወቅት አስታውሶ በመከወን፣ የራስን አዳዲስ ሃሳቦች እየጨመሩ አሻሽሎ በመከወን ሊሆን ይችላል። ቃል ግጥም ለመከወን የተወሰነ አጋጣሚ መኖር አለበት። የቃል ግጥም የመከወኛ አጋጣሚ ካላገኘ የመኖር ህልውናውን ሊያጣ ወይም ሊጠፋ ይችላል። ከዚህ ነጥብ ጋር በማያያዝ በጽሑፍ የሚገኙ ስነጽሑፎችን ከቃል ግጥም ጋር በማነጻጸር ስንመለከት ተስተላልፏቸው በጽሑፍ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ሳይበረዙና ሳይለወጡ ከመዝለቃቸውም በተጨማሪ በማን፣ ለማን፣ መቼና የት እንደተጻፉ ማወቅ ይቻላል። ቃል ግጥምን ስንመለከት ግን በማን፣ ለማን፣ መቼና የት እንደተደረሱ በትክክል ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል።

የከዋኙ የዜማና የቃል ግጥም አከዋወን እውቀት እንደዚሁም የማስታወስ ችሎታ ለቃል ግጥሙ ተስተላልፎ ወሳኝነት አለው። የቃል ግጥም ከላይ ወደታች በቃል ስለሚተላለፍ በተስተላልፎው መካከል የመዘንጋት ወይም የመረሳት እድል ያጋጥመዋል። በተጨማሪም ከአንድ ከዋኝ የተከወነ ቃል ግጥም በሌላ ከዋኝ በሚከወንበት ወቅት በርካታ ለውጥ ሊኖር ይችላል። "As it passes from singer to singer it is changing unceasingly. Old stanzas are dropped and new ones are added; rhymes are altered; names of the characters are varied…" በማለት (Finnegan፣ 1977፣ 144) ተስተላልፎው በማያቋርጥ ሁኔታ በለውጥ የታጀበ መሆኑን ያስረዳሉ። እንደሳቸው አገላለጽ ነባር ስንኞች በአዲስ ሊተኩ ይችላሉ። በቀድሞዎቹ ስንኞቹ የነበሩ ገጸባህርያት ስሞች በሌሎች ስሞች ሊተኩ ዜማዎቹ ሊቀየሩ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

በባህል፣ በቦታ፣ በዘመን፣ በከዋኙ የግል ችሎታ እና በመከወኛ አጋጣሚዎች ምክንያት የቃል ግጥም ለውጥ ይከሰታል። Finnegan " በቃላዊ ግጥም ተስተላልፎ በቃል ፣ በሐረግ፣ በስንኝ፣ በዋና ሐሳብና በማባያ ጉዳይ ላይ ለውጦች ይከሰታሉ።" በማለት ያስረዳሉ። (1977፣135) ከዚሁ ጋር በማያያዝ ለውጡ አንዳንድ ጊዜ የቃል ግጥሙን ጭብጥ እስከማሳት ድረስ ሊዘልቅ እንደሚችል ይገልጻሉ። የቃል ግጥሞች ይዘት በፖለቲካና በማህበራዊ፣ በዘመንና በቦታ እንዲሁም በእድገት ወይም በብልጽግና በመሳሰሉት ለውጦች ምክንያት ሊለዋወጡ ይችላሉ።

### 2.2.6. የቃል ግጥም ፋይዳ

የቃል ግጥም ፋይዳ ሲባል የሚከወኑት የቃል ግጥሞች ለስነቃሉ ባለቤቶች ያላቸውን ጠቀሜታ ይመለከታል። የተለያዩ የቃል ግጥም ዓይነቶች ለየራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ወይም ተግባር ያላቸው ቢሆንም እነዚሁ የተለያዩ ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ጠቀሜታ ሊኖራቸው ይችላል። በሌላ በኩል በቅርጽ የተለያዩ ቃል ግጥሞች ተመሳሳይ ተግባር ሊኖራቸው ይችላል። ፈቃደ አዘዘ "የሠራተኞችን ጥረት ለማስተባበር እና የሥራውን አሰልችነት ለማለዘብ የሚዘመር የሥራ ግጥም (ለምሳሌ "ሆ በሬ!") በሌላ ሁኔታ ለመዝሙርነቱ ብቻ ለጨዋታ ያህል ሊከወን ይችላል።" (1991፣ 17) በማለት የተለያዩ የቃል ግጥም ዓይነቶች ተመሳሳይ ተግባር ሊኖራቸው እንደሚችል ያስረዳሉ።

በክብረበዓላት የሚከወኑ ቃል ግጥሞች መንፈሳዊ ወይም ዓለማዊ ይዘት ሊኖራቸው ይችላል። አንዳንዶቹ ክብረበዓሉን አስመልክተው የሚቀርቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በይዘታቸው ክብረበዓሉን የማይመለከቱ አለማዊ ናቸው።

ክብረ በዓሉን የሚመለከቱ ቃል ግጥሞች በዓሉን ለማወደስ ለማመስገንና ለማክበር ያገለግላሉ። አለማዊ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ደግሞ የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ አመለካከቱንና ስሜቱን ለመግለጽ የሚያገለግሉ ናቸው።

የቃል ግጥም ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚያበረክተው በርካታ ተግባራት አሉት። ቃል ግጥም መረጃን ከትውልድ ወደ ትውልድ ያቀብላል። ባህልና ወግን ጠብቆ ለማቆየት ያገለግላል። ሥነምግባርን ለማስተማር፣ ከአስቸጋሪ ሁኔታ ለማምለጫነት ጥቅም ላይ ይውላል። ስንፍናን በመንቀፍ የደከመን በማበረታታት ሥራን ያለመሰልቸት ለመሥራት ያስችላል። በአጠቃላይ ቃል ግጥም ተቆጥሮ የማያልቅ በርካታ ጥቅሞች አሉት። (Finnegan, 1977, 3-7, 1970, 273 )

በመሆኑም እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን የቃል ግጥም ንድፈ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ ከደላንታ ወረዳ የተሰበሰቡት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ድረሳ፣ ተስተላልፎ፣ ክዋኔ፣ አውድና ፋይዳ ምን እንደሚመስሉ በምዕራፍ አራት ቀርበዋል። ከዚያ በፊት ግን ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ መልክአ ምድራዊ ገጽታ እንዲሁም ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች በቀጣዩ ምዕራፍ ቀርቧል።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ መልክአ ምድራዊ ገጽታ፣ ኢኮኖሚያዊ መሠረቶችና ባህላዊ ሁኔታዎች ተዳሰዋል።

### 3.1. መልክአምድራዊ አቀማመጥ

የደላንታ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ነው። ወረዳው እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ በሰሜን ወሎ ዞን ሥር የነበረ ሲሆን ከ2003 ዓ.ም የበጀት ዓመት ጀምሮ በደቡብ ወሎ ዞን ሥር ተከልሏል። ከወረዳው ባህልና ማስታወቂያ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ወረዳው በ$38^0$ 40' ሰሜን እና $11^0$ 20' ምሥራቅ የሀሳብ መሥመሮች ይገኛል። ደላንታ ወረዳ በሰሜን ከዋድላ እና ከጉባላፍቶ ወረዳዎች በምዕራብ ከዳውንት ወረዳ በደቡብ ከተንታ ወረዳ በምሥራቅ ከአምባሰል ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል።(2001፣3)

ከወረዳው ንግድና ትራንስፖርት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው (2006፣ 1) የደላንታ ወረዳ 106,017 ሄክታር መሬት ስፋት ያለው ሲሆን 30% ሜዳማ 36.5% ወጣ ገባ 30% ገደላማ እና 3.5% ተራራማ የመልክአ ምድር ስብጥር አለው። (ሰሜናዊው ክፍል ገደላማ ሲሆን ምዕራቡ ክፍል ደግሞ ሜዳማ ነው።) የደላንታ ምድር ከባህር ጠለል በላይ ከ2,100 እስከ 3,800 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን 26.4% ደጋማ 41.3% ወይና ደጋ 28.5% ቆላማ እና 3.8% ውርጫማ የአየር ጠባይ አለው።

ከወረዳው ነዋሪ መካከል 86 በመቶ የሚሆነው በገጠር ሲሆን ቀሪው ወደ 14 በመቶ የሚጠጋው የከተማ ነዋሪ ነው። ከወረዳው ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ በተገኘ መረጃ መሰረት የወረዳው ህዝብ ብዛት 157,233 (ወንድ 71,080 ሴት 86,153) ሲሆን የነዋሪው ስብጥር በገጠር 135,588 በከተማ 21,645 ህዝብ እንደሆነ ተገልጿል።

### 3.2. ኢኮኖሚያዊ ገፅታ

ከወረዳው ባህልና ማስታወቂያ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የወረዳው ኢኮኖሚ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 97% የሚሆነው በግብርና ላይ የተመሠረተ ሲሆን

በተለይ በእንስሳት የሚገኘው ገቢ የአርሶ አደሩን 45% አመታዊ ገቢ ይሸፍናል። በተጨማሪም በወረዳው ገብስ፣ ባቄላ፣ ምስር፣ ስንዴ፣ ሽምብራ፣ ጤፍና አብሽ በብዛት የሚመረቱ ሰብሎች ናቸው። (2001፣3) ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "ኦፓል" የተሰኘ የከበረ ማዕድን በመገኘቱ በርካታ ወጣቶች ማዕድኑን ከመሬት ውስጥ በማውጣት ተጨማሪ ገቢ በማግኘት ላይ ይገኛሉ።

በደላንታ ወረዳ ከሚኖረው ህዝብ መካከል 8,979 ሙስሊሞች ሲሆኑ ቀሪው ህዝብ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚቻልበት ደረጃ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው። በወረዳው 130 የኦርቶዶክስ እምነት ቤተክርስቲያኖች እና አንድ መስጊድ የሚገኙ ሲሆን ሌሎች የሀይማኖት ተቋማት የሉም። በወረዳዋ 99.9% የሚሆኑት ነዋሪዎች የአማራ ብሔር ተወላጆች ናቸው።

## 3.3. ማህበራዊና ባህላዊ ገፅታዎች

ከደላንታ ወረዳ ባህልና ማስታወቂያ የተገኘው መረጃ እንደሚገልጸው፣ "የወረዳው ህዝብ በብዙ የአማራ ክልል ደጋማ ቦታዎች የሚታየው የደገኛ ክርስቲያን ባህል አለው።" (2001፣ 3) እንደ አብዛኛው የወሎ ወረዳዎች የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች ስብጥር የሚታይበት ሳይሆን እንደ አብዛኛው የደቡብ ጎንደር ወረዳዎች የክርስቲያን ባህል ያለው አካባቢ ነው። አካባቢው ለአገሪቱ ሰሜን መካከለኛው የደጋ ምድር እና ለሰሜን ምሥራቁ የቆላ መሬት ጠርዝ በመሆኑ የባህሎች መሸጋገሪያ ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ መረጃው ይገልጻል።

ስለ ደላንታ ወረዳ ስያሜ በአካባቢው የሀይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች የተለያዩ ግምቶች ይሰነዘራሉ። ከሚነገሩ ግምቶች መካከል አንዱ ከግራኝ መሐመድ ጦርነት ጋር የተያያዘ ታሪክ ያለው ነው። ግራኝ መሐመድ ከደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ጦሩን ከትቶ የሰሜን ኢትዮጵያን ክፍል በወረረበት ወቅት የአሁኑ ደላንታ ወረዳ በበጌምድር ግዛት ሥር በላስታ አውራጃ የሚጠቃለል ነበር። ግራኝ መሐመድ ዙሪያቸውን በገደል የተከበቡትን የዋድላና የደላንታ ሜዳማ ቦታዎች በቀላሉ መቆጣጠር አልቻለም። መጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ ከዚህ ታሪክ ጋር አያይዘው የሚከተለውን መረጃ ሰጥተውኛል።

> የዋድላና ደላንታ ህዝብ በየገደሉ አፋፍ ዙሪያውን ናዳ በማጥመድ ግራኝ መሐመድ ወደ ሜዳማው የክርስቲያን አገር መዝለቅና መቆጣጠር ይቸገራል። ግራኝም ለፈጣሪው 'ይህን አገር እንዳሸንፍ ከረዳኸኝ ስለት አስገባለሁ' ለማለት በራሱ ቋንቋ 'ዋድ ላንተ አስገባለሁ' ብሎ ይናገራል። ይህንን የሰሙ ሰዎች ግራኝ ከተናገረው ቃል በመነሳት አካባቢውን ዋድላ ደላንታ ብለው ሰየሙት ከዚያ በኋላ ሰሜናዊው ክፍል ዋድላ ሲባል ደቡባዊው ክፍል ደላንታ በመባል እሰከአሁን ስያሜው ጸንቷል። (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 22 ቀን፣ 2006 ዓ.ም)

ስለ ደላንታ ወረዳ ስያሜ የት መጣነት ሁለተኛው አስተያየት የተገኘው ከወረዳው ንግድና ኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ነው። የጽሑፍ መረጃው የአካባቢው ታዋቂ የአገር ሽማግሌ የሆኑትን ሻምበል ሀይለ ልዑል ማስረሻን በመጥቀስ የሚከተለውን አስፍሯል።

> ደላንታ የሚለው ቃል የመጣው አካባቢውን መጀመሪያ ያቀናው አበጋዝ ወይም ባላባት ስም እንደሆነ ይገልጻሉ። ለአባባላቸውም እንደማስረጃ የሚያቀርቡት በአጎራባቿ ዋድላ ወረዳ ውስጥ 'ዘረ ዋድላ' የምትባል ቀበሌ ያለችና ስያሜዋም ዋድላ ለሚባለው ባላባት ዝርያዎች በመኖሪያነት ተመርጣ የነበረች መሆኗን ነው (የደላንታ ወረዳ ንግድ መመሪያ፣ 2001፣3)

**አለባበስ** ፦ በደላንታ ወረዳ በገጠር አካባቢዎች እናቶች በአብዛኛው ከፈትል የተሠራ ቀሚስና ነጠላ ይለብሳሉ። አልፎ አልፎ የፋብሪካ ውጤት ከሆነ ጨርቅ የተሰፋ ቀሚስ ይለብሳሉ። እናቶች ቀሚሳቸውን በመቀነት ታጥቀው ከላይ ነጠላ ይደርባሉ። ቀሚሱ በጥልፍ የሚንቆጠቆጥ ሲሆን ነጠላው ወይም ኩታው ጫፉ ላይ ጥለት ይኖረዋል። ወጣት ሴቶች የፋብሪካ ውጤት የሆነ ጨርቅ አሰፍተው ይለብሳሉ። ያገቡ ሴቶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ መቀነት መታጠቅና ነጠላ መደረብ ባህሉ ያስገድዳቸዋል። ያላገቡ ልጃገረዶች ግን የፋብሪካ ውጤት የሆነ ቀሚስ ለብሰው የቱታ ጃኬት ወይም ከክር የተሰራ ሹራብ ይደርባሉ እንጂ ነጠላ አይለብሱም። ሹራብ መደረቡ መቼ እንደተጀመረ መረጃ ባላገኝም በቅርብ ዓመታት እየተዘወተረ የመጣ አለባበስ ነው።

አባቶች ኮትና ቦላሌ ለብሰው ከላይ ጋቢ ወይም ኩታ ይደርባሉ። ወጣት ወንዶች ደግሞ የግብርና ሥራ ላይ (እርሻ፣ አረም አጨዳ) ካልተሰማሩ በስተቀር እንደማንኛውም የከተማ ወጣት ቦላሌ ሱሪና ሸሚዝ ይለብሳሉ። በሥራ ቀን ከሆነ ግን ቁምጣ ይለብሳሉ።

ከአለባበስ ጋር ተያይዞ በበዓላት ቀናት ሴቶች ዓይናቸውን ኩል በመኳልና እጅና እግራቸውን እንሶስላ በመሞቅ ያጌጣሉ። ቀደም ባለው ጊዜ ሴቶች ለአንገታቸው ድሪ፣

ለእጃቸው ድኮት (አምባር) ለእግራቸው አልቦ የሚባሉ ጌጣጌጦችን ይጠቀሙ ነበር። አሁን አሁን ግን ከአምባር በስተቀር እነዚህ ጌጦች በወጣት ሴቶች እምብዛም ጥቅም ላይ ሲውሉ አይታዩም።




**የሴቶች አለባበስ በገጠር ቀበሌዎች**

በደላንታ ወረዳ የገጠር አካባቢዎች ከነባሩ ባህል እየተለወጠ የሚገኘው አንዱ የሴቶች የፀጉር አሰራር ነው። ቀደም ሲል ያላገቡ ሴቶች መለያ የሆነ የፀጉር አሰራር ዓይነት ነበር። ልጃገረዶች ከላይ መሃሉንና ከታች ዙሪያውን በማስቀረት ይላጩና ያልተላጨውን ክፍል ይሰሩታል። ባል ካገቡ በኋላ ግን ሙሉውን ፀጉር በማሳደግ ሹሩባ ይሰራሉ። ከቤተሰብ ወይም ከዘመድ መካከል አንድ ሰው በሞት ከተለየ እናቶች ፀጉራቸውን ይላጫሉ።

***ጋብቻ፡-*** *ጋብቻን በሚመለከት በገጠር አካባቢዎች የወጣቶች ትዳር የሚመሰረተው በወላጆች ምርጫ ነው። ወረዳው ቀደም ሲል ያለዕድሜ ጋብቻ በብዛት ከሚፈፀምባቸው አካባቢዎች አንዱ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን የሚተጫጩ ወጣቶች በአካባቢው የቀበሌ አስተዳደርና በጤና ባለሙያዎች ለትዳር ብቁ መሆናቸው ካልተመሰከረላቸው በስተቀር መጋባት አይችሉም። ተጋቢዎች ከዕድሜ በተጨማሪ የኤች አይ ቪ ምርመራ ማድረግም ይጠበቅባቸዋል።*

# ምዕራፍ አራት

## 4. የደላንታ ወረዳ ሴቶች የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ አከዋወንና ተስተላልፎ

በዚህ ክፍል የደላንታ ወረዳ ሴቶች የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ፣ አከዋወንና ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያሸጋግሩበት ስልት ወይም ተስተላልፎ ይገለፃል። ከዚያ በፊት ግን የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ምንነትና አመጣጥ እንዲሁም ሴቶች የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች በምን ዓይነት ሥልት እንደሚከውኑ ይቀርባል።

አበሹቴና ኧኸይቦሌ የተሰኙት ቃላት በቀድሞዎቹሙ ሆነ በአንፃራዊነት በቅርብ ጊዜ የታተሙ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ አይገኙም። የቃላቱ ትርጉም በትክክል ማወቅ የሚያስችል መረጃም አልተገኘም። እንደ መጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ ገለፃ "አበሹቴ እና ኧኸይቦሌ የአማርኛ ቃላት አይደሉም። ጨዋታዎቹ ከኢየሱስ ክርስቶስ መያዝ፣ መደበደብ፣ ህማም ጋር የተያያዘ ሀይማኖታዊ መሠረት አላቸው።" በማለት ያስረዳሉ።



ከመጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ ጋር ቃለ መጠይቅ ሲደረግ

አያይዘውም መጋቢ አዕላፍ ደረጀ "ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ አይሁዳውያን እየተጫወቱበትና እየዘበቱበት የነበረበትን ሰዓት ለማስታወስ ወይም ለመዘከር የሚደረግ ከሃይማኖቱ ጎን ለጎን የመጣ ነው" በማለት ያብራራሉ። (ጥር፣ 22 ቀን 2006 ዓ.ም)

ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዩ የተባሉት መረጃ ሰጪም የመጋቢ አአዕላፍ ደረጀን ከመጠየቁ በፊት ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ የመጋቢን አባባል በሚደግፍ አገላለጽ የጨዋታውን ጥንተ መነሻና አከዋወን እንደሚከተለው ይገልፃሉ። "ቀደም ባለው ጊዜ በጃንሆይ ዘመን በኋላም በደርግ ዘመን አበሹቴና ኾኽይቦሌ ጨዋታዎች በፋሲካ ጊዜ ብቻ የሚደረጉ ነበሩ" በማለት ከኢየሱስ መያዝ ጋር የተያያዘ ሃይማኖታዊ መሠረት እንዳለው ከገለፃቸው እንረዳለን። ወ/ሮ ውርጫለቁ ገለፃቸውን በመቀጠል ከትንሳኤ በዓል ውጪ ባሉ ክብረ በዓላት መጫወት ከተጀመረ ከአርባ አመት ያለፈ ዕድሜ የለውም ብለዋል።

በፋሲካ በዓል ወንዶች የኢየሱስ በጦር መወጋትና መደብደብ ለመዘከር ጊጤ የሚባል የጦር ውርወራ ውድድር ሲጫወቱ (የቆመ የእሬት ወይም የእንዶድ ግንድን በጦር የመውጋት ውድድር ሲያደርጉ) ሴቶች ደግሞ ኾኽይቦሌና አበሹቴ እንደሚጫወቱ ወ/ሮ ውርጫለቁ ገልፀውልኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006ዓ.ም)

በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ክፍል የቃል ግጥሞች የሚከወኑበት ምክንያትና ወቅት እንዳላቸው መገለጹ ይታወሳል። የአበሹቴና የኾኽይቦሌ ቃል ግጥሞች ይዘታቸው ዓለማዊ ቢሆንም የመከወን ምክንያታቸው ወይም መነሻቸው ግን ከላይ እንደተገለፀው ሃይማኖታዊ መሠረት እንደሆነ መደምደም ይቻላል።

## 4.1. የቃል ግጥሞች አደራረስ

### 4.1.1. የኾኽይቦሌ ቃል ግጥሞች አደራረስ

የኾኽይቦሌ ቃል ግጥም አደራረስ በምዕራፍ ሁለት ከተገለፀው የቃል ግጥም አደራረስ ጋር የሚሰምር ነው፤ ተመሣሣይነት አለው። ሴቶቹ የኾኽይቦሌ ቃል ግጥሞችን በቃል አጥንተው በመሸምደድ፣ ቀደም ሲል የሰሙትን በማስታወስ እንዲሁም በክዋኔ ወቅት እዚያው በዚያው በመፍጠር ይከውናሉ።

በመስክ ቆይታዬ ከሰበሰብኳቸው የኾኽይቦሌ የቃል ግጥሞች አብዛኞቹ በሸምደዳ የተገኙ ሲሆኑ ቃል ግጥሞቹ ለአውዱ እንዲመቹ ተደርገው የሚቀርቡ ናቸው። ሴቶቹ

ዓውዱን መሠረት አድርገው የቃልና የሐረግ ለውጥ በማድረግ ከሁኔታው ጋር በማስማማት ያዜማሉ። የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች በአብዛኛው ሴቶች እርስ በርሳቸው የሚሞጋገሱባቸው በመሆናቸው የአበሹቴን ያህል ፈጠራ አይታባቸውም። በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት ሴቶቹ ያሞገሷቸውን ሴቶች መልሶ ለማሞገስ ከሚያደርጉት ጥረት ውጪ ለፈጠራ የሚያነቃቃቸው ለፉክክር የሚያነሳሳ ለየት ያለ ነገር የለም። በመሆኑም በሁሉም ቦታዎች ተደጋጋሚ ግጥሞችን መስማት የተለመደ ነው። ቀጥሎ የቀረቡት ግጥሞች ይህን ሃሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው። ለምሳሌ ቄጻ/ወገላት ጥር ስላሴ በሚከበርበት ቀን ንግስቴ አከለ የጥር ስላሴ አዚማዋለች።

ቃል ግጥም፣ 1 ዓለም አዳነ የሎሚ ዛፍ፣
አንቺን ያገባ ይበል ዘራፍ።
(ንግስቴ አከለ ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም)

ይህንኑ ግጥም ጥር 18 ቀን 2006 ዓ.ም ጠቅላዲ በተባለው ቀበሌ ዓለም ታረቀኝ የተባለችው ወጣት ጓደኛዋን ለማሞገስ ተጠቅማበታለች።

ቃል ግጥም፣ 2 አታላይ የማነ የሎሚ ዛፍ
አንቺን ያገባ ይበል ዘራፍ።

የኧኸይቦሌ ግጥሞቹ ከላይ እንደተገለፀው አብዛኛዎቹ በሽምደዳ የሚቀርቡ ናቸው። በሰባቱም ክብረ በዓላት ላይ የተዜሙት ወይም የተከወኑት ቃል ግጥሞች ተመሣሣይነት አላቸው። አዲስ ፈጠራ እምብዛም አይታይባቸውም። ሴቶቹ ቃል ግጥሞቹን የሚሸመድዱት ወይም አስታውሰው የሚከውኑት በየበዓላቱ በመገኘትና በተደጋጋሚ በመስማት ነው። በኧኸይቦሌ ጨዋታ ውስጥ የሥርግ፣የወንዶች ሆታ እና የአበባዮሽ ሆይ ቃል ግጥሞችን መስማት የተለመደ ነው። ለአውድ አስማምተው ይጫወቷቸዋል።

### 4.1.2. የአበሹቴ ቃል ግጥሞች አደራረስ

የአበሹቴ ቃል ግጥሞች አደራረስ ከላይ ከተገለጸው የኧኸይቦሌ ግጥሞች አደራረስ ጋር ተመሣሣይነት ቢኖረውም ልዩነትም አለው። በቃል አጥንቶ በመሸምደድ፣ ቀደም ሲል የሰሙትን በማስታወስ ከኧኸይቦሌ ጋር ተመሣሣይ ሲሆን በክዋኔ ወቅት እዚያው በዚያው የመፍጠር ድርጊቱ ከኧኸይቦሌ ጨዋታ የተሻለ ነው። ምክንያቱም በአበሹቴ

ጨዋታ ሴቶቹ በሁለት ቡድን ተከፋፍለው በተወሰነ ደረጃ የሚሞጋገሱና በአብዛኛው የሚሰዳደቡ በመሆኑ ምላሹን ወዲያውኑ ለመስጠት ቃል ግጥሞቻቸውን ከአውዱ ጋር አስማምቶ ለመፍጠር ይነቃቃሉ። ምልልሱ ወንዶች በገና ጨዋታ ከሚከውኑት የቃል ግጥም ክዋኔ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የሚከተሉትን ቃል ግጥሞች አደራረስ ለአብነት መመልከት ይቻላል።

አይቻልም ሲሉት ይቻላል መከራ፣
ወገላት አደርኩኝ ከቁንጫው ጋራ፡፡
(ብርዘገን ዘገየ፣ ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም)

ይህ ቃል ግጥም መረጃ አቀባዬ ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ እንደነገሩኝ ወገላት ከተሰኘው ቀበሌ ለእንግድነት በመጣች አንድ ሴት በአበሹቴ ጨዋታ ወቅት የተገጠመ ነው። ግጥሙን የገጠመችው ሴት የስላሴ በዓልን አስታካ ብትመጣም ዋና ዓላማዋ ወ/ሮ ብርዘገን በስም የጠቀሱልኝን ወንድ በውሽምነት ይዛ ስለነበር እግረ መንገዷን ከእሱ ጋር ለማደር ነበር። ይሁን እንጂ የሰውየው ሚስት ተጠራጥራ ስለነበር ባሏ ሴትዮዋ ወደ አረፈችበት በቅርብ ርቀት ወደሚገኙት ጎረቤቶቿ እንዳይሄድ አስጠንቅቃው በአይነ ቁራኛ ስትከታተለው ስላመሸች ውሽማው ጋር ሳይገናኙ አደሩ። በማግስቱ የአበሹቴ ጨዋታ ሲከወን ሴትዮዋ ያሰበችው እንዳልተሣካላትና ብቻዋን በማደሯ እንቅልፍ ሳይወስዳት ከቁንጫ ጋር ስትታገል እንዳደረች ብሶቷን ከላይ በተጠቀሰው ግጥም ትገልፃለች ሁኔታው የገባት የሰውየው ሚስት ደግሞ ወዲያውኑ የሚከተለውን መልስ ሰጥታታለች።

ባናውቅ ነው እንጂ ቸርነትሽን፣
መች ታድሪ ነበር ወገላት ብቻሽን።
(ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ፣ ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም)

በማለት ስለ ሴትዮዋ ቸርነት ያላወቀች ያልሰማች በመሆኗ እንጂ ሰው ይፈለግልሽ ነበር በሚል ሽሙጥ ወዲያውኑ ፈጥራ አቀንቅናለች። የግጥሙ ፈጣሪ "ቸርነትሽን አላወቅንም እንጂ "ስትል ቸርነት የሚለው ቃል ሸርሙጣ መሆንሽን አላወቅንም ለማለት የተጠቀመችበት አባባል ነው። መጀመሪያ በእንግድነት የመጣችው ሴት ብሶቷን ለመግለጽ አስባና አሰላስላ ለፈጠረችው የቃል ግጥም ሁለተኛዋ ሴት እዚያው በዚያው በመፍጠር ምላሿን ሰጥታለች።

በሌላ በኩል ወይዘሮ ውርጫለቁ ባዬ የአበሹቴ ቃል ግጥሞችን አደራረስ አስመልክተው "ልጆች ሆነን ታላላቆቻችን ሲጫወቱ በመስማት የሰማነውን መልሰን እንጫወተዋለን። አንዳንድ ጊዜ አዲስ ግጥም የሚገጥሙ ሴቶችም አሉ።" በማለት የሚከተለውን ግጥም አዚመውልኛል።

አንቺ የኔ ጐባን መሃለኛይቱ፣
ማዞሪያ ስሪልኝ ከነመግላሊቱ።
(ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም)

ከላይ የቀረበው ግጥም ሁለት ጣውንቶች በተቃራኒ ቡድን ሲጫወቱ አንዱ ሌላዋን ለመስደብ የገጠመችው የአበሹቴ ግጥም ነው። ገጣሚዋ ጣውንቷን ሸክላ ሰሪ መሆኗን ለመግለጽ ተጠቅማበታለች። "በወቅቱ በአካባቢው ሸክላ ሰሪ የሆኑ ባለሙያዎች የሚናቁ በመሆኑ ጣውንቷን 'የተናቅሽ ነሽ' ለማለት በማሰብ የተገጠመ ነው።" ( ውርጫለቁ ባዬ በቃለመጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም )
ግጥሙ የሚመለከታት ሴትም እዚያው በዚያው ግጥም በመፍጠር መልሱን ሰጥታለች።

ማዞሪያ ብሰራ ከነመግላሊቱ፣
መች ትከድኚዋለሽ አንቺ መንጋላይቱ።

እዚያው በፈጠረችው ግጥም "ማዞሪያውን ከነመግላሊቱ ወይም ከነክዳኑ ልሰራልሽ እችላለሁ። ነገር ግን አንቺ ጅላጅል ስለሆንሽ በአግባቡ አትጠቀሚበትም፣ ማዞሪያውን ከፍተሽ የዝንብ መጫወቻ ታደርጊዋለሽ" በማለት ፈጠራዋን ተጠቅማ መልስ ሰጥታታለች። (ውርጫለቁ ባዬ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም)

ባልንጀራ ብዬ ልቤ እያመናት ፣
አታሎ ነዳፊ ቀጭን ፈታይ ናት።
(ካሣይቱ እውነቱ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 20 ቀን 2006 ዓ.ም)

ግጥሙ የሚመለከታት ሴት ደግሞ አቀንቃኟ እያመሰገነቻት ሳይሆን እየሰደበቻት መሆኑ እንደገባት ለመግለጽ፣

ሰደበችኝ አሉ ምን ብላ ምን ብላ?
አታሎ ነዳፊ ቀጭን ፈታይ ብላ።

በማለት ቀጭን ፈታይ ነሽ የሚለው ሀረግ አታሎ ነዳፊ በሚለው ቅኔያዊ ስድብ መታጀቡ ለነገር መሆኑ እንደገባት በመግለጽ ወዲያውኑ መልስ ሰጥታለች። በተጨማሪም የተሰዳቢዋ ጓደኛ የግጥሙን አውድ ተከትላ ለጓደኛዋ ያላትን ድጋፍ በሚከተለው ቃል ግጥም ገልፃለች።

አታሎ መንደፍስ የሴት ወጉ ነው፣
ቀጭን መፍተል እንኳ የሴት ወጉ ነው፣
እሷ የምታውቀው ገንፎ በገል ነው።

በዚህ ቃል ግጥም የጓደኛዋ መሰደብ የቆጫት ሴት ጓደኛዋን በመደገፍ "ጥጥ መንደፍም ሆነ ቀጭን መፍተል ባህላችን ነው። እሷ ወይም ተሳዳቢዋ ግን አንቺን ለመስደብ ብቃቱ የላትም። የእሷ ችሎታ ገንፎ በሰባራ ሸክላ ማገንፋት ብቻ ነው ።" በማለት ወዲያውኑ እዚያው በዚያው መልስ ለመስጠት ፈጠራዋን ተጠቅማለች።

ከላይ እንደተገለፀው የደላንታ ሴቶች የአበሹቴ ቃል ግጥሞችን በየበዓላቱ በመስማት ሸምድደው እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት ፈጠራ ተጠቅመው እዚያው በአውዱ ላይ በመፍጠር ይከውናሉ። ቃል ግጥሞቹን ሸምድደውም ይሁን ፈጥረው ሲያቀርቡ ነባር የግጥሙን አወራረድና የዜማውን አሰባበር ሳይለቁ የቃል፣ የሀረግና የስንኝ ለውጥ አድርገው እንደሚከውኑም በመስክ ምልከታዬ አስተውያለሁ።

በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣
አረገዝኩኝ አለች ቀፈቷን ብታይ።

በላች በላችና ዱባና ድንች፣
አረገዝኩኝ አለች አሯ ቢከማች።

በላች በላችና ገብሱን ከነአሰሩ፣
አረገዝኩኝ አለች ቀለቤን ስፈሩ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሶስቱም መንቶ ግጥሞች በአራቱም ቀበሌዎች የአበሹቴ ጨዋታ ወቅት ከዋኞቹ አዚመዋቸዋል። በቡድን ውይይት ወቅትም በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ ግጥሞች እንደሚዜሙ ተረጋግጧል። ሶስቱም ቃል ግጥሞች በይዘታቸው ተመሣሣይነት

አላቸው። በቃል ግጥሞቹ ላይ የሚታየው ለውጥ የየስንኞቹ ሁለተኛ ሐረግ ላይ ነው። በመጀመሪያው ግጥም ሁለተኛ ሐረግ "የወጡን ላይ ላይ" በሁለተኛው ቃል ግጥም ሁለተኛው ሐረግ "ዱባና ድንች" በሶስተኛው ግጥም ሁለተኛው ሐረግ "ገብሱን ከነአሰሩ" በመብላቷ ምክንያት የሆዷ ቦርጭ በመጨመሩ ሴትየዋ "እርጉዝ ነኝ" አለች የሚል መልዕክት ያስተላልፉሉ።

በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣[1]
ፈነጠቀችበት ከመኝታው ላይ።

በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣ [2]
ፈነጠቀችበት ከቆለጡ ላይ።

ከላይ የቀረቡት ሁለቱ መንቶ ቃል ግጥሞች መጀመሪያ ከቀረቡት ሶስት መንቶ ቃል ግጥሞች የስንኝ ለውጥ አድርገው ይታያሉ። ሁለተኛው ስንኛቸው ከቀድሞዎቹ ሙሉ ለሙሉ በመለወጡ የይዘት ለውጥም ተከስቷል። "ፈነጠቀችበት ከመኝታው ላይ" እና "ፈነጠቀችበት ከቆለጡ ላይ" የሚሉት ስንኞች ከመጠን በላይ ከመብላቷ የተነሣ ሠገራዋን መቆጣጠር አልቻለችም የሚል ይዘት አላቸው።

የላይኛዎቹ ሦስት ቃል ግጥሞች ብዙ መብላት ቦርጫም ያደርጋል የሚል ሃሣብ ያዘሉ ሲሆን ሁለተኛዎቹ ደግሞ ሆዳምነት ከቁጥጥር ውጭ ያደርጋል በማለት በልክ መመገብን የሚመክሩ ቃል ግጥሞች ናቸው። በሌላ በኩል እነዚህ አንድ ላይ የቀረቡት ግጥሞች የይዘት ለውጥ ባይኖራቸውም በመካከላቸው የቃላት ለውጥ አድርገው ይታያሉ።

በአጠቃላይ ሙሉውን ወይም በከፊል ለውጠው በመሸምደም ወይም በአዲስ መፍጠር በቃል በሀረግ ወይም በስንኝ ለውጥ በማድረግ ከክዋኔው አውድ ጋር አስማምተው ያዜማሉ። በመቀጠል የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔን እንመለከታለን።

## 4.2. የኽኸይቦሌ የአበሹቴ የቃል ግጥሞች አከዋወን

በምዕራፍ ሁለት አንድ ፎክሎር ለመከወን ምክንያት እንደሚያስፈልገው እንደተገለጸው ሁሉ የደላንታ ወረዳ ሴቶችም የአበሹቴና የኽኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን ለመከወን የሚጠቀሙባቸው አጋጣሚዎች አሏቸው። ሥጦታዬ አስማሜ የተባሉ መረጃ ሰጪ

"የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች የሚከወኑት በገና፣ በጥምቀት እና በፋሲካ እንዲሁም የታቦት ንግስ በሚደረግበት የክብረ በዓላት ወቅት ነው" በማለት ጨዋታዎቹ የሚከወኑበትን አጋጣሚዎች ገልጸዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 4 ቀን 2006ዓ.ም)

ጥናቱ በተካሄደባቸው አራት ቀበሌዎች በተደረገው ምልከታ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃላዊ ግጥሞች የተከወኑት ታቦታት በሚነግሱበት ዕለታት ታቦትቱ ወደየመንበራቸው ከገቡ በኋላ ከቤተክርስቲያን ግቢ ውጭ በሚገኙ ደልዳላ ቦታዎች ላይ ነው። በፋሲካና በገና ወቅት ግን ታቦት ስለማይወጣ በየመንደሩ በሚገኙ ደልዳላ ቦታዎች ጨዋታዎቹ ተከውነዋል። ጨዋታዎቹ ከቤተክርስቲያን ግቢ ውጪ ለምን እንደሚከወኑ መጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ "የጨዋታዎቹ ውስጠ ይዘት ዓለማዊ በመሆናቸው ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲከወኑ አይፈቀድም" በማለት ገልጸዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 22 ቀን 2006 ዓ.ም)

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ክዋኔ ቅደም ተከተል አላቸው። በታቦት ንግስ ወቅት ታቦቱ ከገባ በኋላ የዘፈኑ መድረክ በወንዶች ሲተካ ሴቶች ከቤተክርስቲያን ግቢ ውጪ በሚገኝ ደልዳላ ቦታ በመሄድ በቅድሚያ ኧኸይቦሌ በመቀጠል አበሹቴ ቃል ግጥሞችን ይከወናሉ። በገናና በፋሲካ በዓላት ግን ዘፈን አይኖርም፣ ቀጥታ ወደ ሁለቱ ጨዋታዎች ይገባሉ። በገና በዓል ወንዶች ከመንደር ራቅ ብለው የገና ጨዋታ ሲከውኑ ሴቶች ደግሞ መንደራቸው አካባቢ የቃል ግጥሞቹን ይከውናሉ።

በፋሲካ በዓልም ከሁለቱ ጨዋታዎች በስተቀር ሌላ ዘፈን አይኖርም። ወንዶች ጊጤ የሚባል የጦር ውርወራ ውድድር ሲያደርጉ ሴቶቹ ደግሞ ወንዶቹ ከሚጫወቱበት ቦታ ብዙ ሳይርቁ ከቅርብ ርቀት ጨዋታቸውን ያከናውናሉ። በገናና በፋሲካ ወቅት ጨዋታው የሚጀመረው ከሰዓት በኋላ የፀሐይዋ ግለት መቀነስ ሲጀምር 9 ሰዓት አካባቢ ሲሆን የሚጠናቀቀው ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ጨለማው ዓይን መያዝ ሲጀምር ነው።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ዘጠኝ ሰዓት የሚጀምሩበት ምክንያት "ሴት ልጅ በጧት ተነስታ የምትከውናቸው የቤት ውስጥ ሥራዎች ስላሉ ነው። ምሳ ከተበላ በኋላም የመተጣጠቢያና የመኳኳያ ጊዜ ያስፈልጋታል።" (የቡድን ውይይት፣ ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም)




የአበሹቴና የኧሸይቦሌ ጨዋታዎች ከመጀመራቸው በፊት የማሟሟቂያ ዘፈን ሲዜም

### 4.2.1. የኧሸይቦሌ ቃል ግጥሞች አከዋወን

ኧሸይቦሌ ጨዋታ ሴቶቹ እጆቻቸውን በግራና በቀኝ በሚገኙ ጓደኞቻቸው ትከሻ ላይ በማድረግ ክብ ሠርተው ዜማውን ተከትለው ጎንበስ ቀና በማለት በስልት በመወዛወዝ መስመራቸውን ጠብቀው በመዞር የሚከውኑት ጨዋታ ነው። ጨዋታው እንደ ተሳታፊዎቹ ብዛት በተለያዩ ቡድኖች በመከፋፈል ይከወናል። የአንዱ ቡድን ብዛት ከ10 እስከ 20 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል። አንድ ቡድን አልፎ አልፎ የተለያየ የእድሜ ደረጃ ባላቸው አባላት ሊመሰረት ቢችልም አብዛኛውን ጊዜ ግን ተቀራራቢ እድሜ ባላቸው ሴቶች ይመሠረታል። (የቡድን ውይይት፣ ጥር 24 ቀን 2006 ዓ.ም)

እያንዳንዱ ቡድን በአንድ አውራጅ እየተመራና በሌሎቹ አባላት እጀባ ጨዋታው ይቀጥላል።

አውራጅ- ኧሸይቦሌ ኧሸይቦለሌ (2)

ተቀባይ፡- ኧሸይቦሌ ኧሸይቦለሌ (2)

አውራጅ-    ኧኸይቦሌ አከሌ አበሉ፣  ኧኸይቦሌ የሎሚ ዛፍ፣

ተቀባይ፡-    ኧኸይቦሌ ኧኸይቦለሌ (2)

አውራጅ-    ኧኸይቦሌ አንቺን ያገባ፣ ኧኸይቦሌ ይበል ዘራፍ።




**የኧኸይቦሌ ጨዋታ በወጣት ሴቶች ሲከወን**

የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች  ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት የሚሆን የጊዜ እርዝማኔ ከተጫወቱ በኋላ ቀጣይ ጨዋታ ወደ ሆነው የአበሹቴ ጨዋታ ይሸጋገራሉ።

### 4.2.2. የአበሹቴ ጨዋታ አከዋወን

አበሹቴ ሴቶች በአብዛኛው እንደየእድሜ ደረጃቸው በሁለት ቡድን ተከፍለው የሚከውኑት ጨዋታ ነው። አንድ ቡድን ከ8 እስከ 12 የሚደርሱ አባላት የሚኖሩት ሲሆን የቡድኑ አባላት በተርታ ወይም በመደዳ በመቆም እጆቻቸውን በጓደኞቻቸው ትከሻ ላይ በማድረግ ተቃቅፈው ይቆማሉ። የተቃራኒው ቡድን አባላትም ፊታቸውን ወደ ተቃራኒ ቡድን በማድረግ ተቃቅፈው ይቆማሉ። እንደ ቦታው ስፋትና ጥበት ሁለት ወይም ሦስት እርምጃ እንደተቃቀፉ ወደኋላ እያዜሙ በማፈግፈግ ከተራራቁ በኋላ የዜማውን ስልት ተከትለው እንደገና ወደፊት በመጠጋጋት ይቀራረባሉ። እግሮቻቸው

ዜማውን ተከትለው በስልት እየረገጡ አንዴ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ቀጥሎ በመቀራረብ ቃል ግጥሞቹን እየተቀባበሉ ተራ በተራ ያዜማሉ።




**የአበሹቴ ጨዋታ በሁለት ቡድን ተከፍለው ሲጫወቱ**

የሁለቱ ቡድኖች አውራጆች ወይም አቀንቃኞች ተራ በተራ እየተቀባበሉ የሚያዜሙ ሲሆን ተቀባዮቹ ግን ሁለቱም አውራጆች ሲያቀነቅኑ በጋራ በመቀበል ያጅቧቸዋል። የአንዱ ቡድን አቀንቃኝ አንድ ግጥም ካወረደች በኋላ ተራውን ለተቃራኒ ቡድን አቀንቃኝ የመልቀቅ ግዴታ አለባት።

| | |
|---|---|
| አውራጅ | አበሹቴ አበሹት እያያ |
| ተቀባዮች | አበሹቴ አበሹት እያያ |
| አውራጅ ፡- | አበሹቴ ያ የማነው እንዝርት? |
| ተቀባዮች፡- | አበሹቴ አበሹት እያያ |
| አውራጅ፡- | አበሹቴ እመከታው ላይ፤ |
| ተቀባዮች፡- | አበሹቴ አበሹት እያያ |
| አውራጅ፡- | አበሹቴ እከሊት አበሉ፣ |
| ተቀባዮች፡- | አበሹቴ አበሹት እያያ |
| አውራጅ፡- | አበሹቴ የቀጭን ፈታይ። |

የመጀመሪያዋ አውራጅ አንድ የቃል ግጥም እንዳዜመች ተራዋን ለተቃራኒ ቡድን አቀንቃኝ ወይም አውራጅ ታስረክባለች። እየተቀባበሉ ካዜሙ በኋላ ከደከማቸው ወይም ግጥም ካለቀባቸው የአውራጅነቱን ቦታ ፈቃደኛ ለሆኑ የቡድን አባላት ያስረክባሉ። ተረካቢዎቹም የሚበቃቸውን ያህል ካወረዱ በኋላ ለቀጣይ ተረኛ በመስጠት ጨዋታው ይቀጥላል። በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝታችን እንዳየነው ከዋኞች ለቃል ግጥሙ ተስተላልፎ ትልቁን ሚና የሚጫወቱ ናቸው። የአበሹቴም ሆነ የኧኸይቦሌ ቃል ግጥም ከዋኞች ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከቦታ ወደ ቦታ የሚደረገውን ተስተላልፎ የሚያስቀጥሉ ናቸው። መረጃውን በሰበሰብኩባቸው ቀበሌዎች በምልከታዬ እንዳረጋገጥኩት በአንዱ ክብረበዓል ሲያቀነቅኑ የነበሩ አውራጆች በሌላው ቀበሌም ንቁ ተሳታፊዎች ነበሩ።

የአበሹቴ ጨዋታ አከዋወን አራት ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች አሉት። በመጀመሪያ ሴቶቹ እንደየፍላጎታቸው በሁለት ቡድን ይደራጃሉ። በቡድን የሚደራጁት በአብዛኛው ባላቸው የጓደኝነት ደረጃ ወይም መቀራረብ ነው። በቡድን ከተደራጁ በኋላ ጨዋታውን የሚጀምሩት የጨዋታውን አዝማች በጋራ በማዜም ነው። የአበሹቴ አዝማች ግጥም ከሌሎቹ የአበሹቴ ግጥሞች ረዘም ያለ ነው። አዝማቹን ግጥም በመቀባበል ካዜሙ በኋላ ወደ ሁለተኛው ደረጃ ይተላለፋሉ።

**የአበሹቴ አዝማች**

እርግብ እርግቦሽ ለማዳ፣
ምናበረረሽ አሸዋ ሜዳ? (2)
አበረረኛ ክፉ እረኛ! (2)
እኔን ያብርረኝ ያክንፈኛ (2)
የሆዱን ብሶት ሳይነግረኛ(2)
የሆዱን ብሶት ቢነግርሽ፣
ትሂጃለሽ ወይ ተሻግረሽ ?
ለምን አልሂድም ተሻግሬ?
ከናት ካባቴ ተማክሬ፤
የምወደውን አስከትዬ፣
የሴት እቃዬን አንጠልጥዬ።

መረጃ ከሰበሰብኩባቸው በዓላት መካከል ይህን የአበሹቴ ቃላዊ ግጥም በመግቢያነት የተጠቀሙት ጥር 18 ቀን 2006 ዓ.ም የሰባር አጽሙ ጊዮርጊስ የታቦት ንግስ ዕለት ብቻ ነበር። ነገር ግን በቡድን ውይይት ወቅት ባገኘሁት መረጃ ቀደም ሲል በሌሎች ቦታዎችም አጀማመሩ በዚሁ መግቢያ ግጥም እንደነበር ቀስ በቀስ ግን እየቀረ እንደመጣ ልረዳ ችያለሁ። "የአበሹቴ ጨዋታ ታቦት ገብቶ፣ ዘፈን ተዘፍኖና የኾሽይቦሌ ጨዋታ ከተከናወነ በኋላ በመጨረሻ ላይ የሚከወን በመሆኑ ለሴቶቹ የጊዜ እጥረት እንዳያጋጥም ወይም እንዳይመሽ ቀጥታ ወደ ዋናው ጨዋታ ለመግባት ሲባል ቀርቷል።" በማለት ገልጸውልኛል። (የቡድን ውይይት፣ ጥር 24 ቀን 2006ዓ.ም)

በአበሹቴ ጨዋታ ሁለተኛው ደረጃ (በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቦታዎች የመጀመሪያው ደረጃ እየሆነ ነው።) ተቃራኒ ቡድኖች የሚሞጋገሱበት ነው። በአብዛኛው የጨዋታው ክፍለ ጊዜ ተቃራኒ ቡድኖች የሚሰዳደቡ ቢሆንም አጀማመሩ ግን በመሞጋገስና በመደናነቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ጨዋታው የተቃራኒ ቡድን አባላትን ጥሩና መልካም ባህርያትን ነቅሶ በማውጣት በማሞካሸት ከተሟሟቀ በኋላ ወደ ቀጣዩና ወደ ዋናው የጨዋታ ክፍል ይሸጋገራል።

በጨዋታው ሦስተኛ ደረጃ ተቃራኒ ቡድኖች በየቡድን አቀንቃኞቻቸው እየተመሩ ተራቸውን ጠብቀው እያንዳንዱን የተቃራኒ ቡድን አባል ይሳደባሉ። በየመንደሩ ወይም በየጎረቤቱ የሚታሙና በሹክሹክታ የሚነገሩ ጉዳዮች ወይም ሀሜቶች በዚህ ጨዋታ ወቅት በግጥም መልክ ይፋ ይሆናሉ። እያንዳንዷ አባል እንዳለባት የችግር ዓይነት ሙያ የሌላት፣ ፀባይ የሌላት፣ አመንዝራ የሆነች፣ የእጅ አመል ያለባት፣ መልከ ጥፉ የሆነች፣ ጽዳቷን የማትጠብቅ ወዘተ. እየተባለች ትሰደባለች።

በጨዋታው አራተኛና የመጨረሻው ክፍል በመሞጋገስ ለሚቀጥለው ዓመት በሰላም እንዲያደርሳቸው መልካም ምኞት በመመኘት፣ በመለያየታቸው ማዘናቸውን በመግለጽ የሚሰነባበቱበት ነው። የአበሹቴ ጨዋታ በመሞጋገስ እንደተጀመረ ሁሉ በመሞጋገስ ይጠናቀቃል። ወደቤታቸው ሲገቡ ቂምና ቁርሾ ይዘው እንዳይሄዱ ጥሩ ስሜት ኖሯቸው እንዲለያዩ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

## 4.3. በታቦት ንግሥና በዓበይት የክርስቲያን በዓላት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች አውድ

በዚህ ክፍል የደላንታ ወረዳ ሴቶች በቡድን ሆነው የሚያዜሟቸው የቃል ግጥሞች በሚከውኑባቸው የታቦት ንግሥና ዓበይት የክርስቲያን ክብረ በዓላት አጋጣሚዎች አውዳቸው ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች በታቦታት ንግስ ወቅት የሚከወኑት ታቦት ከገባ በኋላ ነው። ታቦት እስኪገባ ድረስ ወንዶች "ሆ" ሲሉ ሴቶች እንደየፍላጐታቸው በሁለት ምድብ ዓለማዊና መንፈሣዊ ዜማ ያቀነቅናሉ። በአብዛኛው እናቶች እና ጥቂት ወጣት ሴቶች በመንፈሣዊ ዜማ "በወግ ያግባህ በወግ" እያሉ እልልታውን እያቀለጡ ሲያቀነቅኑ አብዛኞቹ ወጣት ሴቶች አለማዊ የሆኑ ባህላዊ ዘፈኖችን ያቀነቅናሉ። የሚዘፈኑት ዘፈኖች አብዛኞቹ በይዘታቸው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው።

ታቦት ከገባ በኋላ እናቶችና ሁሉም ወንዶች ወደ ሰንበቴ ቤት ሲገቡ ወጣት ሴቶችና ህፃናት እዚያው ቤተክርስቲያን ውስጥ ከበሮ እየመቱ ይዘፍናሉ። የሴቶቹ ዘፈን የሚቀጥለው ጠላ ጠጥተው ሞቅ ያላቸው ወጣቶች ከበሮውን እስከሚቀበሏቸው ድረስ ብቻ ነው። ቅድሚያ አግኝተው የተስተናገዱ ወንድ ወጣቶች ወደ ዘፈኑ ይመለሳሉ። ቀስ በቀስ የወንዶቹ ቁጥር እየበዛ ሲሄድ ሴቶቹ ከበሮውን አስረክበው ከቤተክርስቲያኑ ግቢ በመውጣት በየአመቱ ታቦቱ ሲነግስና የጥምቀት ዕለት ብቻ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን ወደሚከውኑባቸው ቀደሞ ወደሚታወቀው ቦታ ይሄዳሉ።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች በገና እና በፋሲካ ዕለታት የሚከወኑት በየጎጡ በተሰባሰቡ ሴቶች ብቻ ነው። በዕለታቱ ታቦት ስለማይነግሥ ከሌላ አካባቢ የሚመጡ እንግዶች አይኖሩም። በዚህም ምክንያት የተመልካቹ ቁጥር ይቀንሳል። ከነዋሪው ውጪ የሚመጡና የሚሳተፉ ቢኖሩ ሌላ ቦታ ባል አግብተው በዕለቱ ቤተሰቦቻቸው መልስ የጠሯቸው ሴት ወጣቶችና ባጋጣሚ የተገኙ እንግዶች ብቻ ናቸው።

### 4.3.1. በታቦት ንግሥ የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ጨዋታዎች ቃል ግጥም አውድ

ከዚህ ቀጥሎ ሥላሴ ታቦት ንግሥ ወቅት የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ጨዋታዎች ቃል ግጥም አከዋወን አውዱ ምን ይመስል እንደነበር እንመለከታለን።

#### 4.3.1.1. በታቦት ንግሥ የኧኸይቦሌ ጨዋታ አውድ

ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም በቄጳ ምስትንክር ቀበሌ የሥላሴ ታቦት ንግሥ ዕለት ከ9 ሰዓት ተኩል እስከ 11 ሰዓት ከሩብ ድረስ የኧኸይቦሌ ጨዋታ ተከውኗል። ወጣት ሴቶችና ህፃናቱ ከሚዘፍኑበት ቦታ ተነስተው በፍጥነት እየተራመዱ ኧኸይቦሌና አበሹቴ መጫወቻ ሜዳ ሲደርሱ የመጀመሪያው ቡድን በ11 ወጣት ሴቶች ተመስርቶ ጨዋታው ተጀመረ።

የስምንቱ ተጫዋቾች ልብስ ከላይ ጥቁርና አረንጓዴ መስመር ያለው ሹራብ ሲሆን ቀሚሣቸው  ከፋብሪካ ውጤት የተሰፋ ነው። አራቱ ሴቶች ከሹራቡ ላይ አነስተኛ የአንገት ልብስ በእነሱ አጠራር ሻርፕ ጣል አድርገዋል። ሶስቱ ሴቶች ከላይ አረንጓዴ ቀለም ያለው የቱታ ጃኬት የለበሱ ሲሆን ቀሚሣቸው ከፋብሪካ ውጤት የተሰፋ ሆኖ ከስር አረንጓዴ ቱታ ለብሰዋል። ያገቡ ወጣት ሴቶችና እናቶች የለብሱት ለገበያ ቀንና ለተለያዩ ክብረ በዓላት የሚለብሱትን የክት ልብስ ነው። አራቱ ሴቶች ጸጉራቸውን በጥቁር፣ አንዷ ነጭ ሆኖ ጥቁር ነጠብጣብ ባለው ሻሽ ያሰሩ ሲሆን ሌሎቹ በቀጭኑ ሹርባ ተሰርተው በቅባት አርሰውታል። ቡድን የመሰረቱት ወጣት ሴቶች ሲያቀነቅኑ ለጊዜው መጫወት ያልፈለጉ ሴቶችና ህጻናት ዙሪያውን ከበው ተመልካች ሆነዋል።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁለተኛ ቡድን ተመሰረተ።  ቡድን የመሰረቱት ወጣት ሴቶች ሲያቀነቅኑ መጫወት ያልፈለጉ ሴቶችና ህፃናት አሁንም ዙሪያውን ከበው ይመለከቷቸው ነበር። በጨዋታው ላይ ያሉት ሴቶች ከውጭ የቆሙትን ወደ ጨዋታው ለመሣብና ለማጓጓት እየደጋገሙ

ሀ. ኧኸይቦሌ ማለት የአባት እድር ነው፣
ያንቺ ኩራትሽ እምኑ ላይ ነው።

ለ. ሳዱላ ሁሉ ተቀምጠሽ፣
ከቁንጮጮሽ ላይ ወፍ አራብሽ፣
ጎንበስ በይና ላራግፍልሽ።

(ንግስቱ አከለ፣ ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም)

በማለት በግጥም ሀ የኧኸይቦሌ ጨዋታ ከጥንት ከጧቱ ጀምሮ የነበረ ባህላችን ሆኖ ሳለ አንቺ የማትጫወቺው ማን ሆነሽ ነው? ብሎ በመጠየቅ ተመልካች የሆኑ ሴቶች

ባህላቸውን መናቅ እንደሌለባቸው በማሳሰብ በጨዋታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ጋብዘዋል። በግጥም ለ ደግሞ አንድ ቦታ ተገትራችሁ ከምትቀሩና የወፍ ኩስ መጣያ ከምትሆኑ ከእኛ ጋር ተቀላቅላችሁ ተጫወቱ የሚል ግብዣ በማቅረብ አቀንቅነዋል። ከውጭ የነበሩት ተመልካቾችም ቀስ በቀስ አንድ አንድ እያሉ ወደ ጨዋታው እየተጨመሩ ክቡ እየሰፋ፣ እየሰፋ፣ እየሰፋ ሄደ። ከሃያ አምስት ደቂቃ በኋላ ክቡ ለሁለት ተከፍሎ ሁለት ቡድን ተመሰረተ።

የጨዋታው ሜዳ ከሰንበቴ በተመለሱ እናቶችና ታዳሚ/ ተመልካች ወጣት ወንዶች ቀስ በቀስ እየተሞላ መጣ። የሰንበቴ ጠላ ሲጠጡ የነበሩ እናቶች አንዳንዶቹ ነጠላቸውን ለተመልካች በመስጠት አንዳንዶቹ እንደለበሱት ጨዋታውን ተቀላቀሉ። አንዳንድ እናቶች ከወጣቶቹ ጋር ተቀላቅለው ሲጫወቱ ዘጠኝ እናቶች የራሳቸውን ቡድን መሠረቱ።

እናቶች ከወጣቶቹ በአለባበሳቸው የተለዩ ናቸው። እቤት ውስጥ በተፈተለ ጥጥ የተሠራ ባህላዊ ቀሚስና ነጠላ ለብሰዋል። አብዛኞቹ ሻሽ አስረዋል። ከመካከላቸው አንዳንዶቹ ህጻን እንዳዘሉ ወደ ጨዋታው ተቀላቀሉ። ወጣት ወንዶች ከበሮውን ከሴቶቹ ከተቀበሉ በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል እንኳ አልዘፈኑም። እየተንጠባጠቡ ሴቶቹ ወደሚጫወቱበት ቦታ በመሄድ ዙሪያውን ከበው ተመልካች ሆኑ። በየቡድኑ ያሉ አቀንቃኞች እየደከማቸው ሲሄድ ጓደኞቻቸውን በስም እየጠሩ እንዲሩዱቸው በማሰብ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ።

> አለም ታረቀኝ ተቀበይኝ፣
> ማይሳማተኝ ማይጠፋብኝ።

(እመቤት ያረጋል፣ ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም)

በማለት እመቤት ጓደኛዋን የአቀንቃኝነቱን ተራ ተቀበይኝ ስትላት ዓለምም ተቀብላ የከዋኝነት ተግባሯን ቀጠለች። ከአቀንቃኝ አቀንቃኝ እየተቀባበሉ ቆይተው 11 ሰዓት ላይ የእሽይቦሌው ጨዋታ በአበሹቴ ጨዋታ ተተካ።

የጨዋታው ሽግግር በጣም ፈጣን ነበር። አንዱ ቡድን አበሹቴ ለመጫወት ክቡ ለሁለት ቡድን ሲከፈል የሁለተኛው የእሽይቦሌ ቡድን በቅጽበት ፈርሶ ከመጀመሪያው ቡድን ጋር ተቀላቀለ።

### 4.3.1.2. በታቦት ንግሥ የአበሹቴ ጨዋታ

ጥር 7 ቀን 2006 ዓ.ም ዘጠኝ ሰዓት የተጀመረው የኸኽይቦሌ ጨዋታ አስራአንድ ሰዓት ላይ በአበሹቴ ጨዋታ ተተክቷል። የአበሹቴው ጨዋታ ቡድን አመሰራረት ትርምስ የበዛበት ነበር። ጓደኛሞች የተቃራኒ ቡድን አባል ሆነው እርስ በርስ ላለመሰዳደብ ሲሉ በአንድ ቡድን ለመካተት መጓተትና እርስ በርስ መሟሟብ ከተደረገ በኋላ ሁለት ተቃራኒ ቡድኖች ተመሰረቱ። የአንዱ ቡድን አቀንቃኝ የሁለቱም ቡድን አባላት እየተቀበሏት የመጀመሪያውን የውዳሴ ግጥም፣

ያ የማነው እንዝርት እመከታው ላይ፣
አታላይ የማነ የቀጭን ፈታይ፤
መፍተሉንማ ማንም ይፈትለዋል፣
እንደ አታላይ አ'ርጎ ማን ያሳምረዋል?

ብላ ካቀነቀነች በኋላ ተራውን ለተቃራኒ ቡድን ለቀቀች። ተቃራኒ ቡድን አቀንቃኝም ከዚህ በታች የቀረበውን አንድ የውዳሴ ግጥም አዜመች።

ጎተራ ላይ ሁና ታሽካካለች ዶሮ፣
አበቡ ከቤ ድልድል ወይዘሮ።

በማለት ካወደሰች በኋላ ለተቃራኒ ቡድን ተራውን ስትለቅ ባለተራው ቡድን አቀንቃኝ ቀደም ሲል ስሟን ጠርታ ያወደሰቻትን ሴት፣

ወዲያ ማዶ ጤፍ ወዲህ ማዶ ጤፍ፣
አታላይ የማነ የማነሽ ሙጢአፍ ?

በማለት ሰደበቻት። በመጀመሪያው የውዳሴ ግጥም የስሜት ለውጥ ሳታሳይ ሙገሳውን የተቀበለችው አታላይ የመጀመሪያው የስድብ ግጥም ሲዜምባት ግን እየሳቀች በሀፍረት ፊቷን በአንድ እጇ ሸፈነች። ተረኛው የነአታላይ ቡድን አቀንቃኝ የስድብ ግጥም ማስታወስ ተቸግራ በእፍረት አቀርቅራ ስትቀር ተመልካቹ በሣቅ አውካካ። በዚህ ጊዜ ዱላ የያዘ የ8 ዓመት ወንድ ልጅ "እኔ ልበልላችሁ" በማለት በሁለቱ ቡድን መሐል ሲያልፍ ተመልካቹ እንደገና በሣቅ ተንከተከተ። ከዋኟ እንደምንም ብላ የመጀመሪያውን የስድብ ግጥም፣

እንሰዳደብ ካልሽ እኔ እበልጥሻለሁ፣

በጥርሶችሽ መሃል አር አይቼብሻለሁ።

በማለት ተራዋን ከተወጣች በኋላ ጨዋታው ተሟሙቋል። ተመልካቹ በኧኸይቦሌ ጨዋታ ወቅት ፍዝ ተመልካች የነበረ ሲሆን በአበሹቴ ጨዋታ ጊዜ ግን እያንዳንዱን ግጥም በሰማ ቁጥር የሳቅ ምላሽ እየሰጠ ጨዋታው ቀጠለ። ለተመልካቹ ንቁነት የግጥሞቹ ይዘት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

በጨዋታው ወቅት ተመልካቹ የተጫዋቾቹን የመንቀሳቀሻ ቦታ ስለሚያጣብብ አንዳንድ ተመልካቾች "ሰፋ ሰፋ አድርጉላቸው" በማለት ለጨዋታው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ። በመጨረሻም ፀሐይዋ በሻገር ከሚገኘው ጋራ ጀርባ ገብታ ስትሰወር መጀመሪያ እናቶች እየተንጠባጠቡ ወደየቤታቸው ሲሄዱ ቀስበቀስ ወጣቶቹም ቁጥራቸው እየቀነሰ ሄደ። ጨለማው ለዓይን ያዝ ሲያደርግ መጨረሻ የቀሩት የሚከተለውን ዜማ አቀነቀኑ። "አመት ያድርሰን ዓመቱ፣ ሳይለያየን አጅሬ ሞቱ።" ከዚያም ሁሉም ወደ ተለያየ አቅጣጫ ተበታተኑ።

### 4.3.2. በዓበይት የክርስቲያን በዓላት የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ጨዋታዎች ቃል ግጥም አውድ

ሚያዝያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም የዕለተ ፋሲካ በቄዳ ምስትንክር ቀበሌ ወገላት በተባለችው መንደር ልዩ ስሟ "ዋንዛው መንደር" በተሰኘች ጎጥ የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ክዋኔ በቦታው በመገኘት አውዱ ምን እንደሚመስል ተመልክቻለሁ።

#### 4.3.2.1. በፋሲካ በዓል የኧኸይቦሌ ጨዋታ አውድ

ቦታው ትልቅ የዋንዛ ዛፍ ያለበት ነው። በዋንዛ ዛፉ በስተምሥራቅ የቅንጭብትና የቁልቋል አጥር አለ። ከቁልቋሉና ቅንጭብቱ ቀጥሎ አንድ ማሳ፣ ከማሳው ቀጥሎ ወንዝ አለ። በስተምዕራብ በኩልም የአካባቢው ሰዎች ለመጠጥ የሚጠቀሙበት ወንዝ በግምት በመቶ ሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። በዋንዛውና በወንዙ መካከል ቁጥቋጦ የበዛበት ቁልቁለት መንገድ አለ። ሰዓቱ ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኗል። በቦታው ቀድመው የተገኙት ሕጻናት ናቸው። ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን በቁጥር ዘጠኝ የሆኑ ወንድ ታዳጊ ወጣቶች ከአንድ ሜትር የማያንስ የእንዶድ ዛፍ ግንድ (ሥር?) ተሸክመው በመምጣት ከዛፉ በግምት ሠላሳ ሜትር ርቀት ላይ መሬቱን ቆፍረው የተወሰነ አካሉን

ወደ መሬት ውስጥ በማድረግ አቆሙት። ቀጥለው በቡድን ተመዳድበው ቀደም ሲል ባዘጋጁት ቀጭን ረጅም የእንጨት ጦር ግንዱን ዒላማ ያደረገ ውድድር ጀመሩ።

ሴት ህጻናቱ ከፊሎቹ ዛፉ ሥር ቁጭ ብለው ሲያወሩ ከፊሎቹ የታዳጊ ወጣቶቹን የጦር ውርወራ ውድድር ከኋላ ሆነው እየተመለከቱ የወጣት እና የጎልማሳ ሴቶችን መምጣት በትዕግስት ይጠባበቃሉ። ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ወጣትና ጎልማሳ ወንዶችና ሴቶች ከየቤታቸው በመውጣት መሰባሰብ ጀመሩ። ዘጠኝ ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ላይ በስምንት ወጣት ሴቶች የኧኸይቦሌ ጨዋታ ተጀመረ። ጨዋታው ዛፍ ሥር በመሆኑ የፀሐዩ ግለት ለተጨዋቾቹ ችግር አልፈጠረባቸውም። ሴቶቹ ጨዋታውን ሲጀምሩ ሰባት ሆነው ቢሆንም የጨዋታን መጀመር የሰሙ ሌሎች ሴቶች አስር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሜዳዋን አጥለቀለቋት። በዘጠኝ ታዳጊ ወንድ ወጣቶች የተጀመረው የጦር ውርወራ ውድድርም ረጃጅምና ጫፉ የሾለ የእንጨት ጦር በያዙ ወንዶች ተወረረ።

አንዳንዶቹ ሴቶች ከቤታቸው እንደመጡ አፍታም ሳይቆዩ ተንደርድረው የኧኸይቦሌ ጨዋታውን ሲቀላቀሉ አንዳንዶቹ ለጊዜው ተመልካች መሆንን መርጠው ዙሪያውን ተኮለኮሉ። በርካታ ሴት ህጻናትና ጥቂት ወንድ ህጻናት ዙሪያውን ከበው ቃል ግጥሞቹን እየሰሙ ክዋኔውን ሲከታተሉ አንዳንድ ህጻናት ክቡ ውስጥ ገብተው ቆሙ ። ክቡ ውስጥ የተቀመጡ ህጻናትም ነበሩ።

የኧኸይቦሌ ተጫዋቾቹ ዙሪያ ክብ ሠርተው እጅ በትከሻ ላይ አድርገው በመተቃቀፍ የቃል ግጥሙን ዜማ ተከትለው የእግራቸውን አረጋገጥ፣ የጭንቅላታቸውንና የትከሻቸውን እንቅስቃሴ እያለዋወጡ ይሽከረከራሉ። የኧኸይቦሌ ጨዋታ እንደ ግጥሙ ዓይነት ዜማው የተለያየ በመሆኑ አቀንቃኟ ግጥሙን በየስልቱ ስታዜም ተቀባዮቹ ዜማውን ተከትለው እንቅስቃሴያቸውን ይለዋውጣሉ።

"አሆይ ሰልዬ አሆይ ሰልዬ "
"መገና ላይ ላይ በላቸው፣ (2)
ወደ መጡበት ወዳገራቸው።"
"ስብርብር በይለት" (2)
በሽጌው ሞት።"

"ኧኸይቦልየ ኧኸይቦለሌ" (2)

"እሽምቡቧ፣ "

አቀንቃኟ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን አዝማቾች በተወሰነ የጊዜ ርቀት እየለዋወጠች ስታዜም ተቀባዮቹም የእሷን ዜማ ተከትለው ቅላጼያቸውንና እንቅስቃሴያቸውን ይለዋውጣሉ። በምልከታዬ እንደተረዳሁት የኧኸይቦሌ ጨዋታ ቃል ግጥሞች ከአበሹቴ ቃል ግጥሞች አንጻር ለፈጠራ የሚገፋፉ ሁኔታ አነስተኛነት ምክንያት የቃል ግጥሞቹ ብዛት በቁጥር ውስን ቢሆኑም የዜማው ዓይነት መብዛትና የእርስ በርስ መወዳደሱ ጨዋታው ሳይሰለች ለረጅም ሰዓት እንዲከወን አድርጎታል። በፋሲካ ዕለት ዘጠኝ ሰዓት ከአምስት የተጀመረው የኧኸይቦሌ ጨዋታ ተራውን ለአበሹቴ ጨዋታ የለቀቀው አስራአንድ ሰዓት ላይ ነው። በኧኸይቦሌ ጨዋታ ጊዜ የወንዶች ሙሉ ትኩረት የጦር ውርወራ ውድድር ላይ ነበር።

#### 4.3.2.2. በፋሲካ በዓል የአበሹቴ ጨዋታ አውድ

ሚያዝያ 12 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው የፋሲካ በዓል የኧኸይቦሌ ጨዋታ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ አበሹቴ ጨዋታ የተደረገው ሽግግር በታቦት ንግሥ ዕለታት እንደነበረው ሽግግር ትርምስ የበዛበት አልነበረም። ተጫዋቾቹ በአንጻራዊነት በቁጥር የቀነሱና የአንድ መንደር ልጆችም በመሆናቸው ማን ከማን ጋር እንደሚቧደኑ ቀድመው በልባቸው የወሰኑ ይመስላሉ፤ በቀላሉ ሁለት ቡድን መሥርተው ጨዋታውን ቀጥለዋል።

በኧኸይቦሌ ጨዋታ ጊዜ የራሳቸው ጨዋታ በሆነው የጦር ውርወራ ውድድር ላይ ተጠምደው የነበሩ ወንዶች በአበሹቴ ጨዋታ ጊዜ ቀስ በቀስ የሴቶቹን ጨዋታ መክበብ ጀመሩ። በጦር ውርወራ ጊዜ ተራ ጠባቂና ተመልካች የነበሩት ሁሉ በአበሹቴ ጨዋታው ዙሪያ ተሰባሰቡ። በአበሹቴው ጨዋታ እንደተለመደው በተቃራኒ ቡድን መካከል የሚደረገው የመወዳደስ ዜማ ከተቀነቀነ በኋላ መሰዳደቡ ቀጠለ። የመጀመሪያዋ ተሳዳቢ ቡድኗን ወክላ ስም ሳትጠራ የተቃራኒ ቡድን አባላትን በሙሉ የሚሰድብ ቃል ግጥም አወረደች።

እንሳደብስ ካልሽ እንውጣ ተራራ፣

አርሽን አሸክሜ በሰባራ እንስራ።

በማለት አድራሻው ለማን እንደሆነ የማይለይ ግጥም በማዜም አጠቃላይ ቡድኑን በመስደብ ተጀመረ። የተረኛው ቡድን አቀንቃኝ በተራዋ፣ የሚከተለውን ግጥም አዚማለች።

እንሰዳደብ ካልሽ እኔ እበልጣለሁ፣
በጥርሶችሽ መሃል አር አይቻለሁ።

ቀጥሎ ተረኛዋ አቀንቃኝ የተቃራኒ ቡድን የሆነችውን ከተማሽ የተባለች የተቃራኒ ቡድን አባል ሴት ስም በመጥራት የሚከተለውን ቃል ግጥም አቀነቀነች።

ከከተማሽ ጓሮ ዘልዬ ብገባ፣
ተከምሮ አየሁት አሯ እንደገለባ።

ተመልካቹ በአንድ ጊዜ በሳቅ ሲያውካካ የተቃራኒ ቡድን አቀንቃኝ ቡድኗን ወክላ ብድር ለመመለስ የተቃራኒን ቡድን አባል ስም ጠርታ እንደሚከተለው አዚማለች።

የሙሉነሽ አባት ምንኛ ከበረ፣
ልጁ እያራችለት፣ እሱ እየከመረ።

በዚህ መልኩ የሁሉም የቡድን አባላት ስም ተደጋግሞ እየተጠራ ሙያቸው፣ መልካቸው፣ ጽዳታቸው ወዘተ. እየተነሳ ስድቡ ቀጠለ። ተመልካቹ በየአንዳንዱ የቃል ግጥም መጨረሻ ላይ እየሳቀ ቆይቶ አስራሁለት ሰዓት ተኩል ላይ የተለመደው የመወዳደስ ግጥሞች በሁለቱም ቡድኖች ከተከወነ በኋላ ወንዱም ሴቱም ወደ የቤቱ ተበታትኗል።

## 4.4. የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ተስተላልፎ

በምዕራፍ ሁለት የንድፍ ሃሣብ ቅኝት ሲደረግ ተስተላለፎ ማለት የቃል ግጥሞቹ ከቦታ ቦታ ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉበትን ስልት የሚመልከት እንደሆነ መገለጹ ይታወሣል። በዚህም መሰረት የደላንታ ወረዳ ሴቶች የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን በየበዓላቱ በመገኘት ይለምዳሉ። የለመዱትንም በየበዓላቱ ተገኝተው በመከወን ቃል ግጥሞቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

በአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ተስተላልፎ ላይ ከዋኞች ትልቁን ድርሻ የሚይዙ ሲሆን ታዳሚዎችም የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በመስክ ምልከታዬ

እንዳረጋገጥኩት የቃል ግጥም ከዋኞች ከቀበሌያቸው ውጭ በሚነግሱ ታቦታት ዕለት ሲያቀነቅኑ ተመልክቻለሁ። ከከዋኞች በተጨማሪ በርካታ ተሣታፊዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ራቅ ብለው ሄደው ሚናቸውን ይወጣሉ። ለምሳሌ የጥር ስላሴ በቄዳ ምስትንክር ቀበሌ ሲጫወቱ ያየኋቸው ሴቶች ሰባት ኪሎ ሜትር ተጉዘው በድንግሎት ማሪያም የታቦት ንግስ ዕለት ሲጫወቱ ተመልክቻለሁ። በዚህም ከዋኞችና ተሳታፊዎች ቃል ግጥሞቹ ከቦታ ወደ ቦታ ተስተላልፎ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

ተስተልፎው ቀደም ሲል ያጠኑትን እንደ ገና መልሰው በመግጠም ወይም በአዲስ መልክ በመፍጠር ሊሆን ይችላል። በአበሹቴና በኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ከዘመን ወደ ዘመን ተስተላልፎው እንዲቀጥል ከታዳጊዎች ጀምሮ በእድሜ 50 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች  መሣተፋቸውን አስተውያለሁ፤ ይህም ሽግግሩ ከዓመት ዓመት ከዘመን ዘመን ቀጣይ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል። በመስክ ቆይታዬ ጨዋታውን በትኩረት ስትከታተል ያገኘኋት የ11 ዓመት ታዳጊ ድርብ ገዜ "በየበዓሉ ታላቅ እህቴን ተከትዬ እመጣና ጨዋታውን እመለከታለሁ፤ እስካሁን ተጫውቼ አላውቅም።" በማለት ገልፃለች። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 13፣ 2006ዓ.ም) እሙዬ ሀብታሙ እሷም እንደ ህፃን ድርብ  ተጫውታ ባታውቅም በየበዓላቱ ከእናቷና ከእህቷ ጋር ወደ ጨዋታው ቦታ በመምጣት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች እንደ ለመደች ገልፃልኛለች። ታናሽ እህቷን በማወደስ ቀጣዩን ግጥም አዚማልኛለች።

*ያ የማነው እንዝርት እመከታው ላይ፣*
*ዳግም ሀብታሙ ቀጭን ፈታይ።*
(ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 13 ቀን 2006 ዓ.ም)

በአጠቃላይ የደላንታ ወረዳ ሴቶች የቃል ግጥሞችን በሽምደዳ በፈጠራና አውድን ተከትሎ በማሣማማት በየክብረ በዓላቱ በመከወን ከቦታ ወደ ቦታ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጋሉ።

## 4.5. የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ፋይዳ

የቃል ግጥም ፋይዳ  ሲባል ቃል ግጥሞቹ ለስነቃሉ  ባለቤቶች ያላቸው ጠቀሜታ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት መጠቀሱ ይታወሣል። በክብረ በዓላት የሚከወኑት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ማህበረሰቡ መጥፎ የሚለውን ምግባር በመንቀፍ መልካም

የሚለውን በማወደስ ጠቃሚ የሚላቸውን እሴቶች ለማስጠበቅ የሚያገለግሉ ናቸው። የደላንታ ህዝብ ከወንዶች የሚጠብቀውን እንደ ጀግንነትና ታታሪነት የመሳሰሉት እሴቶችና ስነ ምግባሮች በአብዛኛዎቹ የኧሽይቦሌ ግጥሞች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከሴቶች የሚጠበቀውን እንደቸርነት፣ የትዳር ታማኝነትና ባለሞያነት የመሳሰሉ እሴቶችና ስነ ምግባሮች ደግሞ በአብዛኛው በአበሹቴ ቃል ግጥሞች ውስጥ እናገኛለን። በመሆኑም እነዚህ ቃል ግጥሞች የአካባቢውን ማህበረሰብ ስሜቱና ፍላጐት ማንጸባረቂያና ማስጠበቂያ በመሆን ያልተጻፈ ሕግ ሆነው ያገለግላሉ።

በምዕራፍ ሁለት የንድፍ ሃሣብ ቅኝት የቃል ግጥሞች ፋይዳ በሚለው ክፍል እንደቀረበው ሁሉ የአበሹቴና የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞችም እንደማንኛውም ማህበረሰብ ቃል ግጥሞች የስነ ቃሉ ባለቤት ለሆነው የደላንታ ማህበረሰብ "መልካም ናቸው የሚላቸውን እንደ ቸርነት፣ ደግነትና ታትሪነት የመሳሰሉት እሴቶች እንዲጠበቁና ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው የሚላቸውን ሌብነት፣ ስንፍናና አመንዝራነት የመሳሰሉት ተግባሮች ጐጂ እንደሆኑ ለማስተማር ጥቅም ላይ ያውላቸዋል።" (የቡድን ውይይት፣ ጥር፣ 24 ቀን 2006ዓ.ም)

የአበሹቴና የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔዎች ሴቶቹ እርስ በርስ እንዲግባቡና የቡድን ስሜት እንዲኖራቸው እንዲሁም ከጨዋታው ውጪም በማህበራዊ ኑሯቸው እንዲተሳሰሩ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም አቶ ተሾመ ካሴ፣ ጨዋታዎቹ ምን ጥቅም አላቸው? ብዬ ለጠየኩት ጥያቄ "ከተቃራኒ ቡድን በሚሰነዘር ስድብ በመነሳት ራሳቸውን እንዲገመግሙና እንዲያሻሽሉ፣ በውዳሴውም ደስታና እርካታ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በሌላ ጊዜ ፀያፍ የሚባሉ አነጋገሮችን በመጠቀም ሳያፍሩ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ።" በማለት ማብራሪያ ሰጥተውኛል።(ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 20 ቀን 2006 ዓ.ም) በእነዚህ ጨዋታዎች ሌላ ጊዜ የማይደፈሩ ወሲብ ነክ ቃላት ያለምንም እፍረት ይነገራሉ። ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ የማይነገሩ ነውር የሆኑ ቃላት በዚህ ጨዋታ ነውርነታቸው ይቀራል። በመጨረሻም ከጨዋታዎቹ የሚገኘው ተዝናኖትም በሥራ የከረመን አዕምሮና አካልን ፈታ የሚያደርግ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የአበሹቴና የኧኸይቦሌ የቃል ግጥሞች የይዘት ትንተና

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የቃል ግጥሞች እንደ ቃል ግጥሞቹ ዓይነት የሚከወኑበት አውድ ይለያያል። የሚከወኑበት አውድ ብቻ ሳይሆን ይዘታቸውም የተለያየ ነው። የቃል ግጥሞች የሚከወኑበት አውድ መለያየት እንዲሁም በሌላ በኩል ይዘታቸው መለያየቱ የቃል ግጥሞችን ለመተንተን በዓይነት በዓይነታቸው መቦደን አስፈላጊ ያደርገዋል። የቃል ግጥሞች በተመሳሳይ አውድ ቢከወኑም እንኳ ይዘታቸው ሊለያይ ይችላል። በአንፃሩ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች በተለያየ አውድ ሊከወኑ ይችላሉ። ስለሆነም ቃል ግጥሞቹን በቡድን መድቦ መተንተን ተገቢ ነው።

በዚሁ መሰረት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ የቃል ግጥሞችን የይዘት ትንተና ለማድረግ የአከዋወን ሂደታቸውንና ተግባራቸውን መሠረት በማድረግ ምደባ ተደርጓል። በመሥክ ሥራ ወቅት የተሰበሰቡት የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች በሁለት ዐበይት ክፍሎች ተመድበዋል። የአበሹቴ ግጥሞች በወጣትና ጐልማሳ ሴቶች የሚቀነቀኑ እንደመሆናቸው መጠን በይዘታቸው የሴቶችን፣ ሙያ፣ ቁንጅናና ባህርይ የሚያነሱ ሲሆን አልፎ አልፎ የሴቶቹ ባሎች፣ አባቶች ወይም ወንድሞች ከሴቶቹ ጋር በተያይዘ ምክንያት ሊነሱ ወይም ሊወደሱ ይችላሉ።

በአበሹቴ ክዋኔ በጨዋታው ሂደት መጀመሪያና መጨረሻ አካባቢ የቃል ግጥሞቹ ይዘት ሙገሳ ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን በአብዛኛው (በጨዋታው መሃል) መሰዳደብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በዚህም የተቃራኒ ቡድን ሴቶች ተራ በተራ የመሰደብ እጣ/እድል ይደርሳቸዋል። እነሱም በተራቸው ይሳደባሉ።

በዚህም መሠረት የአበሹቴ ግጥሞች የውዳሴና የስድብ ተብለው በሁለት ምድብ ተከፍለዋል። ቃል ግጥሞቹ በሁለት የተከፈሉበት ምክንያት በመሥክ ቆይታዬ መረጃ ባሰባሰብኩበት ወቅት በሁሉም ቦታዎች ሁሉም አቀንቃኞች ተመሳሳይ ይዘቶችን ሲያነሱ በውዳሴና በስድብ /በትችት/ ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ። እነዚህ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተመደቡ ግጥሞች እያንዳንዳቸው በንዑሳን ክፍሎች ተመድበዋል።

የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞችን ስንመለከት ሴቶች ራሳቸውንና የሴት ጓደኞቻቸውን ብቻ የሚያወድሱ፣ ወንዶችን የሚሳደቡ በጣም አልፎ አልፎ ብቻ ወንዶችን የሚያሞግሱ ናቸው። በኧኸይቦሌ ጨዋታ ወንዶችን ለመሳደብ የሚጠቀሙባቸው ቃል ግጥሞች አንዳንዶቹ ከሆታ ግጥሞች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፤ ልዩነታቸው የሚነገሩበት አውድ ብቻ ነው። በሆታ ጊዜ ወንዶች ፈሪ ወይም ሰነፍ ወንዶችን የሚሰድቡባቸው ሲሆን በኧኸይቦሌ ጨዋታ ግን ሴቶች ወንዶችን የሚያጥላሉባቸውና የሚሰድቡባቸው በጥቂቱ የሚያወድሱባቸው ግጥሞች ናቸው።

በኧኸይቦሌ ጨዋታ ሴቶች ሴቶችን አይሳደቡም። ይልቁንም እርስ በርስ ይሞጋገሳሉ። በቃል ግጥሞቻቸው ስለ ወደፊት ህይወታቸው ይመካከራሉ። በመጪው ጊዜ በትዳርና በሥራ ምክንያት መለያየታቸው የማይቀር ስለሆነ አሁን ጊዜያቸውን መጠቀም እንዳለባቸው ያሳስባሉ።

ከሠበሰብኳቸው 258 ቃል ግጥሞች መካከል 174ቱ የአበሹቴ 84ቱ የኧኸይቦሌ ናቸው። ከአበሹቴ ጨዋታ 59 ቃል ግጥሞችን (20 የውዳሴ 39 የስድብ) ከኧኸይቦሌ ጨዋታ 35 ቃል ግጥሞች ማለትም 26 የውዳሴና 9 የስድብ ቃል ግጥሞችን በየተመደቡበት ይዘት ሥር ተተንትነዋል። እነዚህ ግጥሞች የተመረጡበት ምክንያት በጥናቱ ለማሳየት የተፈለገውን ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ያሳያሉ ተብሎ በመታመኑ ነው ።

## 5.1. የአበሹቴ ግጥሞች ትንተና

የአበሹቴ ግጥሞች ያታን የሚለዩ ናቸው። ሴቶች ለሴቶች ብቻ የሚያቀነቅኗቸው ናቸው። ከመረጃ ሰጪዎች መካከል ወይዘሮ ብርዘገን ዘገየ "የአበሹቴ ግጥሞች ወጣትና ጐልማሳ ሴቶችን ለማወደስና ለመስደብ የሚቀነቀኑ ናቸው።" ሲሉ ገልፀዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ 14/05/2006 ዓ.ም) የአበሹቴ ግጥሞች የውዳሴና የስድብ ተብለው የተከፈሉ ሲሆን በውዳሴ ሥር ሞያን፣ ቸርነትን፣ ውበትን፣ ፍቅርን የሚገልፁ ተብለው ተመድበዋል። በስድብ ሥር አመንዝራነትን፣ ሌብነትን፣ ሙያቢስነት፣ መልከ ጥፉነትን የጽዳት ጉድለትንና ሆዳምነትን የሚገልፁ ተብለው በመመደብ ተተንትነዋል።

### 5.1.1. በአበሹቴ ጨዋታዎች የውዳሴ ቃል ግጥሞች

#### 5.1.1.1. ባለሙያነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

በነዚህ ግጥሞች ውስጥ የምትወደሰው ሴት ምን ያህል ባለሙያ እንደሆነች፣ በሴቶች ባልትና ወደር የሌላት እንደሆነች ይገለጽባቸዋል። ሁሉም ሴቶች ባለሙያ ቢሆኑም ይች ሴት ግን ከሁሉም የምትበልጥ አቻ የሌላት ናት የሚል ይዘት አላቸው። በተጨማሪም በእነዚህ የውዳሴ ግጥሞች ተሞጋሿ ከባለሙያዎች የምትበልጥ ባለሙያ እንደሆነች ይቀነቀንላታል።

ሀ　መፍተሉንማ ሁሉም ይፈትላል፣
　　የእከሊት አበሉ ከሁሉ ይበልጣል።

ለ　ሴቱ ድስቱን ጣደ ምኑን ሊሠራው?
　　እከሊት አበሉ ቅመሙን ይዛው።

ሐ　ሴት ወይዘሮ ሁሉ ሲበላ በሌማት፣
　　እከሊት አበሉ መሶበ ወርቅ አላት።

መ　ሴቶች ተሰባስበው ሙያ ሲቋጠሩ፣
　　እከሊት አበሉ ትበልጣለች አሉ።

ቃልግጥም/ሀ/ ሁሉም ሴቶች ፈትለው መልበስ የሚያስችል እውቀትና ብልሃቱ ቢኖራቸውም ይህች በስም የተጠራች ሴት ግን ወደር የላትም የሚል የተጋነነ የውዳሴ ድምጽ ያሰማናል ። "መፍተሉንማ ሁሉም ይፈትለዋል" በማለት ፈትል በማንም ሊከወን የሚችል ተራ ተግባር ነው በማለት ሥራውን በማቃለል ግጥሙ ከተናገረ በኋላ ይህቺ ሴት ግን ይህን ተራ ነገር በጥበቧ ከፍ ወዳለ ደረጃ ያሸጋገረችው መሆኑን ይገልጻል። "የእከሊት አበሉ ከሁሉም ይበልጣል።" በማለት እሷ የምትፈትለው ከሌሎቹ ሴቶች ፈትል ላቅ ያለ፣ የሸረሪት ድር የሚባለው ዓይነት ውበት አለው የሚል ሃሳብ ይዟል። ሞያ ያስከብራል፣ ያኮራል። ልዩ ሞያ ያላት ሴት ተራ ስላልሆነች ትከበራለች የሚል ይዘት አለው።

በቃል ግጥም /ለ/ ሁሉም ሴቶች ወጥ ቢሠሩም እንደዚች ሴት ጣፋጭ ወጥ መሥራት አይችሉም የሚል ይዘት እንመለከታለን። በማህበረሰባችን ወጥ መሥራት የሴቶች ሁሉ

ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህ ሁሉም ሴት ወጥ የመሥራት ግዴታውን መወጣቱ አይቀርም፤ እንደምንም ይሠራል። ግን "ሴቱ ድስቱን ጣደ ምኑን ሊሠራው" በማለት ችሎታው ወይም ሞያው በተሞጋሿ ሴት ቁጥጥር ሥር እንዳለ ግጥሙ ይናገራል። "እህሉ አንድ ሴቱ አስራሁለት" እንደሚባለው ሁሉም ሴቶች ተመሳሳይ የሆነ ችሎታ የላቸውም። በግጥሙ ሴቶች ወጥ ለመሥራት ድስታቸውን ቢጥዱም "እከሊት አበሉ ቅመሙን ይዛው።" በማለት የወጥ አጣፋጭ የሆነው ቅመም በእሷ እጅ ብቻ የሚገኝ ስለሆነ የሌሎቹ ሴቶች ልፋት ከንቱ ነው ይለናል። ከመረጃ ሰጪዎች መካከል ወ/ሮ አታሉ አስሜ "ወጥ እንዲጣፍጥ ቅመም አስተዋፅኦ አለው። ሽሮውና በርበሬው በቅመም ተመጥኖ መዘጋጀት አለበት። ይህ ብቻ በቂ አይደለም ወጡ ሲሰራ ከውሃ እስከ ጨው ያሉት በርካታ ቅመማት መመጠን አለባቸው ለመመጠን እውቀት ወይም ሞያ ያስፈልጋል" ሲሉ ገልፀውልኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 23 ቀን 2006 ዓ.ም) እንደ መረጃ አቀባዬ ገለፃ ቅመም የተባለው ወጡ ውስጥ የሚጨመረው የቅመም ዓይነት ብቻ ሳይሆን የመመጠን ችሎታም ጭምር ነው። በአጠቃላይ በግጥሙ ውስጥ የተሞገሰችው ሴት የወጥ አሠራር ክህሎትን ለብቻዋ ይዛዋለች፤ የተለየ ተሰጥኦ አላት፤ ተወዳዳሪ ወይም አቻ የላትም የሚል መልዕክት አለው።

በቃል ግጥም /ሐ/ ሁሉም ሴት ምግብ አቅርቦ የሚበላበት ሌማት አለው፤ የዚህች ሴት የምግብ ማቅረቢያ ግን የተለየ ነው የሚል ይዘት አለው። የአመጋገብ ሥርዓት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ያንጸባርቃል። ምግብ ሲቀርብ ለህጻናት ለአባወራ ለአዋቂዎች፣ ወዘተ አቀራረቡና ማቅረቢያው ይለያያል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከሞያ በተጨማሪ ሀብትም ያስፈልጋል። ይህች ሴት በሙያዋም በሀብቷም ትልቅ ደረጃ ላይ ያለች ናት በማለት ግጥሙ የሴትዮዋን ደረጃ ያሳየናል። "አሁን አሁን በገጠር ሳይቀር ምግብ በትሪ የማቅረብ ልማድ በሰፊው ይታያል። ቀደም ባለው ጊዜ ግን እማዎራዎች ቤተሰቡ የሚመገብበት ሌማት መስፋት ይጠበቅባቸው ነበር።" (አታሉ አስሜ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 23/ 2006 ዓ.ም) ሌማቱ በአለላ የተንቆጠቆጠ ጌጠኛ ከሆነ የሴቷን ባለሙያነት የሚመሰክር ተደርጎ ይወሰዳል። ይህች በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰችው ባለሙያ ሴት ግን ከሁሉም ሴቶች የላቀ ሞያና ሀብት ባለቤት ስለሆነች እሷ ቤት የሚበላው በመሶበ ወርቅ ነው የሚል ይዘት አለው።




**ከወ/ሮ አታሉ ጋር ስለ ጨዋታዎቹ ቃለ መጠይቅ ሲደረግ**

*ቃል ግጥም /መ/ ሴቶች እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ በሙያ እየተፎካከሩ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያሳይ ነው። ሞያ የሴትነት መለኪያ ነው። ሁሉም ሴት ባለሞያ መባልን ይፈልጋል፤ በዚህም ምክንያት ሴቶቹ ሞያቸውን ለማስመስከር መሥራት የሚችሉትን ለሌሎች ለማሳየት "ሴቶች ተሰብስበው ሙያ ሲቋጠሩ" በማለት ሸንጎ መቀመጣቸውን በግርምት ይነግረናል። ሙያ ያላት ሴት በድግስ ወቅት እንድታማክር በሁሉም ዘንድ ትጠየቃለች። በባለሙያነቷ ክብር ታገኛለች። በመሆኑም ሁሉም ሴቶች ይህን ክብር ለማግኘት ይፎካከራሉ። ይሁን እንጂ ግጥሙ የምትወደሰውን ሴት በስም በመጥራት "እከሊት አበሉ ትበልጣለች አሉ።" በማለት የሴትዮዋ ችሎታ በሁሉም ተመስክሮላታል የሚል ይዘት አለው። ሴቶች ተሰባስበው የሚችሉትን ሙያ ሲቆጥሩና ሲያስቆጥሩ ስሟ የተጠቀሰው ተሞጋሽ ግን ሁሉም ያመኑላት ባለሙያ ነች። የእሷ ሙያ ከሌሎች ጋር ለመነጻጸር ስለማይቻል ከውድድር ውጭ ነች፤ አንደኛነቱን ደረጃ ሁሉም ሴቶች በስምምነት አጽድቀውላታል የሚል ነው።*

### 5.1.1.2. ለጋስነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ግጥሞች ተወዳሿ ሴት ምን ያህል ለጋስ እንደሆነች የሚገልጹ ናቸው። እንግዳ በልቶ የሚጠግብ የማይመስላት ሁሉም ሰው የሚያውቃት ቸር እንደሆነች ቃል ግጥሞቹ ይናገራሉ።

ሀ  እከሊት አበሉ ምጣድሽ አይውጣ፣
    የጠገበው ሲሄድ የራበው ሲመጣ።

ለ  እከሊት አበሉ ሞሰበ ጎድጓዳ፣
    የራበው ታውቃለች ጎኑ የተጎዳ።

ሐ  አገልግል ሰፍቼ ለማን ላበርክተው፣
    ለእከሊት አበሉ ለምታነጉተው።

መ  ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ መግላሊት፣
    እከሊት አበሉ የሆዴ መድሃኒት።

ቃል ግጥም /ሀ/ የምትወደሰው ሴት እቤትሽ እንግዳ ሄዶ ሳይበላ ሳይጠጣ የማይወጣበት ቸር ሴት ነሽ፣ በመሆኑም እንግዳ መምጣቱን ስለማያቋርጥ ምጣድሽ ሙሉ ቀን ተጥዶ ይዋል የሚል ይዘት አለው። የንፉግ ምድጃ ቀዝቃዛ ነው፤ እጁም አጭር ነው፤ ስለዚህ በንፉግ ደጃፍ የሚያልፍ ሰው የለም። በአንጻሩ ቸር የሆነ ሰው እጁ ሰፊ ነው፤ መስጠት ያስደስተዋል፣ ምድጃው የማይቀዘቅዝ የሞቀ ነው። በመሆኑም ጎብኝው በርካታ ነው። ምጣዱ ከወጣ ወደ ቤቷ የሚጎርፈው እንግዳ የሚስተናገድበት እንጀራ ሊያጣ ይችላል፤ ስለዚህ ምጣዱ ከምድጃው ላይ ፈጽሞ መውጣት የለበትም በማለት የሴትዮዋን ከመጠን ያለፈ ቸርነት በማጋነን የሚገልጽ ነው። ይህች ለጋስ ሴት ከቤቷ የመጣ ሰው መጋበዝ ብቻ ሳይሆን በግብዣው ረክቶና ጠግቦ ይመለሳል በማለት የሚገልፅ ግጥም ነው።

በቃል ግጥም /ለ/ ተወዳሿ ሴት በበረከት የተሞላች ናት። የሞሰቧ እንጀራ ተበልቶ አያልቅም፣ በመሆኑም ቸርነቷ ሰፊ ነው በማለት የሚገልፅ ነው። ሰው ምን ቸር ቢሆን ኪሱ ባዶ ከሆነ ጓዳው ከተራቆተ ይቅርና እንግዳ የራሱንም ልጆች ማስተናገድ አይችልም። ደግነትና ቸርነት በባዶ ቤት ዋጋ የለውም። ድህነት ሞሰብን ያደርቃል፤ በአንጻሩ ሀብትና ቸርነት አንድ ቤት ሲገኙ ሞሰቡ ዘወትር ሙሉ ይሆናል። ቸርነቱ ካለ

ያ ቸርነት ለራበው ሰው ማግኤቱ ነው። ይህ ቃል ግጥም የምትወደሰው ሴት ቸር ከመሆኗም በላይ ሀብቷ የተትረፈረፈ የሁሉም አጉራሽ እንደሆነች የሚገልጽ ነው።

ቃል ግጥሙ "ሀብታም ለሃብታም ይጠቃቀሱ ድሃ ለድሃ ይላቀሱ" ከሚለው ይትባህል በተቃራኒው ቸርነቱ ለልታይ ልታይ ሳይሆን ከልብ በሆነ ለጋስነት ምግቡ ለሚያስፈልጋቸው የሚሰጥ ከስጋ አልፎ ለጽድቅ የሚያበቃ መሆኑን ያመለክታል። "የራበው ታውቃለች ጎኑ የተጎዳ" የሚለው ስንኝ ጎንን ለመጠገን ረሃብን ለማስታገስ፣ አቅመ ቢሶችንና ድኩማንን ለመርዳት የምትተጋ ናት ይለናል።

በቃል ግጥም /ሐ/ ተሞጋሿ ሴት እንጎቻ የምታበላ ቸር በመሆኗ የማስታወሻ ሥጦታ የሚገባት ሰው እንደሆነች የሚገልፅ ነው። እንጎቻ ፍቅርን መግለጫ ነው። እንጎቻ ለማንም አይነጎትም። ከትልቅ እንጀራ ላይ ቆርሶ መስጠት እየተቻለ በትንሹ መጥኖ በራሷ ሙሉ የሆነች ትንሽ እንጀራ ማንጎት ለተጋበገፉ ልጅ ክብርና ፍቅርን ያሳያል። እንጎቻ ማንጎትም ትልቅ እንጀራ መጋገርም የሚወስደው ጊዜና የሚያስፈልገው ማገዶ እኩል ነው። ቸር ሰው ግን ከጉልበቱና ከጊዜው ይበልጥ ፍቅሩ ይበልጥበታል። ቃል ግጥሙ "አገልግል ሰፍቼ ለማን ላበርክተው" በማለት ስጦታ የሚገባው ሰው ማን ነው? በማለት ያጠይቃል። በሁለተኛ ስንኝ ግን መልሱን በማያወላውል ሁኔታ ሥጦታው የሚገባት ፍቅርን ለምታውቅ ክብርን ለምታውቅ አንጉታ ለምታበላ ቸር ሴት መሆን ይገባዋል ይለናል።

በቃል ግጥም /መ/ ተወዳሿ ሴት የምታበላ የምታጠጣ የርሃብ መድሃኒት እንደሆነች የሚገልጽ ነው። በቆየው የአካባቢው ባህል የሆድ ህመም ለያዘው ሰው ቅጠል በመበጠስና ሥር በመማስ የተቀመመ መድሃኒት መስጠቱ የተለመደ ነው። ከዚሁ ነባር ባህል ጋር በማያያዝ በሆድ ህመም ለተመሰለው ረሃብ ይህቺ ሴት መድሃኒቱን እንጀራ እንደምትሰጥ ቅኔያዊ በሆነ መንገድ ተገልጿል። በቃል ግጥሙ "ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ መግላሊት" በማለት መግላሊት ለማውጣት ብዙ ድካምን እንደጠየቀ ምሼ ምሼ የሚለው ቃል ያመለክታል። መግላሊት የድስት ክዳን ነው። የድስት ክዳን ወጡ ውስጥ ቆሻሻም ሆነ ነፍሳት እንዳይገባበት የሚከላከል መከታ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

የቃል ግጥሙ ሁለተኛ ስንኝ "እከሊት አበሉ የሆዴ መድሀኒት" በማለት የምትወደሰው ሴት ሆድ ባዶ ሆኖ ረሃብ እንዳይገባ መከታ በመሆን ፍቱን የረሃብ መድሀኒት የምታበላ መሆኑን ይገልጻል።

#### 5.1.1.3. ውበትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

በእነዚህ ቃል ግጥሞች የምትወደሰው ሴት ቁንጅናዋ ወደር ወይም አቻ የሌላት መሆኑ እየተጋነነ የሚቀርብባቸው ናቸው።

ሀ ሽንብራ ከክቼ ላስጣው ከደጅሽ፣
እከሊት አበሉ ፀሐይ ነው ገላሽ።

ለ በቀይ ማዘያ ቀይ ልጅ አዝላለች፣
እከሊት አበሉ እርሷ ትሆናለች።

ሐ ባልንጀራ ቢሉሽ በቁመት ነወይ፣
እከሊት አበሉ አብሮ አደጌ ነይ።

መ እከሊት ጥርስሽን አንቆርቁሪው በቅል፣
እንዘራዋለን አምሳያው ቢበቅል።

በቃል ግጥም /ሀ/ ተጠቃሿ ወይም ተወዳሿ ሴት ቁንጅናዋ ከፀሃይ ብርሃን የሚስተካከል መሆኑን የሚገልፅ ነው። ተሞጋሿ የፀሃይ ብርሃንን ያህል ሙቀት ያላት አካባቢዋን ሁሉ የምታደምቅ ተደርጎ ተስላለች። ከመረጃ ሰጪዎች መካከል አንዷ የሆኑት ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ "ፀሃይ የቁንጅና የውበት ምሳሌ ናት። ፀሃይ ስትጠራ እንኳ በሴት ፆታ ነው። የምታምር፣ ሁሌም የምትስቅ፣ አካባቢዋን ሁሉ በሙቀቷ የምታደምቅ ናት" ሲሉ አብራርተውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም) እንደ መረጃ አቀባዩ ገለፃ ተወዳሿ ሴት እንደፀሃይ የደመቀች፣ ፍልቅልቅ በመሆኗ ተከክቶ የፀሃይ ብርሃን የሚያስፈልገው ሽንብራ እደጇ ቢሠጣ ሙቀቱ ክኩን ሊያደርቀው ይችላል የሚል መልእክት አለው ብለውኛል።

ቃል ግጥም /ለ/ የምትወደሰው ሴት ዘረ መልካም ናት፤ እሷ ብቻ ሳትሆን የምትወልዳቸውም ልጆች ቀያይ ናቸው። ልጇ ቀይ የሚያምር ማዘያዋም ቀይ የሚያምር ከሆነ እንዲህ የተሟላ ነገር ያላት እሷ ብቻ ናት የሚል ይዘት አለው። እንደ መረጃ ሰጭዬ ወ/ሮ አስረበብ ዘገየ "ቀይ ባገራችን የቁንጅና መለኪያ ነው። አንድን ሴት ቆንጆ ናት ለማለት 'ቅላቷ ግምጃ የመሰለች' ይባላል። ቀይ ሰው አይን ውስጥ ይገባል" ሲሉ ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም) በመሆኑም ተወዳሿ

ማዘያዋ የተመረጠ ቆንጆ፣ ልጇ ቆንጆ ከሆነ ምንም አያጠራጥርም እሷ ስሚ የተጠቀሰችው ቆንጆ ሴት ናት የሚል መልእክት አለው።



ከወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ ጋር ቃለ መጠይቅ ሲደረግ

ቃል ግጥም /ሐ /ተወዳሿ ሴት ባልጀራነቷ ወይም ጓደኝነቷ አብሮ ከማደግ የመጣ ስለሆነ ጥልቀት ያለው ነው የሚል ቃና አለው። ጓደኝነት በውበት ላይ አይመሰረትም። የሰውን ልጅ ዛላውን አይቶ ውስጡን ማወቅ አይቻልም። ምግብም ቢሆን ለአይን ያማረ ሁሉ አይበላም፤ እንደዚሁም ጓደኝነት በማማርና በቁንጅና ሳይሆን በጥልቀት በመተዋወቅ ነው። ጓደኝነቷ በቁመት መመሳሰል ወይም በአካላዊ ተመሳስሎ የሚመሠረት ሳይሆን ሥር በሰደደ መተዋወቅ ወይም አብሮ በማድግ ክፉ ደጉን አብሮ በማሳለፍ የተፈተነ መሆን አለበት የሚል አንድምታ አለው። ባልንጀራነት ተራ ነገር ሳይሆን ምስጢር መካፈልን ልብ ለልብ መተዋወቅን የሚሻ ስለሆነ አንቺ ለኔ ልዩ ነሽ የሚል መልእክት አለው።

በቃል ግጥም /መ/ ደግሞ የተወዳሿ ሴት ጥርስ በእሷ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ተዘርቶ የሚበቅል ከሆነ ክረምት እስከሚደርስ በቅል ውስጥ በጥንቃቄ ይቀመጥ የሚል ይዘት አለው። በአካባቢው ባህል መሰረት ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ለሚቀጥለው የዘር ወቅት

ጥቅም ላይ የሚውለው ምርት የተመረጠና ተበጥሮ ከእንክርዳድና ከልዩ ልዩ የአረም ፍሬ የጸዳ መሆን አለበት። ዘሩ ከተመረጠና ከተበጠረ በኋላ በትልልቅ ቅል በማስገባት ወይም በማንቆርቆር ከእርጥበትና ከተባይ ተጠብቆ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ለምትወደሰው ሴት የጥርሷን ተፈላጊነት ከምርጥ ዘር ጋር በማነጻጸር ልዩ ጥበቃ ወይም እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ተጋኖ ቀርቧል።

በሌላ በኩል ሣቅ የተግባቢነት የደስተኝነት ምልክት ነው። ጥሩ ሰው አያኮርፍም፤ ተደስቶ ሰውን ያስደስታል። የሚስቅ ሰው በአካባቢው ላለ ሰው ብርሃንን ይፈነጥቃል። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ሰው ቢበረክትና ቢበዛ መልካም ነው የሚል ይዘት አለው።

### 5.1.1.4. ወዳጅነትን የሚያወድሱ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

ከዚህ በታች የቀረቡት ቃል ግጥሞች የምትሞገሰው ወይም የምትወደሰው ሴት ተወዳጅነቷ ወደር የሌለው የሰው ፍቅር የታደለች መሆኗን የሚገልጹ ናቸው።

ሀ ሳሩን በሬ በላው ቅጠሉን አንበጣ፣
ምን ሊጎዘጎዝ ነው እከሊት ስትመጣ።

ለ እከሊት አበሉ ባለመስታወት፣
ያየሽ አፈር ይብላ የጠላሽ ይሙት።

ሐ እከሊት አበሉ ነውርሽን እወቂ፣
መቀነቱን ፈተሽ በሀር ታጠቂ።

መ እከሊት አበሉ ነይ እቴ ነይ እቴ፣
የውስጥ ልብሴ ነሽ የላይ መቀነቴ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ተወዳጇ ሴት በእንግድነት ስትመጣ ክብሯን የሚመጥን አቀባበል ሊደረግላት ይገባል፤ ይሁን እንጂ ጐዝጉዘንና አንጥፈን እንዳንጠብቃት ጉዝጓዙ የለም። ስለዚህ ምን እናድርግ ? የሚል ጭንቀት ይዞናል የሚል ይዘት አለው። በተቆረጠ ቀን የሚመጣ እንግዳ ለአቀባበሉ ቅድመ ዝግጅት ይደረግለታል። በተለይ ተወዳጅ እንግዳ ከሆነ ዝግጅቱ ከፍ ያለ ይሆናል። ቃል ግጥሙ ለሚወዱት ሰው ተራ አቀባበል አይደረግም፣ አቀባበሉን ሞቅ ለማድረግ ደግሞ ጮማውን፣ ዶሮውንና ማኛውን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን መቀበያ እልፍኙን ማዘጋጀት ይገባል። ለተወዳጁ ሰው

የሚመጥን መሆን ይገባዋል ይለናል። በመሆኑም ተሞጋሿ ሴት ክብር የሚገባት ተጎዝጉዞና ተነጥፎላት ልትጠበቅ የሚገባት ተወዳጅ መሆኗን ይገልፃል።

ቃል ግጥም /ለ/ ተሞጋሿ ሴት ዘወትር መስታወት ፊት የምትቀርብ ቆንጆና ተወዳጅ ስለሆነች በክፉ ያያትና የጠላት ሰው ሞት ይገባዋል የሚል ይዘት አለው። መረጃ አቀባዬ ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ እንደገለፁልኝ መስታወት የቆንጆ ሴት እቃ ነው። መስታወት ውበትን ለመጠበቅ፣ ጉድፍን ለማስወገድ ጠቃሚ የሴት እቃ በመሆኑ በአካባቢው በሥጦታ የሚበረከት የፍቅር መግለጫም ነው። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 09/ 2006 ዓ.ም) በመሆኑም አሞጋሿ ሴት ይህችን ቆንጆ ሴት 'ከጠላት ይጠብቅሽ፣ ከክፉ አይን ይሰውርሽ' በማለት ወዳጅነቷን ወይም ፍቅሯን ለመግለፅ የምትጠቀምበት ቃል ግጥም ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ አሞጋሿ ለወዳጇ በምክር መልክ የታጠቅሽው መቀነት ካንቺ ክብር ጋር የማይሄድና የማይመጥንሽ ነው የሚል መልእክት ለማስተላለፍ የምትጠቀምበት ግጥም ነው። መቀነት ያገቡ ሴቶች ብቻ የሚታጠቁት ትዳር የመያዝ ምልክት ነው። በሌላ በኩል መቀነት በአካባቢው የጽናት ምልክት ነው። መቀነት ጌጥ ነው። መቀነት ሲርብ ምግብ እስኪገኝ ጠበቅ አድርጎ በመያዝ ድጋፍ ነው። በአካባቢው መቀነት ብዙ ትርጉም አለው። የአካባቢው ሴቶች በህብረቀለማት የተንቆጠቆጠ መቀነት ከጋቢ መግዣ  ዋጋ የበለጠ አውጥተው ሲገዙ ቅሬታ የላቸውም። ግጥሙ ተወዳሿ ሴት ከጥጥ የሚሠራውና ማንኛዋም ተራ ሴት የምትለብሰውን መቀነት መታጠቅ እንደ ነውር የሚቆጠርባት በመሆኑ ከሀር የተሠራ መቀነት ይገባታል የሚል ይዘት አለው።

ቃል ግጥም /መ/ አሞጋሿ ሴት ወዳጇን ከእኔ አትራቂ፣ እህቴ ሆይ ነይልኝ ምክንያቱም አንቺ ለእኔ እንደ ውስጥ ልብሴና መቀነቴ ነሽ የሚል ይዘት አለው። ለባዕድ ሁሉን ነገር 'አትንገር ብለው ቢነግሩት' እሱም መልሶ 'አትንገር' ብሎ ገመናን አደባባይ ማውጣቱ አይቀርም። እህት ግን የእህቷን ገመና ለማንም አሳልፋ አትሰጥም። እንደ መረጃ አቀባዬ ወጣት ሀብታም መብሬ አገላለፅ "የውስጥ ልብስ ገመና ደባቂ ነው። መቀነት ደግሞ ደጋፊ እና ጌጥ ነው። እህትም በችግር ጊዜ ገመናን ደባቂና ደጋፊ እንዲሁም እንደጌጥ የምትቆጠር ናት።" (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 2006 ዓ.ም)

ከላይ በቀረቡት የአበሹቴ ግጥሞች ሴቶች፣ ከእነሱ በተቃራኒ ቡድን የሚገኙ ሴቶችን በጨዋታው መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የሚያወድሱባቸውና የሚያሞግሱባቸው ናቸው። በአበሹቴ ጨዋታ አብዛኛው የጨዋታ ክፍለ ጊዜ በስድብ ግጥሞች የተሞላ ቢሆንም አጀማመሩ ሁሌም በውዳሴ ነው። መረጃ አቀባዩ ወ/ሮ ካሳይቱ እውነቱ "አበሹቴ ጨዋታ በስድብ አይጀመርም፤ በስድብም አይጠናቀቅም መጀመሪያውና መጨረሻው ውዳሴ ነው። ስድቡ በውዳሴ ከተጀመረ በኋላ ነው። መደምደሚያውም ውዳሴ ነው።" በማለት ገልፀውልኛል። (ቃለ መጠይቅ፣ 20/05/2006 ዓ.ም) እንደ መረጃ አቀባዩ አገላለፅ በአበሹቴ ጨዋታዎች የመጀመሪያዎቹ ግጥሞች በማባበል ወደ ስድቡ የሚያንደረድሩ ሲሆኑ የመጨረሻዎቹ ግጥሞች ደግሞ ጨዋታው ከመበተኑ በፊት የተሰዳቢዎቹን የሻከረ ስሜት ማለስለሻ ናቸው። በጨዋታው ማጠናቀቂያ ላይ ከሚከወኑ የቃል ግጥሞች መካከል የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል።

እንዲህ እንዳላችሁ እንዲህ እንዳለን፣
ዓመት ይድገማችሁ ዓመት ይድገመን።

እከሊት አበሉ ነይ እቴ ነይ እቴ፣
የውስጥ ልብሴ ነሽ የላይ መቀነቴ።

በማለት ተራ በተራ ተወዳድሰው የዕለቱ ጨዋታ መጨረሻ ይሆናል። የጨዋታው ስርዓት የአበሹቴ ተጫዋቾች የመጨረሻዎቹን የውዳሴ ግጥሞች እያስታወሱ በመልካም ስሜት ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ያደርጋል።

በአበሹቴ ጨዋታ የውዳሴ ግጥሞች ተወዳሿን ሴት ባላት ነገር ላይ ተመሥርቶ የውዳሴ ግጥሙ ይቀነቀናል እንጂ የሌላትን እንዳላት ተደርጎ አይቀርብም። መረጃ አቀባዩ ወ/ሮ ካሳይቱ እውነቱ ሲገልፁ፣ "ጥቁር ሴት ብትኖር 'የጥቁር ቆንጆ' አጭር ሴት ብትኖር 'እጥር ምጥን ያለች' ይባላል እንጂ ያለመልኳ ወይም ያለቁመቷ ቀይ ነች ወይም ሎጋ ነች እየተባለች አትወደስም" በማለት ያስረዳሉ።

### 5.1.2.በአበሹቴ ጨዋታ የስድብ ቃል ግጥሞች

በአበሹቴ የስድብ ቃል ግጥሞች ተሰዳቢዋ ምን ያህል ሙያ የሌላት ሴት እንደሆነች፣ ምን ያህል አመንዝራ ወይም ሴሰኛ እንደሆነች፣ ምን ያህል የእጅ አመለኛ ወይም ሌባ

እንደሆነች፣ ምን ያህል መልከ ጥፉ እንደሆነች፣ ምን ያህል ሆዳም እንደሆነች፣ ወይም ደግሞ ምን ያህል ጽዳቷን የማትጠብቅ እንደሆነች ጠቋሚ ይዘት ያላቸው ናቸው።

### 5.1.2.1. ሞያ የሌላትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

ከዚህ በታች የቀረቡት የአበሹቴ ግጥሞች የምትሰደበው ሴት ምን ያህል ሞያ የሌላት ሴት እንደሆነች የሚገልፅ ይዘት ያላቸው ናቸው።

ሀ ቀጭን መፍተል እንኳ የሴት ወጉ ነው፣
አንቺ የምታውቂው ገንፎ በገል ነው።

ለ በወር ትፈትላለች አንድ ሽልቃቂ፣
እቴ አልሆነልሽም የሰው ቤት ልቀቂ።

ሐ እከሊት አበሉ የሰራችው ሽሮ፣
ብዙ ሰው ገደለ እንደጠጅ አስክሮ።

መ እከሊት አበሉ የደፋችው በፍታ፣
አይኑን አፈጠጠ ቂሶቹን ሊማታ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ወንዶችን ማማለልም ሆነ ቀጭን መፍተል የቆንጆና የባለሙያ ሴት ወግ ነው፤ አንቺ ግን ሙያ ቢስ ነሽ የሚል ይዘት እናገኛለን። ትዳር ከያዘች ሴት ብዙ ነገር ይጠበቃል። የቤተሰብ ሃላፊ መሆን ቀላል አይደለም። ለራሷ ቀሚስ ለባሏ ጋቢ ፈትላ ማሠራት የቆየ ባህል ነው። ይሁን እንጂ በቃል ግጥሙ ቀጭን መፍተሉ ቀርቶ "አንቺ የምታውቂው ገንፎ በገል ነው" በማለት ተሰዳቢዋ መፍተልም ሆነ ሌላ የባልትና ሥራ የማትችል ከገንፎ አቅም በወጉ ሠርታ ማሳየት የተሳናት መሆኗን ያሳያል። ገል ስባሪ ሸክላ በመሆኑ ከእሳት መጫሪያነት ውጪ አገልግሎት የለውም። ይህች ሴት ግን ሙያ ስለሌላት እንጀራ ጋግሮ ወጥ ሠርቶ መብላት ይቅርና ጸዳ ያለ በወጉ የተሠራ ገንፎ እንኳን እንደማትችል ይተቻል።

በቃል ግጥም /ለ/ ተሰዳቢዋ ሴት ሙያ የሌላት በመሆኑ በአንድ ወር ውስጥ ከአንድ ልቃቂት በላይ ጠብ ሊልላት የማይችል በመሆኑ በትዳር ልትቆይ የማይገባት ናት የሚል ይዘት አለው። ትዳር ታታሪነትን ይጠይቃል። ሦስት ጉልቻ በትጋት የሚሠምር

ልፋትን የሚጠይቅ ነው። በቃል ግጥሙ በሙያዋ ውጤታማ ያልሆነች ሴት ለጋብቻ ብቁ አይደለችም፤ ብቃት ላላት ሴት መልቀቅ አለባት ይላል። ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ ይህ ቃል ግጥም በጣውንቶች መካከል ያለ የቅናት ስሜት መግለጫ ነው። ባሏን የቀማቻት ሴት ከሷ የተሻለ ሙያ ስለሌላት ቤቴን ልቀቂ የሚል መልእክት ለማስተላለፍ የሚገጠም ነው በማለት ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ 09/05/2006 ዓ.ም) እንደ ወ/ሮ ወርጫለቁ ገለፃ ባሏን መታረቅ የምትፈልግ ሴት አዲሲቷን ሴት ከቤቴ ውጪ ብላ ሃሳቧን የምትገልፅበት መንገድ ነው።

በቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢዋ ሴት ሞያ የሌላት፣ በሴት ሞያ የመጨረሻ ቀላል የሆነውን ሽሮ ማፍላት እንኳ የማትችል ረኸጥ ናት የሚል ይዘት አለው። ሽሮ እንጀራ ባለበት ቦታ ሁሉ የማይጠፋ በአብዛኛው ቤት ውስጥ ቤተኛ የሆነ ምግብ ነው። ቅመምና ቅቤው የሽሮውን ዓይነት ያለያየው ይሆናል እንጂ እንጀራ ባለበት የማይጠፋ ሁሉም የሚሠራው ቀመሩ ቀላል ማባያ ነው። በቃል ግጥሙ የምትወቀሰው ሴት ግን ወጥ ብላ ያቀረበችው ሽሮ የብዙ ሰዎችን ጤና አቃውሏል የሚል መልእክት ይዟል። ሽሮ ማንም ሊሠራው የሚችል ተራ ምግብ ሆኖ ሳለ ይህች ሴት ግን ይህንን እንኳ በአግባቡ መሥራት የሚያስችል ሞያ የላትም ለማለት የተገጠመ ቃል ግጥም ነው።

በቃል ግጥም /መ/ ይህች ሞያ የሌላት ሴት ያዘጋጀችው ድፎ ወይም በፍታ ላይ አልፎ አልፎ በወጉ ያልተፈጨ ስንዴ ፈጦ ይታያል የሚል መልእክት ይዟል። ስንዴ ስለተገኘ ዳቦ አይጋገርም። ስንዴውን በወጉ ከእንክርዳዱ ማጽዳት፣ አድቅቆ መፍጨት ወይም ማስፈጨት፣ አሽቶ ማቡካት፣ ኩፍ ሲል መጋገርና እሳቱን በመመጠን ጊዜውን ጠብቆ ማውጣት ያስፈልጋል። ሞያ የሌላት ወይም የተዘናጋች ሴት ከላይ ከተገለጹት ሂደቶች አንዱን ካጎደለች ድፎው የተበላሸ መሆኑ አይቀርም። ቀደም ባለው ጊዜ በየመንደሩ ወፍጮ ስላልነበረ የገጠር ሴቶች እቤታቸው ውስጥ በሚያዘጋጁት የድንጋይ ወፍጮ ለቤተሰባቸው ቀለብ የሚሆን እህል መፍጨት ይጠበቅባቸው ነበር። በወቅቱ አልሞና አድቅቆ መፍጨት እንዲሁም የላመውን ዱቄት በወንፊት ማጣራት ከሴቶች የሚጠበቅ አንዱ የሞያ መመዘኛ ነበር። ከሸርክት ወይም በአግባቡ ካልተፈጨ እህል ምግብ የምታዘጋጅ ሴት ሞያቢስ ተብላ ትወገዛለች፣ ትናቃለች። በግጥሙ የተጠቀሰችው ሴት ለድፎ ዳቦ የሚሆን በአግባቡ የተዘጋጀ ዱቄት ስለሌላት ወይም በወንፊት የማጣራት ሥራ ባለመስራቷ ምክንያት የጋገረችው በፍታ ስንዴው እላዩ ላይ ፈጦ የሚታይባት በማለት የሚተች ቃል ግጥም ነው።

### 5.1.2.2. አመንዝራነትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

ከታች የተዘረዘሩት ቃል ግጥሞች ሲሰኙነት፣ አመንዝራነት ወራዳ ተግባር መሆኑን የሚገልጹ ናቸው።

ሀ  አሻሻ ወልሻሻ ደባደቦ ከንፈር፣
    አንቺም ታውቂያለሽ ወይ ና ብሎ ማሳፈር።

ለ  እንዲህ ወደዚታች የቃርሚያ ልክስክስ፣
    እከሊት አበሉ የሁሉም ፍርክስ።

ሐ  እከሊት አበሉ ቤቷ ፈርሶባታል፣
    የመጣ የሄደው ይማግድባታል።

መ  ጓደኞችሽ አስር አንቺ አስራአንደኛ፣
    አንቺ የኩሬ ውሃ የሁሉም መዋኛ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ከመልክ መልክ የለሽ፣ ከቅርፅ ቅርፅ የለሽ፣ ከኩራት ኩራት የለሽ የጠየቀሽን ሁሉ እሺ በማለት የምታመነዝሪ ነሽ የሚል ይዘት አለው። አቶ ተሾመ ካሴ ይህ ግጥም ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄዬ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውኛል። "ሴት ልጅ ባገራችን ባህል የፈለገው ያህል የምትመኘው ወይም በልቧ የምትሻው ወንድ እንኳ ቢጠይቃት ባንድ ጊዜ እሺ አትልም። ወንዱም ቢሆን ደጋግሞ ሳይጠይቅ እሺ የምትለውን ሴት ይንቃታል" በማለት ሴት ልጅ የወንድን ልብ ሰቅላና አማልላ ደጋግሞ እንዲጠይቅ በማድረግ ተወዳጅነቷን ከፍ ማድረግ እንደሚጠበቅባት አስረድተውኛል። (ቃለ መጠይቅ ጥር 19/2006ዓ.ም) ሴቶች ለራሳቸው ያላቸው ግምት ከፍ ያለ ካልሆነ፣ በቀላሉ የሚገኙ ከሆነ በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውም ግምት ዝቅ ይላል። ስለዚህ ሴት ልጅ ለጠየቃት ሁሉ እሺ አትልም። ልቧ የፈቀደው ወንድ ቢጠይቃት እንኳ በመጀመሪያው ጥያቄ እሺ ከምትል እስከመጨረሻው ብታጣው ትመርጣለች። በዚህም በህብረተሰቡ ዘንድ የምታገኘው ክብር ከፍተኛ ነው።

በቃል ግጥም /ለ/ ሰብል ከታጨደ በኋላ በማሳው ላይ የሚቀረው የተልከሰከሰ ቃርሚያ በመሆኑ ማንም የሚለቅመው ባለቤቱ ንቆ የተወው እህል እንደሆነ ሁሉ ተጠቃሿም ሴት ለጠያቃት ማንኛውም ወንድ ሁሉ የምትሄድ ክብር የሌላት ናት የሚል ይዘት አለው።

ከሁሉም ጋር በማመንዘሯ በህብረተሰቡ የተናቀች ከቃርሚያ ጋር የምትነፃፀር ርካሽ ተደርጋ ትወሰዳለች። በአካባቢው ባህል መሰረት ሰብል ከታጨደና ከተከመረ በኋላ በማሳው ላይ ተዝረክርኮ የሚቀረውን ቃርሚያ ባለቤቱ ንቆ እንደተወው ስለሚቆጠር ማንም ሰው ሰብስቦ ሊወስደው ይችላል። ይህችም ሴት በአመንዝራነቷ ምክንያት ከቃርሚያ ጋር ተነጻጽራ በባለቤቷ ክብር የሌላት የማንም የሆነች ተደርጋ ቀርባለች።

ቃል ግጥም /ሐ/ ቅኔያዊ ግጥም ሲሆን ተሰዳቢዋ ሴት ከቤት ፍራሽ እንጨት ጋር ተመሳስላ ተስላለች። በቃል ግጥሙ "እከሊት አበሉ ቤቷ ፈርሶባታል" የሚለው ሁለት ትርጉም አለው። አንዱ መኖሪያ ቤቷ ፈረሰባት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ትዳሯ ፈረሰባት፤ ባሏን ፈታለች የሚል ትርጉም አለው። ትዳሩን የፈታ በአካባቢው ባህል መሠረት "ጋለሞታ ሆናለች" እየተባለች ትዳር ላይ እንደነበረችበት ጊዜ ታፍራና ተከብራ የመኖር እድሏ ይቀንሳል። በመሆኑም የቤት ፍራሽ እንጨትን ማንም ያገኘው ሰው ለማገዶ እንደሚጠቀምበት ሁሉ ይህች ሴትም አላፊ አግዳሚው ለወሲብ ይጠቀምባታል የሚል ይዘት አለው። ሴትየዋ ሰው የማትመርጥ ከአላፊ አግዳሚው ጋር የምታመነዝር ርካሽ ሴት ናት የሚል መልእክት አለው።

ቃል ግጥም /መ/ ወዳጆችሽ በርካታ ናቸው፤ አንቺ ምርጫ የሌለሽ ከሁሉም ጋር የምታመነዝሪ ሴት ነሽ የሚል ይዘት አለው። ሴትየዋ ወይም በአበሹቴ ጨዋታ የምትሰደበው እንስት ሁሉም ከሚንቦጫርቅበት የኩሬ ውሃ ጋር ተነፃፅራ ቀርባለች። የኩሬ ውሃ ንጽህናው የተጓደለ እንደምንጭ ውሃ ክብር የሌለው ደረጃው ዝቅ ያለ ነው። የምንጭ ውሃ ለመጠጥና ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግል ተጠቃሚውም ተጠንቅቆ የሚይዘው ልጆችና ከብቶች እንዳያደፈርሱት የሚጠበቅ ነው። በአንጻሩ ግን የኩሬ ውሃ እረኛውም ከብቱም የሚንቦጫረቅበት ክብሩ ዝቅ ያለ ነው። በቃል ግጥሙ የምትሰደበው ሴትም ክብር የለሽም ከተገኘው ወንድ ጋር ዝሙት የምትፈፅሚ ነሽ ይላል። መምረጥ ስለማታውቂ ሁሉንም ታስተናግጃለሽ፤ የሴት ወጉ የሌለሽ ርካሽ ነሽ የሚል መልዕክት ያስተላልፋል።

ከላይ የቀረቡት የአበሹቴ ግጥሞች በሙሉ አመንዝራ ሴት ክብር የሌላት፣ በህብረተሰቡ ዘንድ የተናቀች መሆኗን የሚያመለክቱ ናቸው። "ሴት ልጅ በህብረተሰቡ የተከበረች እንድትሆን ከአመንዝራነት የራቀች መሆን ይጠበቅባታል። ራሷን የምትጠብቅ ጨዋ ሆና መገኘት አለባት።" መራጊያው ከቤ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 19 ቀን 2006 ዓ.ም)

### 5.1.2.3. ሌብነትን /ሌባን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የቀረቡት የአበሹቴ ግጥሞች ሌቦችን ለመስደብ የሚቀነቀኑ ናቸው።

ሀ ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ ገለባ፣
 እከሊት አበሉ የሀገሩ ሌባ።

ለ እከሌ አበሉ ቤት ያለች ቀይ ውሻ፣
 አላስቀምጥ አለች ዱቄት በጉስጉሻ።

ሐ እጇን እሰሩልኝ በዝንጀሮ ጭራ፣
 አላስቀምጥ አለች የሞሰብ እንጀራ።

መ ኸረ ዝጉ ዝጉ ፣ ዝጉ በማረሻ፣
 አሁን ትመጣለች የእከሌ ውሻ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ገለባ ምድር ላይ ወይም መሬት ላይ እንጂ ከመሬት ውስጥ አይገኝም፤ እኔ ግን መሬት ውስጥ ቆፍሬ የተደበቀ ገለባ እንዳገኘሁ ሁሉ ተጠቃሿ ሴትም ሌባ መሆኗን አረጋግጫለሁ የሚል ይዘት አለው። ሌብነት አሳፋሪ ተግባር ነው። ሌባ የሚሰርቀው ጨለማ ለብሶ ወይም ጭር ያለ ሰዓት ጠብቆ በመሆኑ ማንነቱን መለየት አስቸጋሪ ነው። መሬት ውስጥ የተደበቀን ገለባ የመፈለግ ያህል ከፍተኛ ጥረት አድርጌ በስም የተጠራችው ሴት ሌባ መሆኗን አረጋግጫለሁ። በመሆኑም ተሰዳቢዋ በዚህ አገር ተወዳዳሪ የሌላት ሌባ መሆኗን ደርሼበታለሁ በማለት የሌብነትን አሳፋሪነት የሚገልጽ ቃል ግጥም ነው።

በቃል ግጥም /ለ/ ተሰዳቢዋ ሴት በአባቷ ወይም በባሏ ውሻ ተመስላ ቀርባለች። የባሏን ወይም የአባቷን ውሻ በማስመሰል ሌብነቷን የሚያጋልጥ ነው። በማህበረሰቡ ውሻ የሌብነት ተምሳሌት ነች። " እከሌ እንደውሻ ልክስክስ ነው" ከተባለ አንድም ሌባነው፤ አንድም አመንዝራ ነው። በቃል ግጥሙ "እከሌ አበሉ ቤት ያለች ቀይ ውሻ" በማለት እከሌ ተብሎ የተጠራው ሰው የተሰዳቢዋ ባል ወይም አባት በመሆኑ ቀይ ውሻ የተባለችው እሷ እራሷ በውሻ ተመስላ የቀረበችበት ነው። ውሻ ሰው የሌለበትና በአግባቡ ያልተዘጋ ቤት ካገኘች ትሰርቃለች። ውሻዋ ከዱቄት እቃ ገብታ ዱቄቱን

እንደምትልስ ሁሉ ይህቺ ሴትም ዱቄት ትሠርቃለች የሚል ይዘት አለው። በጉስጉሻ ወይም በዱቄት እቃ የተቀመጠን ዱቄት የምትሠርቅ ሌባ ናት ተጠንቀቋት የሚል ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢዋ የመሶብ እንጀራ የምትሰርቅ ልክስክስ ሌባ ስለሆነች እጇን በጠንካራ ገመድ እሰሯት የሚል ይዘት አለው። የለመደ ሌባ አይመርጥም። በተለይ ሌባው ጎረቤት ከሆነ ሲወጣም ሲገባም እጁ የገባለትን እቃ አንጠልጥሎ ይሄዳል። በቃል ግጥሙ "እጇን እሰሩልኝ በዝንጀሮ ጭራ" በማለት የምትሰደበው ሴት በምክርና በመጠበቅ ሌብነቷን ማስታገስ የማይቻል መሆኗን የሚያሳይ ነው። የእጅ አመል ያለባትን ሰው ጠብቆ ማዳን አስቸጋሪ ስለሆነ ከዝንጀሮ ፀጉር በተሠራ ገመድ እጇን ማሠር ሳይሻል አይቀርም ይላል።

ቃል ግጥም /መ/ ተሰዳቢዋ የባሏን ወይም የአባቷን ውሻ ተመስላ ቀርባለች። በራችሁን አጥብቃችሁ ዝጉ አለበለዚያ ይህች ሴት እቤታችሁ ገብታ ሠርቃችሁ ትሄዳለች የሚል መልእክት አለው። አደገኛን ሌባ ተራ በር አያድነውም። አጥብቆ መዝጋት ያውም በብረት ማረሻ ተገቢ ነው። ሌብነት መጥፎ ልማድ ነው። ልምዱ ያለው ሰው አዘናግቶ መስረቁ አይቀርም። በቃል ግጥሙ ሁለተኛ ስንኝ "አሁን ትመጣለች የእከሌ ውሻ" በማለት ሌባ ሲያዘናጋ ይዘገያል እንጂ ለመስረቅ መምጣቱ አይቀርም። ስለዚህ ግቢን አጥሮ በርን አጥብቆ መጠበቅ ያዋጣል የሚል ነው።

ከላይ የቀረቡት ሌብነትን ወይም የእጅ አመልን የሚገልጹ ቃል ግጥሞች ሌብነት ፀያፍ እንደሆነ በሌብነት የምትጠረጠር ሴት በህብረተሰቡ ዘንድ የተናቀች መሆኗን የሚያሳዩ ናቸው።

### 5.1.2.4. መልከ ጥፉነትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

እነዚህ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች መልክና ቁመናን በተመለከተ የተቃራኒ ቡድን ሴቶችን ለመሳደብ የሚያገለግሉ ናቸው።

ሀ ሰደበችኝ አሉ ምን ልመልስላት፣
የወይራ ግንዲላ የሰው ቅርጽ የሌላት።

ለ	በሙጃሌ እግሯ አንዴ ብትረግጠኝ፣
ይኸው ሦስት አመቴ እያንቀጠቀጠኝ።

መ	እከሊት አበሉ ሰጋጋ ሰጋጋ፣
አንቺንስ አንስቶ የቤተስኪያን ሳጋ።

ሠ	የእከሊት ጸጉር ሀይማኖተኛ ነው፣
ከፍ አይል ዝቅ አይል እዛው አቦታው ነው።

በቃል ግጥም /ሀ/ ተሰዳቢዋ መሰደብ በማይገባኝ ሴት ተሰደብኩ፣ የሰደበችኝ ሴት ግንድ የምትመስል ቅርፀ ቢስ የሆነች ሴት ናት። ለእሷ የሚመጥን መልስ የለኝም የሚል ይዘት አለው። ስድብ ነውር ነው። ሰው ከምንም ተነስቶ ሰውን አይሰድብም። ለመስደብ ቢያስፈልግ እንኳ በቂ ምክንያት ሊኖር ይገባል። በቃል ግጥሙ "ሰደበችኝ አሉ ምን ልመልስላት" በማለት ስድብ ተገቢ አይደለም ግን ዝም ማለትም ፈሪ ስለሚያሰኝ ምን ዓይነት መልስ ልስጥ? በሚል ምክር በመጠየቅ መልሱን ከሌላ ሰው ሳይቀበል በሁለተኛው ስንኝ "የወይራ ግንዲላ የሰው ቅርጽ የሌላት" በማለት የተሰዳቢዋን መልከ ጥፉነት ይናገራል። በግጥሙ ተሰዳቢዋ ይበልጥ ያንገበገባት ሰዳቢዋ የእሷ ተፎካካሪ ልትሆን የማትችል መልከ ጥፉ መሆኗ ነው። በምትበልጣት ሴት ወይም ከሷ የበለጠች ቆንጆ ሴት ብትሰድባት ኖሮ ይህንንም ያህል የሚቆጭ አልነበረም የሚል መልእክት አለው።

በቃል ግጥም /ለ/ ቅርፅ በሌለው ሙጃሌ ባንሻፈፈው እግሯ ረግጣኝ ህመሙ ለረጅም ጊዜ ይሰማኛል። የምትሰደበው ሴት እግሯ ቅርፀ ቢስና ሸፋፋ ነው የሚል ይዘት አለው። በአካባቢው ማህበረሰብ ከሴት ልጅ ውበት መለኪያ አንዱ እግር ነው። ተሰዳቢዋ ተረከዘ ሎሚ የምትባል ሳትሆን በቅጡ መራመድ የማይችል ሸፋፋ እግር ያላት መሆኗ ሳያንስ እግሯን በአግባቡ አንስታ መራመድ የማትችል በመሆኗ ከፊት ለፊት ያለን ሰው እየረጋገጠች የምትሄድ እንደሆነች ቃል ግጥሙ ይገልጻል። በዚህም ምክንያት ተሳዳቢዋ የመረገጥ መጥፎ አጋጣሚ ደርሶባት የእርግጫው ህመም ሶስት ዓመት ሙሉ እያንቀጠቀጣት መሆኑን በመግለጽ የምትሰደበው ሴት እግረ መልካም አለመሆኗ በግነት የተገለጸበት ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢዋ ቀውላላ ቁመት ያላት፣ ሲያዩዋት የማታምር በመሆኗ እንደ አጣና እንጨት ከቤት መሥሪያነት ውጭ ሌላ አገልግሎት የላትም የሚል ነው። ረጅም እንጨት ለቤት መሥሪያ ሳጋ እንደሚያገለግል ሁሉ ይህች ቀውላላ ሴትም ከቤተክርስቲያን መሥሪያ እንጨት የተለየች አይደለችም። አቶ ተሾመ ካሴ የተባሉት መረጃ አቀባዬ "ሴት ከባሏ ቁመት የበለጠች ከሆነ ለመልስም ሆነ ለሌላ ጉዳይ አብረው ሲሄዱ ሰዎች ሁለቱን ይቀልዱባቸዋል። 'የሴት ረጅም የማቅ ውኻውኻም እምብዛም አያስጐመኻም' " ይባላል ከነተረቱ ሲሉ ገልፀውልኛል። (ቃለ መጠይቅ 20/05/2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /መ/ ሀይማኖተኛ ሰው የሚያጋጥመው ማንኛውም ችግር ያለምንም መልመጥመጥ በጽናት የመቆየት ብቃት አለው። በጥቅም ወይም በፍርሃት ከሚያምንበት ጉዳይ ፈቀቅ አይልም። ቃል ግጥሙም ሀይማኖተኛ ሰው በግብሩም ሆነ በቃሉ የማይናወጥ አቋም እንዳለው ሁሉ የተሰዳቢዋ ሴት ፀጉርም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ የማያሳይ ባለበት ፀንቶ የሚኖር ነው የሚል ይዘት አለው። የዚች ሴት ፀጉር ከአመት አመት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ የማይታይበት ፈፅሞ የማያድግ ነው። የሴት ልጅ ውበት መገለጫ ከሆኑት አንዱ ጐድሎባታል የሚል መልእክት አለው።

### 5.1.2.5. የጽዳት ጉድለትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

እነዚህ የአበሹቴ የቃል ግጥሞች የምትሰደበው ሴት ጽዳት የጎደላት የራሷንና የአካባቢዋን ንጽህና የማትጠብቅ መሆኗን የሚገልጹ ናቸው።

ሀ ንፍጧን አንጠልጥላ ከደረቷ ላይ፣
ባለድሪ መስቀል ማድረጓ ነወይ?

ለ አከሊት አበሉ ባገባች በወሯ፣
ብሄድ በደጃፏ አንሻተተኝ አሯ።

ሐ እከሊት አበሉ ያይኔ ኩል ያይኔ ኩል፣
የወገቧ ቅማል ዘጠኝ ቁና ተኩል።

መ የእከሊትን ቀሚስ ማንም አይዋሰው፣
የቂጧ ጠፈጠፍ እያረሰረሰው።

ቃል ግጥም /ሀ/ የግል ንፅህናዋን የማትጠበቅ ንፍጧን እንኳ በወጉ ማጽዳት የማትችል ገልቱ ሴት ናት የሚል ነው። ንፍጥ አንድም ልጅነትን አንድም ያለ መብሰል ያሳያል። አድጋለች ትልቅ ሰው ሆናለች ስለዚህ እራሷን ችላ ለመኖር ብቁ ናት በምትባልበት ዕድሜዋ በደረቷ ላይ ንፍጥ መታየቱ አሳፋሪ መሆኑን የሚገልጽነው። ተሰዳቢዋ ንፍጧን እንደ ጌጥ ደረቷ ላይ ለጥፋ መሣቂያ ሆናለች ይለናል።

በአካባቢው ለወግ ማዕረግ የደረሰች እድሜዋ ለጋብቻ ደርሷል ተብላ የምትገመት ሴት ከምታሳያቸው ድርጊቶች መካከል አንዱ ደረት ላይ ድሪ የተባለ ጌጥ ማድረግ ነው። ድሪው ክርስቲያን መሆኗን "መናገር" የሚችል በላዩ ላይ ከብር ወይም ከሌላ ቁስ የተሠራ መስቀል ያለው ሊሆን ይችላል። የምትሰደበው ሴት ግን ይህ ሁሉ ለእሷ የሚገባት አይደለም፤ የልጅነት ባህርይዋ ገና ያለቀቃት ናት ይላል ቃል ግጥሙ።

ቃል ግጥም /ለ/ ተሰዳቢዋ ሴት አዲስ ባል አግብታ በሙሽርነቷ ዘመን እንኳ ጽዳቷን የማትጠብቅ ናት የሚል ይዘት ያለው ግጥም ነው። ሙሽርነት የአዲስ ህይወት ጅማሮ ነው። በአዲስ ህይወት አዲስ ተስፋ የሚታይበት። አዲሱ የህይወት መስመር ለሥራ የሚያነሳሳ መንፈስን የሚያስደስት ሆኖ ሳለ የምትሰደበው ሴት ግን በተቃራኒው በሥንፍና የታሰረች የራሷን ነውር እንኳን ራቅ አድርጋ መጣል ያቃታት ናት በማለት ቃል ግጥሙ ይነግረናል። ከመረጃ አቀባዮቹ አንዱ የሆኑት ወ/ሮ እንዳሻሽ ስጦታው ስለ ቃል ግጥሙ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውኛል። "ባል ያገባች ሴት የባሏ ቤተሰቦችና ባሏ እንዳይታዘቧት የምትሠራውን ሥራ ሁሉ የምትከውነው በጥንቃቄ ነው። እንደተሰዳቢዋ ዓይነት ስለ ጽዳት እውቀት የሌላት ሴት ግን በሙሽርነቷ እንኳ ነውሯን አትሸፍንም" በማለት በህብረተሰቡ ጽዳቱን የማይጠብቅ ሰው የሚሰደብ መሆኑን ከግጥሙ በመነሳት ገልጸዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ 20/05/2006 ዓ.ም)

በቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢዋ የግል ንፅህናዋን የማትጠብቅ ማለትም ልብሷንና ገላዋን የማትታጠብ በመሆኗ በወገቧ ዙሪያ የሚርመሰመሰው ቅማል ስፍር ቁጥር የለውም የሚል ይዘት አለው። ኩል የዓይን ጌጥ ነው። የግጥሙ ተናጋሪ "ያይኔ ኩል ያይኔ ኩል" ስትል ተሰዳቢዋን በቅርብ የምታውቃትና ወዳጅነት ያላት መሆኑን ለማሳየት ነው። "ከአብሮ አደግህ ጋር አትሰደድ" እንደሚባለው የሴትዮዋን ገመና በቅርብ ሆኜ

አውቀዋለሁ፣ እሷ ከንጽህና ጉድለት የተነሣ በቁና ሊሠፈር የሚችል የቅማል ሠራዊት እንደወረራት አውቃለሁ የሚል ነው ።

በቃል ግጥም /መ/ ተሰዳቢዋ ሴት የግል ንፅህናዋን የማትጠበቅ በመሆኑ የሷን ልብስ ተውሶ ለመልበስ የሚፈልግ ሰው የለም የሚል ይዘት አለው። መዋዋስ መበዳደር የተለመደ በማህበራዊ ኑሯችን የየዕለት ተግባር ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ ከጎረቤት ዕቃ መዋዋስ፣ ገንዘብም ሆነ እህል መበዳደር ከዚያም ባለፈ ገበያ ወይም ለግብዣ ጥሪ ልብስ መዋዋስ የተለመደ ጥንትም አሁንም ያለ ነው። ቃል ግጥሙ በዚህ ልማድ ውስጥ የምትሰደበው ሴት ለዚህ የመዋዋስ ተግባር ማህበረሰቡ እንደማያሳትፋት ማንም ሰው ቢቸግረው እሷ ጋ ለመሄድ እንደማይፈልግ ይገልጻል። "ለሠርግ፣ ለበዓል ወይም ገበያ ለመውጣት ሴቶች፣ ቀሚስ፣ ነጠላ ወይም ጫማ ይዋዋሳሉ። በተለይ በሚቀራረቡ ጓደኛሞች መካከል የተለመደ ነው። ግን ጽዳቱን ያልጠበቀ ልብስ የሚዋሰው አይኖርም" በማለት ወ/ሮ ሙሉ ሰማኝ ገልፃልኛለች። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር፣ 20 ቀን 2006 ዓ.ም) የአበሹቴ ጨዋታ ጽዳታቸውን ለማይጠብቁ ሴቶች ምክር የሚሰጥበት ነው በማለት አስረድተውኛል።

### 5.1.2.6. ሆዳምነትን የሚሰድቡ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች

እነዚህ የአበሹቴ የቃል ግጥሞች የምትሰደበው ሴት ወይም የሚሰደቡት ሴቶች በልተው የማይጠግቡ ሆዳሞች መሆናቸውን የሚገልጹ ናቸው። በአካባቢው ባህል ሴት ልጅ "ምራቋ ወፍራም ነው፡" የሚለው አባባል ለብዙ ዘመናት ሲተረት የኖረ በመሆኑ የተገኘውን ሁሉ የምትበላ ሴት ለስድብ ትዳረጋለች።

ሀ በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣
አረገዝኩኝ አለች ቀፈቷን ብታይ።

ለ በላች በላችና ዱባና ድንች፣
አረገዝኩኝ አለች አሯ ቢከማች።

ሐ እንዲህ ወደ እዚታች አህያ ሞታለች፣
ያችው እከሊት ልትግጥ ወርዳለች።

መ    ከበተስኪያን ጓሮ ያለች ደረቅ ዋንዛ፣
ብትበላ አትጠረቃ ብትቀባ አትወዛ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ተሰዳቢዋ የወጡን እፍታ ወይም ቅባት የበዛበትን የወጡን ክፍል በብዛት በመብላቷ የተነሳ ቦርጪ ሲገፋ ጊዜ አረገዝኩ እያለች ታወራለች የሚል ይዘት አለው። ወጥ መሥራት በባህሉ ለሴቶች ብቻ የተሠጠ ተደርጎ ይታያል። የተሠራውን ወጥ ግን አባወራ ሳይመጣ ቢርባት እንኳ መብላት እንደነውር ይቆጠራል። ወ/ሮ ካሳይቱ እውነቱ የተባሉት መረጃ አቀባዬ "በአካባቢያችን ሴት ልጅ ብቻዋን አትበላም። እፍታውን በልታ የምትጠብቅ ሴት ሆዳም ተብላ ትሰደባለች" በማለት አስረድተውኛል። (ቃለ መጠይቅ 20/05/2006 ዓ.ም) በመሆኑም ቃል ግጥሙ የምትሰደበው ሴት ባህሉን የጣሰች ከበሏ ጋር መብላት ሲገባት ብቻዋን የምትበላ ሆዳም ናት የሚል ነው።

በቃል ግጥም /ለ/ ተሰዳቢዋ ዱባውንም ድንቹንም የተገኘውን ሁሉ አግበስብሳ እየበላች ሆዱ ሲሰፋ ጊዜ አረገዝኩኝ ትላለች የሚል ይዘት አለው። በማህበረሰቡ ዱባና ድንች የድሃ ምግቦች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። አልፎ አልፎ ካልተበሉ ለውፍረት የሚዳርጉ ምግቦች ናቸው ተብሎ ይገመታል። ቃል ግጥሙ የተገኘው ነገር ሁሉ መበላት የለበትም። በተለይ ሴት ልጅ መጥና መመገብ አለባት የሚል መልእክት አለው። ዱባና ድንች በአንፃራዊነት በአካባቢው እንደልብ የሚገኙ የምግብ ዓይነቶች በመሆናቸው ተሰዳቢዋም አጠገቧ የተገኘውን ሁሉ በማግበስበሷ ምክንያት ድርጊቷ ተገቢ አለመሆኑን የሚገልፅ ግጥም ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢዋ ሴት ከሆዳምነቷ የተነሳ የምግብ ምርጫ የላትም የሚል ይዘት አለው። አህያ ሲሞት የጅብ እራት ይሆናል። ጅብ ደግሞ የሆዳምነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። እንደ ወ/ሮ ውርጫለቁ ባዬ ገለፃ  "በባህላችን አህያ እንደማይበላ ይታወቃል። ነገር ግን በህብረተሰቡ ዘንድ ሆዳም ሰው በጅብ ይመሠላል። በመሆኑም በአበሹቴ ጨዋታ ሆዳም የሆነች ሴት በጅብ መስሎ መሣደብ የተለመደ ነው።" በማለት የግጥሙን ሃሳብ ያስረዳሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /መ/ ተሳዳቢዋ ሴት የፈለገውን ያህል ብትበላም ብትጠጣም ወዝም ሆነ ውፍረት የላትም የሚል ይዘት አለው። ቤተ ክርስቲያን ጓሮ የሚገኝ ዛፍ ቅጠሉ

አይመለመልም፣ ግንዱ አይቆረጥም፤ በመሆኑም የተመቸውና ያለመለመ ነው። ይሁን እንጂ ምንም ያህል ምቾት ቢኖርም ከጥቅጥቅ ደን ውስጥ የደረቀና የገረጣ ዛፍ እንደማይጠፋ ሁሉ በሰዎችም መካከል ቢሆን የፈለገ ያህል ምግብ ቢያግበሰብስ ወዝ የሌለው ሰው ሊኖር  ይችላል። ሴትየዋም በቃል ግጥሙ ቤተክርስቲያን ጓሮ ከምትገኝ ደረቅ ዋንዛ ጋር ተነፃፅራ ቀርባለች፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ የማታድግ የደረቀች ዋንዛ የሴትዬዋ አምሳያ ሆና በማንፀሪያነት ማሣያ ሆናለች።

## 5.2 የኸኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ትንተና

የኸኸይቦሌ ቃል ግጥሞች ሴቶችን የሚያወድሱ፣ ወንዶችን በማወደስም በመሳደብም የሚቀነቀኑ ናቸው። በኸኸይቦሌ ጨዋታ ሴቶች ሴት ጓደኞቻቸውን አይሰደቡም። ይልቁንስ ያሞግሳሉ፣ ይመክራሉ ያበረታታሉ።

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡ የኸኸይቦሌ ግጥሞች ልክ እንደ አበሹቴ ግጥሞች ሁሉ የውዳሴና የስድብ ተብለው በሁለት ዐብይ ምድብ የተቦደኑ ሲሆን በውዳሴ ሥር ለሴት ጓደኛ ወይም ባልንጀራ ፍቅር መግለጫነት፣ የወንድ ጓደኛ ወይም የተቃራኒ ፆታ ፍቅር መግለጫነት በልጅነት ወይም ጊዜ ሳያልፍ መጫወትን፣ ቁምነገርን፣ መለየትን የሚገልፁ ተብለው ተመድበዋል።

በኸኸይቦሌ የስድብ ግጥሞች ዐበይት ምድብ ሥር የወንዶችን ፍርሃት የሚገልፁ፣ የወንዶችን ሥራ ፈትነትና ስንፍናን የሚገልፁ ተብለው ተመድበው ተተንትነዋል።

### 5.2.1 የውዳሴ ቃል ግጥሞች በኸኸይቦሌ ጨዋታ ትንተና

#### 5.2.1.1 የጓደኝነት ፍቅር መግለጫ በኸኸይቦሌ ቃል ግጥሞች

በነዚህ ግጥሞች ሴት ጓደኞች ለተመሳሳይ ፆታቸው ያላቸውን መውደድ ይገልጹባቸዋል። ግጥሞቹ ከማወደስና ከማሞገስ አልፈው መሰሎቻቸው ወደር የማይገኝላቸው መሆናቸውን ይገልፃሉ።

ሀ. አከሌ አበሉ የሎሚ ዛፍ፣
   አንቺን ያገባ ይበል ዘራፍ።

ለ. እከሊት አበሉ ባልንጀራዬ፣

በፊቴ ላ'ርግሽ በስተኋላዬ?

ሐ. የኔ ጓደኞች ቀጫጭኖቹ፣

ይናደፋሉ እንደ ንቦቹ።

መ. ያ የማነው እንዝርት መከታው ላይ፣

እከሊት አበሉ ቀጭን ፈታይ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ተወዳጇ ሴት ውበቷ ወይም ተፈላጊነቷ ከሎሚ ዛፍ ጋር ተነፃፅሮ ቀርቧል። በሥም የተጠራችው ሴት መዓዛዋ የሚማርክ በመሆኗና በሁሉም ሰው ተወዳጅ ስለሆነች እሷን ያገባ ሰው ሊኮራ ይገባዋል የሚል ይዘት አለው። ሎሚ የፍቅር መግለጫ ነው። መፈቀርን በሌሎች መወደድን የሚጠላ የለም። ልጅቱም እንደሎሚ ዛፍ የተወደደች የተፈቀረች ነች። የእሷ የትዳር ጓደኛ መሆን ሊያመጻድቅ፣ ሊያኩራራ ይገባል የሚል መልእክት ይዟል። እሷን የትዳር ጓደኛው ማድረግ መቻሉ ሊያስፎክረው የሚበዛበት አይደለም። ምክንያቱም ተራ ሴት አይደለችምና የሚል ነው።

ቃል ግጥም /ለ/ ከወንዶች ሆታ የዘመተ ቃል ግጥም ነው። ግጥሙ ተወዳጇ ሴት በጣም የቅርብ ጓደኛ ወይም ባልንጀራ በመሆኗ በችግርም ይሁን በደስታ ጊዜ እተማመንብሻለሁ የሚል ይዘት አለው። ጓደኝነት ትልቅ ዋጋ የሚሰጠውና በግል ምርጫ በስምምነት የሚደረግ ነው። በሀዘንም በደስታም አብሮ በመሆን የሚያጽናና እና ደስታውን የሚካፈል ተወዳጅ ሰው ነው። አንቺን የመሠለች ታማኝ ጓደኛ ከፊት ሆነ ከኋላ ደጀን ባደርግሽ መቼም ቢሆን መከታዬ ነሽ የሚል መልእክት ያስተላልፋል። እንደ ወ/ሮ አስረበብ አገላለፅ "ባልንጀራ ለችግር ጊዜ ገመና ከታች ለደስታ ጊዜ አብሮ የሚካፈል ነው። የትም ሲሄዱ ፊትና ኋላ ሆነው አይለያዩም።" (ቃለ መጠይቅ፣ 15/05/ 2006 ዓ.ም) በማለት የግጥሙን ሃሳብ አብራርተውልኛል።

ቃል ግጥም /ሐ/ ባልንጀሮቹ በአካል ሲታዩ ቀጫጭኖች ቢሆኑና ለዓይን የሚሞላ ተክለ ሰውነት ባይኖራቸውም እንደ ንብ ተባብረው ጠላታቸውን ማጥቃት የሚችሉ ናቸው የሚል ይዘት ያለው ግጥም ነው። "ንብ በአካል በጣም ትንሽ ፍጡር ሆና ሳለች በታታሪነቷ የታወቀች ነች። ንብ በትጋቷ ማርን የመሰለ ጣፋጭ የምትሰጠውን ያህል በጠላትነት የሚመጣባትን ግን የፈለገውን ያህል ቢገዝፍ በድፍረት ተወግታ የምታሸንፍ ናት።" ወ/ሮ አለም አዳነ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም) ይህን ግጥም

አስመልክተው "በትንንሽ ልጆች ወይም በወጣት ሴቶች የሚገጠም" መሆኑን አብራርተው በእነሱ ቡድን ውስጥ የተካተቱት ልጆች የሚናቁ ወይም ዝቅ ተደርገው የሚታዩ አይነት እንዳልሆኑ ለታላላቆቻቸው የሚገልፁበት ሥልት እንደሆነ ገልፀዋል።

ቃል ግጥም /መ/ መከታው ወይም ግድግዳው ላይ ተሰቅሎ የሚታየው እንዝርት ሙያ ያላት ሴት እንዝርት ነው። እንዝርት በአካባቢው ማህበረሰብ ከሞያ መለኪያ መሣሪያዎች አንዱ ነው።

ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ
ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ።

የሚለው ነባር የቀረርቶ ቃል ግጥም ከላይ የተገለጸውን እንዝርት የሴቶች ሞያ ማሳያ እንደሆነ የሚያጸና ነው። በቃል ግጥሙ የተጠቀሰውም እንዝርት ስሚ በግጥሙ ውስጥ የተጠራው ሴት እንጂ የሌላ ሰው ሊሆን አይችልም ፤ ምክንያቱም ቀጭን ፈታይ መሆኗ ይታወቃልና የሚል ይዘት አለው።

### 5.2.1.2 ፍቅርን/ፍቅረኛን የሚያወድሱ በኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞች

በእነዚህ ግጥሞች ሴቶች የተቃራኒ ፆታ ጓደኞቻቸውን በመጥራት ለመጫወት ዝግጁ መሆናቸውን የሚገልፁባቸው ናቸው።

ሀ. የዋርካ ላይ በርበሬ፣
ሰውም የለኝ ና ዛሬ።
ለ. የዋርካ ላይ ዘንጋዳ፣
ሰውም የለኝ ና እንግዳ።

ሐ. የዋርካ ላይ ገበታ፣(2)
ሰውም የለኝ ና ማታ።
መ. የገረገራ ሚዶ (2)
አያስገባም በረዶ።
የገረገራ ናስ (2)
አያስገባም ንፋስ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ስሙ የማይጠራው ወይም በዋርካ ላይ እንደተቀመጠ በርበሬ የተመሠለው ፍቅረኛ "ዛሬ መምጣት ትችላለህ፤ የሚከለክለን ወይም የሚታዘበን ሰው የለም" የሚል ይዘት አለው። ዋርካ ግዙፍ ነው፣ በሰፋፊ ቅጠል የተሞላ። በውስጡ ወፉንም ጦጣውንም ከልሎ የሚያስተናግድ። ለሰውም ለእንስሳቱም ጥላ ነው - ማረፊያ። ለሰፈር ሽማግሌም አካባቢያዊ ጉዳዮች የሚታዩበትና እርቅ ማውረጃ። ዋርካ ብዙ አገልግሎቶች አሉት። ከነዚህ አገልግሎቶች አንዱ ወጣቶች በዋርካው ሥር ተከልለው የፍቅር ጨዋታ ይጫወቱበታል። በሌላ በኩል በዋርካ ላይ የተቀመጠን ወይም የበቀለን በርበሬ ማንም ሊያየው አይችልም። ምክንያቱም በርበሬን ዛፍ ላይ ይቀመጣል ወይም ይበቅላል ተብሎ ስለማይጠረጠር ተደብቆ ወይም ማንም ሳያየው ብዙ ጊዜ ሊቀመጥ ይችላል። ቃል ግጥሙ በድብቅ ያለው ፍቅር እንዲቀጥል ዛሬ አመቺው ወቅት ነው የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው።

ቃል ግጥም /ለ/ ከላይ በግጥም ሀ እንደተገለጸው ሁሉ ስም አይጠሬው ፍቅረኛ መምጣት የሚችል መሆኑን መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው። ፍቅር ሁሌም እንግዳ ነው። ፍቅር ሁሌም አዲስ ነው። ቃል ግጥሙ "የዋርካ ላይ ዘንጋዳ" ሲል ዋርካ ላይ ዘንጋዳ መገኘቱ አዲስና ያልተለመደ ነገር ነው። ፍቅርም እንደዚሁ የተለየ ነገር አለው የሚል ሀሳብ ይዟል። በፍቅራቸው መሃል ጣልቃ የሚገባ ሰው ባለመኖሩ መምጣትና መገናኘት እንችላለን የሚል ይዘት ያለው ቃል ግጥም ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ ከላይ በግጥም ሀ እና በግጥም ለ ከተጠቀሱት ግጥሞች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሲሆን ልዩነቱ ተወዳጁ ሰው መምጣት የሚችለው ማታ እንደሆነ መገለፁ ላይ ነው። አንድም ድብቅ ፍቅር ይጥማል። አዩኝ አላዩኝ እያሉ በድብብቆሽ የሚገኝ ፍቅር አጓጊነት አለው። አንድም ተመልካች የበዛበት ፍቅር ጣልቃ ገቢው ይበዛበታል። ስለዚህ ፍቅሩን ዘላቂ ለማድረግ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ በምሽት አካባቢው ስለሚጨልም ፍቅረኞች ታዛቢ በማይኖርበት እንደልባቸው መሆን መቻላቸውን የሚያሳይ ነው።

ቃል ግጥም /መ/ ገረገራ በተባለ አካባቢ በሚገኝ ሚዶ ወይም ማበጠሪያ እና የድንጋይ ናስ ወይም ካብ ጋር ተነጻጽሮ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ምን ያህል የጠበቀና ምስጢራዊ እንደሆነ የተገለጸበት ግጥም ነው። አቶ መራጊያው ከቤ "የደጋ ቤት ክፍተት ካለው ብርድ ይገባበታል። ቆላ ግን አየሩ ሞቃት ስለሆነ አየሩ እንዲገባ ስለሚፈለግ ቤቱ ሲሠራ ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ ነው" (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 19 ቀን 2006 ዓ.ም)

በማለት  የደጋ ቤት ንፋስ የማይገባው እንደሆነ ሁሉ በሰዎችም ፍቅር መካከል ነገር እንዳይገባበት ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል። ቃል ግጥሙ ገረገራ በሚባለው አካባቢ ጥቅም ላይ የሚውለው ሚዶ በረዶ የማያስገባ ጥቅጥቅ ያለ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁም በአካባቢው የሚሠራው ናስ (የድንጋይ ካብ) ጥቅጥቅ ከማለቱ የተነሳ ንፋስ እንደማያስገባ ሁሉ የኛም ፍቅር ማንም የማያውቀውና በሌሎች የማይደፈር ነው የሚል መልዕክት ይዟል።

### 5.2.1.3 የተቃራኒ ፆታ ፍቅር መግለጫ በኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ቃል ግጥሞች የተቃራኒ ፆታ ፍቅር የሚገለፅባቸው ናቸው። ሴቶቹ የወንድ ፍቅረኞቻቸውን በስም ሳያነሱ የሚያወድሱባቸው፣ የፍቅር ስሜታቸውን የሚገልጹባቸውና ስለፍቅራቸው ሀያልነት የሚገልጹባቸው ናቸው።

ሀ. ተው ስደድልኝ የጅህን ሎሚ፣
በሽተኛ ነኝ ልቤን ታማሚ።

ለ. አሰለልከኝ (2)
ነገ ዛሬ እያስባልከኝ።

ሐ. ጨኸር ገበያ ይውላል ቅርጫት፣
አቅበጠበጣት ያችን እመጫት።

መ. ሥብርብር እንደሳር (2)
መውደድ አሳር።

በቃል ግጥም /ሀ/ በፍቅር ምክንያት ልቤን የሚያመኝ በመሆኑ ለልቤ ወይም ለፍቅሬ መድሃኒት የሚሆን እንደምትወደኝ የሚያረጋግጥልኝ ሎሚ ስጠኝ የሚል መልእክት አለው። በማህበረሰቡ ሎሚ ለተቃራኒ ጾታ መስጠት የማፍቀር ምልክት ነው። ወ/ሮ ደስታ በሪሁን  "ሎሚ የፍቅር መግለጫ ነው። ወንድ ልጅ የያዘውን ሎሚ ለሚወዳት ብቻ ነው የሚሠጠው" በማለት ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም) ከሚያፈቅሩት ወንድ ሎሚ መቀበል ለሴቷ አስደሳች ሥጦታ ነው። ሎሚ ለመድሃኒትነት እንደሚፈለግ ሁሉ የፍቅር ህመም ላለበትም እፎይታ የሚሠጥ መድሃኒት ነው። የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ሎሚ ላክልኝና እንደምትወደኝ አረጋግጥልኝ፤

እኔ ባንተ ፍቅር ተይዤ አንተን በማሰላሰል በሽታ ላይ ወድቄያለሁ በማለት የፍቅሯን ጽናት ትገልጻለች።

በቃል ግጥም /ለ/ ቀጠሮ በዛ፣ ቁርጥ ያለ የመገናኛ ጊዜ ባለመስጠትህ ሰዎች ልቤ ውስጥ ያለውን እንዲያውቁብኝ እያደረክ ነው የሚል ይዘት አለው። የስለላ ተግባር የተደበቀን ፈልፍሎ ማውጣት እንደሆነ ሁሉ በመጀመሪያው ስንኝ "አሰለልከኝ" የሚለው ስንኝ የደበቅኩትን እንዲያውቁብኝ አደረክብኝ የሚል ትርጉም አለው። ፍቅር የያዘው ሰው ያፈቀረውን ለማግኘት ሁሌም እንደጓጓ ነው። በአካባቢው ባህል መሰረት ሴት ልጅ የወደደችውን ሰው እወድሃለሁ ብላ መናገር ባህሉ አይፈቅድላትም። ወንዱ እወድሻለሁ ብሎ እስኪናገር ድረስ በትዕግስት ትጠብቃለች። የቃል ግጥሙ ተናጋሪ የምትወደው ሰው እንደሚወዳት በግልጽ ባይነግራትም እንደሚወዳት ፍንጭ በየጊዜው እያሳያት ቢሆንም የመጨረሻ ቃሉን ስላልሰጣት ልቤን አታጓጓው፣ ሰዎች ስላንተ ያለኝን ሃሳብ ከሁኔታዬ እየተረዱት ነው። ጉጉቴና ፍላጐቴ እያጋለጠኝ ነው የሚል መልዕክት ታስተላልፋለች።

ቃል ግጥም /ሐ/ ጨኽር ተብሎ በሚታወቀው የገበያ ቦታ የማይሸጥ ነገር የለም። ገበያው የሚመረጠው ወይም የማይኖረው ነገር እንደሌለ ሁሉ ፍቅርም የሚመርጠው የለም። በመሆኑም ያቺ እመጫት እንኳ ፍቅር ይዞ እያረገበገባት ነው የሚል ይዘት አለው። እመጫት መሆን የቤተሰብ ሃላፊነትን የሚያከብድ ነው። ልጅን መንከባከብ ማህበራዊ ኑሮን ችላ ሊያስብል ይችላል። ነገር ግን በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት ምንም እንኳ እመጫት ብትሆንም የፍቅርን ጉዳይ ችላ ብላ ማለፍ አልቻለችም። ፍቅር ይዞ አይሆኑ ሁኔታ እያደረጋት ነው ይላል ቃል ግጥሙ።

ቃል ግጥም /መ/ ለፍቅር ብለሽ ስለ ፍቅር ብለሽ ተሸነፊ፤ ፍቅር ደስ የሚል ነገር ግን በውስጡ ችግርና ጣጣ ያለው ነው የሚል ይዘት አለው። ፍቅር ቀላል ጉዳይ አይደለም። ለወደዱት፣ ላፈቀሩት ሰው ሲባል የመጣውን ችግር መቀበል ተገቢ ነው። ለፍቅር ሲባል ማንኛውንም መስዋዕትነት መክፈል ያስፈልጋል። ቃል ግጥሙ መውደድ መከራ ነው፤ መውደድ ችግር ነው። በመሆኑም ድርቅ ወይም ክችች ብለሽ ሳይሆን ተለሳልሰሽ ቢቻል እንደሣር ስብርብር በማለት ፍቅሩን አስተናግጅለት የሚል መልእክት አለው።

### 5.2.1.4 በወጣትነት መዝናናትን የሚያወድሱ በኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ግጥሞች ወጣት ሴቶች ሆይ! እንዝናና፣ እንቆነጃጅ ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀምበት የሚል ይዘት የሚያንፀባርቁ ናቸው።

ሀ. ሣዱላ ሁሉ በይ ክንብል ደፉ፣
   አምባሩም አለ ድሪም አይጠፉ።

ለ. እንጫወት እንጂ የምን ማፈር ማፈር፣
   አጅሬ ሳይመጣ ሳይጫነን አፈር።

ሐ. የኔ ጓደኛ በይ እርግፍ እርግፍ፣
   አደሱም አለ ኩሉም አይረግፍ።

ቃል ግጥም /ሀ/ ወጣት ሴቶች ሆይ! ጨፍሩ፣ ለመዋቢያ የሚሆን የእጅና የደረት ላይ ጌጣጌጥ ሞልቷል አታስቡ! የሚል ይዘት አለው። ወጣትነት ሁሉም ነገር ነው። ወጣትነት ውበት ነው፤ ሀይል ነው፣ ወጣትነት ሀብት ነው። ቃል ግጥሙ የወጣትነት ሀብት የሆነውን ጊዜያችንን በአግባቡ እንጠቀም ለመዝናናት ስንሄድ የሚያስፈልጉን ጌጣጌጦች ሞልተውናል የሚል ይዘት አለው።

ቃል ግጥም /ለ/ በጊዜያችን እንጫወት፣ ተመልካችን በመፍራትና በማፈር ጊዜያችን በከንቱ ካለፈ የማይቀረው ሞት ይወስደንና መቃብር ይውጠናል የሚል ይዘት አለው። ሞት ለሁሉም ሰው የማይቀር ለሰው ልጅ የተሰጠ እጣ ፋንታ ነው። ይህን የማይቀር እጣ ፋንታ ቆሞ መጠበቅ ሁለተኛ ሞት ነው። በመሆኑም ቃል ግጥሙ ከጊዜ ጋር እሽቅድምድም ማድረግ ይገባናል አለበለዚያ ሞት ይመጣና ይለያየናል የሚል መልእክት አለው። ሞት በቀጥታ ስሙ አይጠራም፤ "አጅሬ" የሚል ቅፅል በግጥሙ ተሠጥቶታል። አጅሬ የተባለው ሞት ሀይለኛነቱን ታግለው የማያሸንፉት ብርቱ ጠላት መሆኑን ለመግለፅ ነው።

ቃል ግጥም /ሐ/ አወዳሿ የምትወደሰውን ሴት "ውዱ ጓደኛዬ ጉንበስ ቀና እያለሽ ጭፈራውን አቅልጭው፤ ፀጉርሽ ላይ ያለው አደስ አልወደቀም፣ የተኳልሽው ኩልም የሚረግፍ አይደለም" በማለት ሙሉ ትኩረቷን ጨዋታው ላይ እንድታደርግ የሚገፋፋ ግጥም ነው። በጨዋታው መሃል የሚዘናጉና የሚፈዙ ወይም የሚገባቸውን ያህል

ያልተንቀሳቀሱት ትኩረት ለመሳብ የሚደረግ ጥሪ ነው። ወ/ሮ ደስታ በሪሁን "አደስ መቀባት ኩል መኳል በአበሹቴና በኸኸይቦሌ ጨዋታ አሁንም ያለ ባህል መሆኑን ጠቅሰው ከዱሮው የቀረው አልቦና ድሪ ማድረግ ነው" በማለት አጊጦና ተውቦ የወጣትነት ጊዜን በደስታ ማሳለፍ ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም)

### 5.2.1.5 ዋዛ ፈዛዛ መቅረቱንና ቁም ነገርን የሚያወድሱ

እነዚህ ግጥሞች ወጣት ሴቶች ከእንግዲህ በኋላ ጊዜያቸውን ቁም ነገር በመስራት እንደሚያሳልፉና ለቀልድና ጨዋታ ጊዜ እንደሌላቸው የሚገልፁባቸው ናቸው።

ሀ ሣዱላ ሁሉ ግገር መስታወት፣
ከእንግዲህ ቀረ ባፈር መጫወት።

ለ የኔ ጓደኛ ሥሪ መደብ፣
ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ።

ሐ የኔ ጓደኛ ሥሪ ጉልቻ፣
ከእንግዲህ ቀረ የእናት እንጎቻ።

መ የኔ ጓደኞች ቁሙ በተራ፣
ማገር ቆርጩ ቤት እስክሠራ።

ቃል ግጥም /ሀ/ ወጣት ሴቶች ሆይ! አሁን አድጋችኋል፤ ለትዳር ደርሳችኋል፤ እንደ ህፃን ጭቃ እያቦኩ አፈር እያቦለሉ መጫወት የለም! የሚል ይዘት አለው። በአካባቢው አንዲት ሴት ልጅ መስታወት ከገዛች ወይም የናቷን መስታወት ቶሎ ቶሎ ማየት ከጀመረች 'አድጋለች ለአቅመ ሄዋን ደርሳለች ወይም እየደረሰች ነው' ተብሎ ይታሰባል። መስታወት ማንነትን ለማየት የሚሞከርበት መለኪያ ነው። ወጣት ሴቶች ለመኳኳል ለማጌጥ መስታወት ይጠቀማሉ። ይህም ለትዳር የሚታጩበት ጊዜ ነው። ትዳር ከተያዘ ደግሞ እንደልብ መጫወት አይቻልም ። ቃል ግጥሙም ወደ 'ሚቀጥለው የዕድገት ደረጃ ሽግግር ላይ ስለምትገኙ የቀረቻችሁን አጭር ጊዜ የልጅነት ጸጋ የሚፈቅድላችሁን ጨዋታ ተጫወቱ የሚል ነው።

ቃል ግጥም /ለ/ ከሠርግ ወደ ኧሽይቦሌ የዘመተ ነው። ቃል ግጥሙ አንቺ ወጣት ሴት ጓደኛዬ ቤትሽን አሠማምሪ፣ ካሁን በኋላ በዋዛ በፈዛዛ የምታሳልፊው ጊዜ የለሽም የሚል ይዘት አለው። አዲስ ጎጆ ወጪ የተሟላ ዕቃ አይኖረውም። በመሆኑም አዲስ ቤት የያዘ ወይም ትዳር የመሰረተ ወጣት ከፊቱ በርካታ የጎጆ ጣጣ ስለሚጠብቀው ለጨዋታ ጊዜ የለውም። ስለዚህ የመጀመሪያውን የሚቦረቅበትን የልጅነት ደረጃ አልፈሸዋል፣ ወደሚቀጥለው ደረጃ ተሸጋግረሻል ይላል። ሀብታም መብሬ የቃል ግጥሙን ምንነት እንደሚከተለው ገልጸዋለች። " ይህ ግጥም አዲስ ሙሽራ ሆና በጨዋታው በመሳተፍ ላይ ላለች ሴት የሚገጠም ነው። ልጅቱን በእግረ መንገድ እንኳን ለዚህ አበቃሽ ለማለት የምንጠቀምበት ነው" (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 15 ቀን 2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /ሐ/ እንደ ቃል ግጥም ለ በጨዋታው ላይ ለምትሳተፍ አዲስ ሙሽራ የሚገጠም ነው-ከሠርግ ዘፈን የዘመተ። በልጅነት ጊዜ ምን እበላለሁ ምን እጠጣለሁ ተብሎ አይታሰብም። ያን ማሰብ የወላጅ ፋንታ ነው። ልጅ ከእኩዮቹ ጋር ተጫውቶ ወደ ቤቱ ሲገባ እናቱ ያነነተችውን ይበላል። ትዳር ውስጥ ከተገባ ግን ሀላፊነት ስለሚኖር እንደልብ መጫወት አይቻልም። ስለዚህ ቃል ግጥሙ የራስሽን ምግብ ራስሽ አዘጋጂ፣ ጉልቻሽን አስተካክለሽ ወጥሽንና እንጀራሽን አዘጋጂ ካሁን በኋላ የእናትሽን እንጀራ አታገኚውም የሚል ነው። ወ/ሪት ንግስቴ አከለ "ጉልቻ ማለት ትዳር ማለት ነው። ጉልቻ ሥሪ የተባለችው ልጅ የራስሽን ቤት ወይም ትዳርሽን አሟሙቂ ለማለት ነው" በማለት ገልጸዋል። (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዝያ 11 ቀን 2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /መ/ ከእንቁጣጣሽ የልጃገረዶች ዘፈን የተወሰደ ነው። አቀንቀኟ ቤት የሌላት በመሆኑ ጓደኞቿን በእንግዳ ወግ እቤቷ አስገብታ ልትጋብዛቸውና ልታስተናግዳቸው የምትችል አለመሆኗን የምትገልጽበት ነው። ቤት ትዳርን ይወክላል። በዚህም አቀንቃኟ ትዳር ባለመመስረቷ የራሷ የሆነ ቤት ስለሌላት በትዕግስት እንዲጠብቋት የሚያሳስብ ነው።

### 5.2.1.6 መለያያትን በመፍራት አብሮነትን ሚያወድሱ

እነዚህ ግጥሞች የዕለቱ የጨዋታ ጊዜ መጠናቀቁን የሚገልፁና በሚቀጥለው ጊዜ በሠላም እንዲገናኙ ምኞትን የሚገልፁ ናቸው።

ሀ. አዘቀዘቀ ገባ ጀምበሩ፣
ሊበታተን ነው ልጅ በየአገሩ።

ለ. ከቤቴ በታች ያለች እንቧይ፣
ኧረ እኛስ አንለያይ።

ሐ. ካመት ያድርሰን ካመት አመቱ፣
ሳይነጣጥለን አጅሬ ሞቱ።

መ. አመት ያድርሰን ካመቱ፣
እንሸኘዋለን በየወረቱ።

በቃል ግጥም /ሀ/ ጊዜው መሸ፣ ጨላለመ ስለዚህ መለያየታችንና ወደየቤታችን መሄዳችን የማይቀር ሆነ የሚል ይዘት አለው። ብርሃን የተስፋ ተምሳሌት ነው፤ የወደፊት መልካም ነገርን ይጠቁማል። ጨለማ ግን በተቃራኒው ያስፈራል። ይህን የጨለማ ጊዜ ደግሞ ሁሉም በየቤቱ ተከትቶና አድፍጦ ያሳልፈዋል። በዚህም የአብሮነትን አስደሳች ጊዜ ወደ አስከፊ ብቸኝነት ይወስደዋል። በቃል ግጥሙ የተንጸባረቀው ይኸው ፍራቻ ነው። ግጥሙ ሙሉ ቀን ስንጫወት ውለን አሁን ግን በመምሸቱ ሁሉም ልጆች ወደ ቤታቸው ለመሄድ እያኮበኮቡ ነው በቃ መለያየታችን ቁርጥ ሆነ የሚል መልእክት አለው።

ቃል ግጥም /ለ/ ከቤቴ አጠገብ ያለችው እንቧይ ሁሌም የምታጫውተኝ እሷ ናት፣ የኔም ጓደኞች ሁሌ ቢያጫውቱኝ ባንለያይ እንዴት ጥሩ ይሆን ነበር? የሚል ይዘት አለው። ብቸኝነት ያስፈራል። በተለይ በልጅነትና በወጣትነት ዕድሜ ብቸኝነትን ማስተናገድ ከባድ ይሆናል። ልጅ የሚያጫውተው ሌላ ልጅ ባይኖር ከአፈር፣ ከድንጋይና ከእንቧይ ጋር ይጫወታል። ጨዋታን ለህጻናት ተፈጥሮ የሰጠቻቸው ጸጋ ናትና። ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ እንደሚገለፁት "እንቧይ የልጆች መጫወቻ ነው። እንቧይ በመካብ፣ በማንከባለል ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ነው" በማለት አያይዘው እንቧይ የጓደኛ የአጫዋች ተምሳሌት ተደርጐ እንደሚቆጠር ይገልፃሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /ሐ/ ዛሬ መለያየታችንና ወደየቤታችን መበታተናችን የማይቀር ነው። ቢሆንም ግን ለሚቀጥለው ዓመት ልክ እንደዘንድሮው መጫወት እንድንችል በሠላም

ያድርሰን የሚል ነው። አሁን መለየቱ ብዙም አያሳስብም ይልቁንስ ሞት የሚባለው ክፉ እጣ ያለያየን ከሆነ ሃዘናችን የባሰ ነው። "ሞት የሰው ልጅ ታግሎ የማያሸንፈው ብርቱ በመሆኑ ነው አጅሬ የተባለው" በማለት ወ/ሮ ብርዘገን ይገልፃሉ።

ቃል ግጥም /መ/ በሰላም ከአመት አመት ያድርሰን ሌላውን ነገር እንዳመጣጡ እንቀበለዋለን የሚል ነው። የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ደስታም ሀዘንም ያጋጥመዋል። ሁሌ ጊዜ ደስታ ወይም ሁልጊዜ ሀዘን አይኖርም። ክፉም ደጉም እየተፈራረቁ መምጣታቸው አይቀርም። ቃል ግጥሙ ክፉም ሆነ ደግ የሚመጣውን ሁሉ እንደየሁኔታው ማለፋችን አይቀርም፣፣ ክፉ ነገር ቢመጣ አዝነን መልካም ነገር ቢመጣ ተደስተን እናልፈዋለን የሚል መልእክት ይዟል። ግጥሙ በቀጥታ አይጥቀስ እንጂ "አጅሬ ሞት ብቻ አይምጣብን እንጂ ሌላውስ እንደፍጥርጥሩ" የሚል ሃሳብ ይዟል።

## 5.2.2 በኧኸይቦሌ ጨዋታ የስድብ ግጥሞች

### 5.2.2.1 ፈሪ ወንዶችን የሚሰድቡ በኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ቃል ግጥሞች ሴቶች ፈሪ ወንዶችን የሚሳደቡበት፣ ለፈሪ ወንድ ጥላቻ እንዳላቸው የሚገልፁባቸው ግጥሞች ናቸው። ወንድ ጀግና ጠላቱን ድባቅ የሚመታ መሆን አለበት የሚል ሃሳብ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

ሀ ተዋጋ ብዬ ብሰጠው ጋሻ፣
ለእናቱ ሰጣት ያመድ ማፈሻ።

ለ እንሂድ ሲሉት አልሄድም ይላል፣
ገለ'ው ሲመጡ በሞትኩት ይላል።

ሐ ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው እንቅብ፣
ሲሸሽ አየነው ቅብቅብ ለቅብቅብ።

መ ይህ የፈሪ ልጅ ሲፈራ ጊዜ፣
ያባቱን ገዳይ አረ'ገው ሚዜ።

ቃል ግጥም /ሀ/ ከጠላት የሚወረወር ጦር መመከቻ እንዲሆን የሰጠሁትን ጋሻ፣ ያለ አገልግሎቱ እቤት አዋለው። እንደ ጀግና ወንዶች ጦር ሜዳ መሄድ ስላልቻለ የሰጠሁትን ጋሻ ለአመድ ማፈሻ እናቱ አውላዋለች የሚል መልእክት አለው።

በአካባቢው ማህበረሰብ ወንድ ልጅ ደፋር ማንኛውም ችግር ቢያጋጥመው መጋፈጥ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል። የሚያጋጥመውን ችግር ለመቋቋም ደግሞ አስፈላጊው የወንድ ልጅ መሣሪያ ሊኖረው ብሎም አጠቃቀሙን ሊያውቅ ይገባል። ጋሻ የጀግና መሣሪያ ነው። ይህ ፈሪ ሰው ግን በተገቢው ቦታ ስላልተጠቀመበት ጋሻው የእናቱ አመድ ማፈሻ ሆኖ እያገለገለ ነው። በዚህም የሰውየው ፍርሃት ተገልፆበታል።

ቃል ግጥም /ለ/ ጓደኞቹ ጠላታቸውን ለመውጋት እንሂድ ብለው ሲያማክሩት ፈሪ በመሆኑ ምክንያት "አልሄድም " በማለት ከጦር ሜዳ ውሎ ራሱን ያገላል። ጓደኞቹ ጦር ሜዳ ውለው ጠላታቸውን ድል አድርገው ሲመጡ ግን "ምነው እኔም በሄድኩ ኖሮ" እያለ ይፀፀታል የሚል ይዘት አለው። ጀግና ጠላቱን የሚያጠቃበትን ጊዜ ይወስናል። ቁርጥ ውሳኔ አድርጎ ካልተንቀሳቀሰ በጠላቱ መቀደሙ አይቀርም። በቃል ግጥሙ ያለው የተጠቀሰው ገጸባህርይ ጊዜውን ለክቶ ስለማይንቀሳቀስ በሌሎች ጀግኖች ሁሌም የሚቀደምና ራሱን ለጸጸት አሳልፎ የሚሰጥ ነው። በመሆኑም ቃል ግጥሙ ፈሪ ሁሌም እንደተጸጸተ ኗሪ ነው ይለናል።

ቃል ግጥም /ሐ/ ተሰዳቢው ጐፈሬውን አሳድጐና አሳምሮ ሲታይ ጀግና ይመስላል። ጠላት ሲመጣበት ግን ማሳ ለማሳ ሲሸሽ ሰው ሁሉ ያየው ፈሪ ነው የሚል ይዘት አለው። "በአካባቢው ባህል ወንድ ልጅ ከሚገባው በላይ መኳኳልና መሽቀረቀር አይጠበቅበትም። መሽቀርቀርና መኳኳል የሴቶች ነው ተብሎ ይታሰባል።" (የቡድን ውይይት፣ ጥር 24 / 2006 ዓ.ም) ለውበቱ አጥብቆ የሚጨነቅ ከሆነ በጀግንነት ቦታ ላይ የሚጠበቀውን ያህል አይሆንም የሚል አስተሳሰብ በመኖሩ የሚሽቀረቀሩ ወንዶች ጀግንነት ላይ የሉበትም ተብለው ይታማሉ በማለት ሃሳባቸውን አካፍለውኛል።

ቃል ግጥም /መ/ የአባቱን ገዳይ በመበቀል ያባቱን ደም መመለስ ሲገባው ፈሪ በመሆኑ ምክንያት በመበቀል ፋንታ ጭራሹን ሚዜ አደረገው የሚል መልእክት አለው። ሀብታሙ ፍስሀ ነዋሪነታቸው ወገልጤና ከተማ ሲሆን የባለቤታቸው ቤተሰቦች ቁዳ ምስትንክር ቀበሌ መልስ ጠርተዋቸው በጨዋታው ቦታ ታዳሚ ሆነው አግኝቼ በማግስቱ በቀጠሮ ተገናኝተን በሰጡኝ ማብራሪያ "በአካባቢ ባህል መሰረት 'ደሙን ያልተወጣ' እንደወንድ አይቆጠርም። የአካባቢው ሰው ይንቀዋል፣ ይሰድበዋል።" (ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 13/2006 ዓ.ም) ስለዚህ ማህበረሰቡ የሚጠብቀውን ምላሽ የማይሰጡ ወንዶች እንደሚሰደቡ አስረድተውኛል። በመሆኑም ቃል ግጥሙ የዚህ ሰው

ፍርሃት ከዘር የወረሰው ነው። አባቱም ፈሪ ነበር፤ እሱም እንዳባቱ ፈሪ ሆነ የሚል ይዘት አለው። ጀግና ቢሆን ኖሮ ያባቱን ገዳይ ወዳጅ አያደርግም ነበር የሚል ነው።

### 5.2.2.2 ሰነፍንና ሥራ ፈትን የሚሰድቡ በኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች

በነዚህ ግጥሞች ሴቶች ሥራፈት ወይም ሰነፍ ወይም መገኘት ባለበት ቦታ ያልተገኘ ወንድን ለመስደብ የሚጠቀሙባቸው ቃል ግጥሞች ናቸው። መሥራት የሚገባህን የወንድ ሥራ በአግባቡ አልተወጣህም በማለት ሃሳባቸውን የሚገልፁባቸው ቃል ግጥሞች ናቸው።

ሀ ምን ታደርጋለህ ? ከፈረፈሩ፣
ባልንጀሮችህ ወልደው ሲድሩ።

ለ ምን ታደርጋለህ? ከአለቱ ሥር፣
ያለመሳሪያ ያለ ምሳር።

ሐ ቦለል እያለ ያረሰው እርሻ፣
አንጀት አያርስ አይሆን ጉስጉሻ።

ቃል ግጥም /ሀ/ ገርፍ የሸረሸረው ገድጓዳ ቦታ ተደብቀህ ሴት በማሳደድ ጊዜህን ለምን በከንቱ ታሳልፋለህ? ያንተ እኩዮች ልጅ ወልደው፣ አሣድገው ለወግ ማዕረግ ሲያደርሱ አንተ ግን አሁንም የጎረምሳ ሥራ ትሠራለህ የሚል ይዘት አለው። በማህበረሰቡ ሁሉም ሰው በየእድሜ ደረጃው ሊያከናውነው የሚገባውን ብቻ እንዲያደርግ ይጠበቃል። አንድ ህጻን ልጅ ዋርካ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ሽምግልና እንዲሠራ አይጠበቅም፣ የራሱ የሥራ ድርሻ አለው ። በዕድሜ የበሰለና ትልቅ ሰውም በየአሳቻ ቦታው ኮረዳ ሲያባርር መዋል ከእሱ የማይጠበቅ አሳፋሪ ድርጊት ነው። ወ/ሮ የሺወርቅ አለሙ "ፈረፈር የተቦረቦረ መሬት ስለሆነ በድብቅ የሚያመነዝሩ ሰዎች መገናኛ ነው" በማለት ፈረፈር ለፈረፈር የሚሄድ ሰው እንደአመንዝራ የሚታይ ከመሆኑም በላይ ሥራ ፈትነትን የሚያሳይ ነው" በማለት ያብራራሉ። (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 9 ቀን 2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /ለ/ አትክልት እንደሚንከባከብ ሰው ወንዝ ለወንዝ ትሄዳለህ አንተ ግን ያለ ሥራ የምትዞር ሥራ ፈት ነህ ሥራ የሚሠራ ሰው በያዘው መሣሪያ ይታወቃል። አንተ ግን በእጅህ ላይ የሚታይ መሣሪያ የሌለህ ከንቱ ነህ የሚል ይዘት አለው። "በአካባቢው

አንድ ገበሬ ከቤቱ ሲወጣ ባዶ እጁን አይወጣም። መጥረቢያ፣ ዶማ ወይም የእንጨት ማሰሪያ ገመድ አንጠልጥሎ የመውጣት ባህል አለ። ቢያንስ ቢያንስ ዱላ ከእጁ ሊጠፋ አይገባም።" በማለት አቶ ሀብታሙ በመግለጽ የቃል ግጥሙ ይዘት ባዶ እጁን የሚሄድ ሰው እንደሥራ ፈት እንደሚቆጠር ገልጸውልኛል። (ቃለመጠይቅ ሚያዝያ 13/2006 ዓ.ም)

ቃል ግጥም /ሐ/ ኮስተር ብሎ፣ በአጭር ታጥቆ ባለማረሱ ወይም ባለመሥራቱ በዓመቱ የሚሠበሰበው እህል እዚህ ግባ የማይባል አነስተኛ የሆነች ጐተራ እንኳ የማይሞላ ነው። ግብርና ወሳኝ የህብረተሰቡ መተዳደሪያ በመሆኑ በእርሻ ወቅት ሁሉም ገበሬ በትጋት መሥራት ይጠበቅበታል። ቃል ግጥሙ በትጋት የማይሰሩትን አርሶ አደሮች የሚተች ነው። ዘና ብሎ ሳይጨነቅ በነካ ነካ በማረሱ የሚያመርተው ምርት እዚህ ግባ የማይባል መሆንን የሚናገር ነው። በዚህም ስንፍናው ለረሃብ ያጋለጠው ሥራ ፈት ነው የሚል ይዘት ያለው ግጥም ነው።

# ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ትኩረት በደላንታ ወረዳ በአበሹቴና በኾኺይቦሌ ጨዋታዎች የሚዜሙ ቃል ግጥሞችን ክዋኔ ማሳየትና የይዘት ትንተና ማድረግ ነው። ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት በደላንታ ወረዳ አራት ቀበሌዎች በመገኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል። ለጥናቱ ምልከታና ቃለ መጠይቅ በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል። ጨዋታዎቹ ፆታ ተኮር በመሆናቸው ምክንያት በመረጃ ስብሰባ ወቅት ኢ-ተሳትፎአዊ ምልከታ ተደርጓል።

የቃል ግጥሞቹ መከወኛ አጋጣሚዎች ዓመታዊ ክብረ በዓላትና የታቦት ንግሥ ናቸው። በዓላቱ ከህዳር 21 ጀምሮ እስከ ፋሲካ ባሉት ጊዜያት የሚከበሩ ናቸው። የአበሹቴና የኾኺይቦሌ ጨዋታዎች በዓመቱ የሚጀምረው የህዳር ማሪያም በምትነግሥበት ቆላማ አካባቢዎች ነው። ምክንያቱም በቆላማ አካባቢዎች የሚገኙ ሰብሎች ከደጋ ሰብሎች ቀድመው ስለሚሰበሰቡና ወጣቶች ለጨዋታ በቂ ጊዜ ስለሚኖራቸው ነው።

ጥናቱ በሰባት ክብረበዓላት የተሰበሰቡ የቃል ግጥሞች ክዋኔ ተመልክቷል። የገና፣ የጥር ስላሴ፣ የጥምቀት፣ የጥር ሚካኤል፣ የጥር ጊዮርጊስ (ሰባር አጽሙ ጊዮርጊስ) የጥር ማሪያምና የፋሲካ በዓላት ናቸው።

የአበሹቴና የኾኺይቦሌ ጨዋታዎች ለመዝናናት ብቻ የሚከወኑ ናቸው። አሸንዳ ወይም ሻደይ በመባል እንደሚታወቀው የሴቶች ጨዋታ ገንዘብ አይሰበሰብባቸውም። ጨዋታዎቹ ዓለማዊ ገጽታና ይዘት ያላቸው ቢሆንም ሀይማኖታዊ መሰረት አላቸው። የጨዋታዎቹ ጥንተ መነሻ ወይም አጀማመራቸው ከፋሲካ በዓል ጋር የተያያዘ ቢሆንም ቀስ በቀስ በሌሎች በበጋ የሚከበሩ በዓላትም የሚከወኑ ናቸው።

ፎክሎር ከማህበረሰቡ አኗኗር ጋር የተያያዘ ነው። በአበሹቴና በኾኺይቦሌ ጨዋታዎች የሚከወኑ ቃል ግጥሞች የደላንታን ህዝብ ፍላጎትና ምኞት የሚያንጸባርቁ ናቸው። ሴቶቹ ከማህበረሰቡ ያፈነገጡ ወይም ማህበረሰቡ የማይፈልገውን ድርጊት የሚፈጽሙ አባላትን በመንቀፍ እንዲሁም የማህበረሰቡን እሴት የሚጠብቁትን በማወደስ በእነዚህ የቃል ግጥሞች አማካይነት ባህሉንና ማንነቱን ለመጠበቅ ብሎም ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት እንዲሳካ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ወቅት የሚገጠሙ ቃል ግጥሞች ይዘት ትኩረት ሙገሳና ስድብ ናቸው። በአበሹቴ ሴቶች ሴቶችን በውበታቸው፣ በሙያቸው፣ በታታሪነታቸው፣ በጽዳት አጠባበቃቸው፣ ወዘተ ያሞግሳሉ። እንዲሁም በተቃራኒው የፆታ እኩዮቻቸውን ነውር እየዘረዘሩ ይሳደባሉ። በአበሹቴ ጨዋታ አብዛኛው የጨዋታ ክፍለ ጊዜ በስድብ ቃል ግጥሞች የተሞላ ነው። በኧኸይቦሌ ጨዋታ ሴቶች ሴቶችን ያሞግሳሉ ወንዶችን ይሰድባሉ። ሴቶች ሴቶችን አይሰድቡም። አልፎ አልፎ የሴቶቹ አባቶች ቆንጆ ወይም ባለሙያ ሴት ልጅ በመውለዳቸው ይሞገሳሉ። ሙገሳው በጥቂቱ ለባልና ለወንድምም ይተርፋል።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች ሴቶችን የአንድ ቡድን አባል በማድረግ ግንኙነታቸው የጠነከረ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና አላቸው። በተጨማሪም በየመንደሩና በየጎጡ ያሉ ሀሜቶችን ይፋ በማድረግ መረጃ ከመለዋወጥ ባሻገር የሚታሙት ሴቶች ከስህተታቸው እንዲታረሙና ማህበረሰቡ መልካም ሥነ ምግባር የሚላቸውን እሴቶች እንዲከተሉ ዕድል ያገኛሉ።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች  ሁለቱም በገጠር አካባቢ የሚከወኑ ናቸው። በመሆኑም ጥናቱ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስር የጠነከረ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የአበሹቴና የኧኸይቦሌ ጨዋታዎች የክዋኔ ቦታና የክዋኔ ድግግሞሽ ለውጥ እየታየባቸው እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። ቀደም ባለው ጊዜ ጨዋታዎቹ የሚከወኑት በፋሲካ ዕለት ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በገና፣ በጥምቀትና ታቦት በሚነግስባቸው የገጠር ቀበሌዎች ይከወናሉ። በሁሉም የወረዳው ቀበሌዎች ይከወኑ የነበሩት እነዚህ ጨዋታዎች በአሁኑ ጊዜ ከከተማ ራቅ ባሉ ቀበሌዎች ብቻ እየተከወኑ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

# ዋቢ ጽሑፎች

ብርሃን አሰፋ። "የአሆላሌ ጨዋታ ክዋኔና የግጥሞቹ ይዘት ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለቢ. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ 1997።

አፀደ ተፈራ። "በሰቆጣ ከተማ የክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ 1997።

ዘሪሁን አስፋው። *የሥነ ጽሑፍ መሰረታዊያን፣* የንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፣ 1992።

የደላንታ ወረዳ ባህልና ማስታወቂያ ጽ/ቤት። "ደላንታ ወረዳ የንግድና የኢንቨስትመንት መመሪያ" ጥቅምት፣ 2001።

የደላንታ ወረዳ ንግድና ትራንስፖርት ጽ/ቤት። "ደላንታ" ጥር ፣ 2006 ዓ.ም።

ደስታ ተክለ ወልድ። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፣ 1962።

ፈቃደ አዘዘ። *የስነቃል መምሪያ።* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻሕፍት ማዕከል፣ 1991።

Bauman, Richard. *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments.* New York: Oxford University Press, 1992.

_______________. "Verbal Art as Performance" Waveland: University Press, 1977.

_______________. "*The Field Study of Folklore in Context*: A handbook of American Folklore." Ed, Richard M. Dorson, New York: New York University Press, 1983.

Ben- Amos, Dan. "*Context" in Context*. Western Folklore Vol.52, No, 2/4, *in Theorizing Folklore; Toward New Perspective on the Politics of Culture*. (Apr. - Oct., 1993), pp. 209-226.

Kapchan, Deborah A. "Performance." *The Journal of American Folklore*, Vol. 108, No. 430, pp. 479-508.

Finnegan, Ruth. *Oral Literature in Africa.* Nairobi: Oxford University press, 1970.

___________. *ORAL POETRY its nature, significance and social Context.* London: Cambridge University press, 1977.

Goldstein, Kenneth. S.A *A Guide for field works in folklore.* Detroiter: Gale Research Company, 1964.

Okpewho, Isidore. *African Oral Literature*: *Backgrounds, Characters and continuity*. Bloomington: Indiana University Press, 1992.

Sims, Martha C., Martine Stepens. *Living Folklore An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Utah: Utah State University Press, 2005.

Vansina, Jan. *Oral Tradition as History*. Madison: University of Wisconsin Press, 1985.

## የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ (ፕሮፋይል)

| ተ. ቁ | ሥም | ፆታ | ዕ ድ ሜ | የመኖሪያ አድራሻ | ሥራ | የተሰጠው መረጃ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መጋቢ አዕላፍ ደረጀ በየነ | ወ | 49 | ወገልጤና ከተማ | የቤት ክህነት ሃላፊ | የጨዋታዎቹ ታሪካዊ አመጣጥ |
| 2 | ወ/ሮ ወርጫለቁ ባዬ | ሴ | 75 | አሲም | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ ምንነት |
| 3 | ወ/ሮ ብርዘገን ዘገየ | ሴ | 65 | ቁዳ ምስትንክር ቀበሌ | አርሶ አደር/ | ስለ ቃል ግጥሞች ክዋኔ/ዓይነት.. |
| 4 | ወ/ሮ ደስታ በሪሁን | ሴ | 25 | ጎሽሜዳ ቀበሌ | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ |
| 5 | ወ/ሮ ዓለም አዳነ | ሴ | 22 | ቁዳ/ምስትንክር | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ |
| 6 | ወ/ሮ ሙሉ ሰማኝ | ሴ | 26 | ዲማ ቀበሌ | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ ይዘት |
| 7 | ወ/ሮ ካሳይቱ እውነቱ | ሴ | 40 | ዲማ ቀበሌ | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ |
| 8 | አቶ ተሾመ ካሴ | ወ | 55 | ዲማ | አርሶ አደር | ስለጨዋታዎቹና ፋይዳ/ስለ ባህል |
| 9 | አቶ ስጦታዬ አስማሜ | ወ | 46 | ወገልጤና ከተማ | የመንግስት ሠራ/ | ስለ ቃል ግጥሞቹ መከወኛ አጋጣሚዎች |
| 10 | ወ/ሪት እመቤት ያረጋል | ሴ | 15 | ቁዳ/ ምስትንክር | - | ስለአበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 11 | ወ/ሮ አስረበብ ዘገየ | ሴ | 52 | ጎሽሜዳ | አርሶ አደር | ስለቃል ግጥሞቹ ክዋኔ/ይዘት |
| 12 | ወ/ሪት ዓለም ታረቀኝ | ሴ | 14 | ቁዳ ምስትንክር ቀበሌ | - | ስለቃል ግጥሞቹ ክዋኔ |
| 13 | አቶ መራጊያው ከበደ | ወ | 35 | አሲም ቀበሌ | አርሶ አደር | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 14 | ሀብታሙ ፍስሀ | ወ | 31 | ወገልጤና | የመንግስት ሠራ/ | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 15 | ደስታው አስማማው | ወ | 24 | ወገልጤና | - | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |

| ተ.ቁ | ሥም | ፆታ | ዕድሜ | የመኖሪያ አድራሻ | ሥራ | የተሰጠው መረጃ ዓይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | ወ/ሮ አታሉ አስሜ | ወ | 25 | ጎሽሜዳ | አርሶ አደር | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 17 | ወ/ሪት ንግስቴ አከለ | ሴ | 18 | ጎሽሜዳ | _ | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 18 | ሀብታም መብሬ | ሴ | 18 | አሲም | - | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 19 | እንዳሻሽ ስጦታው | ሴ | 34 | ዲማ | አርሶ አደር | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 20 | የሺወርቅ አለሙ | | 30 | አሲም | አርሶ አደር | ስለ አበሹቴና ኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች |
| 21 | ድርብ ገዜ | ሴ | 11 | ቂዳ/ምስ ትንክር | - | ስለቃል ግጥሞቹ ለመዳ |
| 22 | እሙዬ ሀብታሙ | ሴ | 11 | ወገልጤና | - | ስለቃል ግጥሞቹ ለመዳ |

**<u>አባሪ 1፦</u>** የኧኸይቦሌና የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ስብስብ

## <u>1.1 የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞች</u>

1. ልሳምሽ አለኝ አለማፈሩ፣
   የበጋ ኩበት መስሎ ከንፈሩ።
2. መለስ መለስ በል እንደሽማኔ፣
   ውሎህ ከሌላ አዳርህ ከኔ።
3. መገና ላይ ላይ በላቸው (2)
   ወደመጡበት፣ ወዳገራቸው።
4. ምን ታደርጋለህ ? ከሠንበሌጡ፣
   ባልንጀሮችህ ገ'ለው ሲመጡ።
5. ምን ታደርጋለህ ? ከቁልቋሉ ሥር፣
   የቆንጆ ወዳጅ ያለህ ይመስል።
6. ምን ታደርጋለህ ? ከፈረፈሩ፣
   ባልንጀሮችህ ወልደው ሲድሩ።
7. ምን ታደርጋለህ? ከአለቱ ሥር፣
   ያለመሳሪያ ያለ ምሳር።
8. ምን ታደርጋለህ? ከኩበቱ ሥር፣
   የጅሪ ወዳጅ ያለህ ይመስል።
9. ምን ታደርጋለህ? ከዛፉ ላይ፣
   ከኛ ጋር ሆነህ ቆንጆ እንዳታይ።
10. ምን ታደርጋለህ? ከገደሉ ስር፣
    የሰይጣን ወዳጅ ያለህ ይመስል።
11. ሣዱላ ሁሉ ምችው በእግርሽ፣
    እሾህም የለው የሚወጋሽ።
12. ሣዱላ ሁሉ ግገር መስታወት፣
    ከእንግዲህ ቀረ ባፈር መጫወት።
13. ሣዱላ ሁሉ በይ ክንብል ደፋ፣

አምባሩም አለ ድሪም አይጠፋ።

14. ሣዱላ ሁሉ ተቀምጠሽ፣
እቁንጮጮሽ ላይ ወፍ አራብሽ፣
ጎንበስ በይና ላራግፍልሽ።

15. ሣዱላ ሁሉ ተቀምጠሽ፣
ተይ ተከተይው አመለጠሽ።

16. ሥብርብር በይለት(2)
በሸጌው ሞት።

17. ሥብርብር እንደሳር (2)
መውደድ አሳር።

18. ሥብርብር እንዳደስ፣ (2)
መውደድ አዲስ

19. ራሴን ስሪኝ ጭራ በጭራ፣
ቆላ እወርዳለሁ እንጨት ሰበራ።

20. በዛላይ በዛታች ሰዎች ሲሯሯጡ፣
ወንዶቹ ሁሉ በመንገድ ቀለጡ።

21. በጠጠር ላይ ሙዳይ፣ (2)
ኧረ እኛስ አንለያይ።

22. ቦለል ቦለል በል እንደነጋዴ፣
አቅማዳው ያንተ ወረቱ የኔ።

23. ቦለል ቦለል በል እንደሸማኔ፣
ኩታው ያንተ ነው ቀሚሱ የኔ።

24. ቦለል ቦለል በይ እንደምንሽር፣
ይሄ ጨዋታ ሳይል ምንሽርሽር።

25. ቦለል እያለ ያረሰው እርሻ፣
አንጀት አያርስ አይሆን ጉስጉሻ።

26. ተዋጋ ብዬ ብሰጠው ሳንጃ፣
ሰጠው ለእረኛ ከብት ማገጃ።

27. ተዋጋ ብዬ ብሰጠው ጋሻ፣
ለናቱ ሰጣት ያመድ ማፈሻ።

28. ተው ማሙሽ ማታ አጠባሃለሁ፣
አሁን ሸጌ ጋር አረበርባለሁ።

29. ተው ስደድልኝ የጅህን ሎሚ፣
በሽተኛ ነኝ ልቤን ታማሚ።

30. አለም አዳነ የሎሚ ዛፍ፣
አንቺን ያገባ ይበል ዘራፍ።

31. አመት ያድርሰን አመቱ፣
እንሸኘዋለን በየወረቱ።

32. አሰለልከኝ (2)
ነገ ዛሬ እያስባልከኝ።

33. አዘቀዘቀ ገባ ጀምበሩ፣
ሊበታተን ነው ልጅ በየአገሩ።

34. እንሂድ ሲሉት አልሄድም ይላል፣
ገለ'ው ሲመጡ በሞትኩት ይላል።

35. እንጨት ሰባሪ ውሃ ወራጅ፣
አላየሽም ወይ የኛን ወዳጅ።

36. እንጨትስ መስበር በዳምጠው እርሻ፣
ምን ብሎሽ ሄደ ያ ጥቁር ውሻ።

37. እንጨትስ መስበር የአጋም የአጋም፣
ምን ብሎሽ ሄደ ያ ልጋጋም።

38. እንጫወት እንጂ የምን ማፈር ማፈር፣
አጅሬ ሳይመጣ ሳይጫነን አፈር።

39. እከሊት አበሉ ባልንጀራዬ፣
በፊቴ ላ'ርግሽ በስተኋላዬ?

40. እከሌ አበሉ ተቀበይኝ፣
ሳይሳሳተኝ ሳይስቁብኝ፣
ቢሳሳተኝስ ቢስቁብኝ፣
አባቴ በብር አልገዛልኝ።

41. ኧሽይቦሌ ማለት የአባት እድር ነው፣
ያንቺ ኩራትሽ ከምንሽ ላይ ነው።
42. ከቤቴ በታች ያለች እንቧይ፣
ኧረ እኛስ አንለያይ።
43. ካመት ያድርሰን ካመት አመቱ፣
ሳይነጣጥለን አጅሬ ሞቱ።
44. ሽይቦሌ እያልኩኝ ያረስኳት እርሻ፣
አንዲቱ ጭብጥ ሞላች ጉስጉሻ።
45. ዛርጤው ዝርጥርጥ ዛርጤው ምንጣፉ፣
የተደገፈው ደረቀ ዛፉ።
46. የሰሌ ውሃ ውስጡ አረንጓዴ፣
እናቱ ሞታ እኔ ተሹሜ።
47. የሰው ሁሉ ባል ቶሎ ይመጣል፣
የኔ ጎታታ ይሰነብታል።
48. የኔ ጓደኛ ሥሪ መደብ፣
ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ።
49. የኔ ጓደኛ ሥሪ ጉልቻ፣
ከእንግዲህ ቀረ የእናት እንጎቻ።
50. የኔ ጓደኛ በይ እርግፍ እርግፍ
አደሱም አለ ኩሉም አይረግፍ።
51. የኔ ጓደኛ በይ ክንብል ደፋ፣
አደሱም አለ ኩሉም አይጠፋ።
52. የኔ ጓደኞች ቀጫጭኖቹ፣
ይናደፋሉ እንደ ንቦቹ።
53. የኔ ጓደኞች ቁሙ በተራ፣
ማገር ቆርጬ ቤት እስክሠራ
54. የዋርካ ላይ በርበሬ፣
ሰውም የለኝ ና ዛሬ።

55. የዋርካ ላይ ቡንኝ (2)
ሰውም የለኝ ናልኝ።
56. የዋርካ ላይ ዘንጋዳ፣
ሰውም የለኝ ና እንግዳ።
57. የዋርካ ላይ ገበታ፣(2)
ሰውም የለኝ ና ማታ።
58. የገረገራ ሚዶ (2)
አያስገባም በረዶ።
59. የገረገራ ናስ (2)
አያስገባም ንፋስ።
60. ያ የማነው እንዝርት መከታው ላይ፣
እከሊት አበሉ ቀጭን ፈታይ።
61. ያንችማ ወንድም አንገተ ጥሩ፣
ጥርሶቹ በሀር የተማገሩ።
62. ያደሌ ውሃ ሲሄድ ያወካል፣
ልቤ ወዳንተ ምነው ያወከውካል።
63. ይሂ ምን ይላል ቁመተ ረጅም፣
ሲሸሽ ሲሮጥም ነፍሱ የለችም።
64. ይሂ ምን ይላል ተልባ ወቃጭ፣
ሲቅም ያመሻል እንቅጥቃጭ።
65. ይሂ ምን ይላል አይነ ጎብላላ፣
ወለደችለት ሚስቱ ከሌላ።
66. ይሂ ምን ይላል እግረ ወልቻማ፣
ያቺን ልጅ ጠቅሶ አላት ነይማ!
67. ይሂ ምን ይላል እግረ ጎታታ፣
ዱላ ቢሰጡት መክቶ አይመታ።
68. ይሂ ምን ይላል የወንድ አልጫ፣
ሱሪውን ጣለው ከሜዳ መውጫ።

69. ይሄ ምን ይላል የጓሮ ፍግ፣
እግዜር ሲፈጥረው አድርጎት በግ።

70. ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ላዛ፣
ሲሄድ አየነው ታዛ ለታዛ።

71. ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው እንቅብ፣
ሲሸሽ አየነው ቅብቅብ ለቅብቅብ።

72. ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ዋሾ፣
ሲሸሽ አየነው ጌሾለጌሾ።

73. ይሄ ምን ይላል ጎፈሬው ዋዛ፣
ሲሸሽ አየነው ዋንዛ ለዋንዛ።

74. ይሄ ነወይ ባልሽ እጋጡ ያለው፣
አህያ ነው ብዬ ወፍጮ ልነዳው።

75. ይህ የፈሪ ልጅ ሲፈራ ጊዜ፣
ያባቱን ገዳይ አረ'ገው ሚዜ።

76. ይሻላል ብዬ ተማሪ ባገባ፣
እንሂድ አለኝ ኮቾሮ ለቀማ፤
የእሱንስ ኮቾሮ ለቃቅሞ ለውሻ፣
አገባ የለምወይ ጠይም ባለጋሻ።

77. ይዋጋል ብዬ ብሰጠው ጦር
ላባቱ ሰጠው ለቤት ማገር።

78. ጀግና ነው ብዬ አግብቼው ነበር፣
ፈሪ ሆነብኝ ሌላ ልቀይር።

79. ጃኖስ ገበያ ይውላል ድስት፣
አሽሞነሞኗት የቄሱን ሚስት።

80. ጠይሙ ጠይሙ ሻሽ የጠመጠመው፣
ልቤን እንደ ቆሎ አሽቶ ቆረጠመው።

81. ጥርጊያ ገበያ ይውላል ዱላ፣
አሞናሞኗት ያቺን ሳዱላ።

82. ጨኸር ገበያ ይውላል ቅርጫት፣
አቅበጠበጣት ያችን እመጫት።
83. ፍቅር ተሰፍሮ ከላይ ከላይ።
ይንደባለላል ካመዱ ላይ።
84. ፍቅር ያልቅና ሲሆን ግትቻ፣
ንዝንዝና ጭቅጭቅ ብቻ።

1.2 የአበሹቴ ግጥሞች

1. ሂጂ ወገልጤና ዳኞቹ ይዩሽ፣
አንድ አሮጌ ጫማ ቢመጸውቱሽ።
2. ሆድሽን ካመመሽ ቁና ተልባ ጠጪ፣
እኔ አልተውልሽም ብትዝረጠረጪ።
3. መፍተሉንማ ሁሉም ይፈትላል፣
የእከሊት አበሉ ከሁሉ ይበልጣል።
4. ማተቧ ጥብቅ ነው አይፈታምና፣
እከሊት አበሉ ታንሳኝ ክርስትና።
5. ማዞሪያ ብሠራ ከነመግላሊቱ፣
መች ትከድኝዋለሽ አንቺ መንጋላይቱ።
6. ምነው ታይኛለሽ የጎሪጥ የጎሪጥ፣
አይንና ጥርሴ ነው ሌላም አይገለጥ።
7. ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ መግላሊት፣
እከሊት አበሉ የሆዴ መድሃኒት።
8. ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ ምላጭ፣
እከሊት አበሉ ያገር ቀላዋጭ።
9. ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁ ገለባ፣
እከሊት አበሉ የሀገሩ ሌባ።
10. ምድር ምሼ ምሼ አወጣሁኝ መጅ፣
እከሊት ወለደች አይን የሌለው ልጅ።
11. ምጣዲቱ ጥቁር ታወጣለች ነጭ፣

እከሊት አበሉ ከሴቶች ብለጪ።

12. ሰደበችኝ አሉ ምን ልመልስላት፣

የወይራ ግንዲላ የሰው ቅርጽ የሌላት።

13. ሰደበችኝ አሉ ምን ብላ ምን ብላ?

አታሎ ነዳፊ ቀጭን ፈታይ ብላ።

14. ሰደበችኝ አሉ ወይ አለመኖሬ፣

ይቺ ያለት ድንጋይ የዳውንቶች በሬ።

15. ሰደበችኝ አሉ ድምጿን ከፍ አድርጋ፣

ይች ዘወርዋራ እግር ያህያ መንጋጋ።

16. ሰድቤ ሰድቤ መልሼ ልካስሽ፣

እንደአፈር አውድማ ቂጥኝ ይፈርክስሽ።

17. ሲዳብስሽ አድሮ ካላመሰገንሽው፣

ሙቀጫ ግልገሉን ምነው በወተፍሽው።

18. ሳሩን በሬ በላው ቅጠሉን አንበጣ፣

ምን ሊጎዘጎዝ ነው እከሊት ስትመጣ።

19. ሴቱ ድስቱን ጣደ ምኑን ሊሠራው፣

እከሊት አበሉ ቅመሙን ይዛው።

20. ሴት ወይዘሮ ሁሉ ሲበላ በሌማት፣

እከሊት አበሉ መሶበ ወርቅ አላት።

21. ሴቶች ተሰባስበው ሙያ ሲቋጠሩ፣

እከሊት አበሉ ትበልጣለች አሉ።

22. ስሄድ ትሄዳለች ስቆም ትቆማለች፣

ይች መታረሪያ እግር ነባር አርጋኛለች።

23. ስትሄድ እጥር እጥር ስትተኛ ጎን የላት፣

ለከሊት አበሉ እንዴት ልሁንላት።

24. ሽንብራ ከክቼ ላስጣው ከደጅሽ፣

እከሊት አበሉ ፀሐይ ነው ገላሽ።

25. ቀሚስሽ ጎንደሬ፣ ኩታሽም ጎንደሬ፣

እከሊት አበሉ ታምሪኛለሽ ለኔ።

26. ቀጭን ትፈትላለች እንደሸረሪት፣

    እከልዬ አበሉ የወንዶች እህት።

27. በላች በላችና የበርበሬ ቂጣ፣

    አፏ ብልቅጥ አለ እንደሰማይ ቁጣ።

28. በላች በላችና የበርበሬ በሶ፣

    አፏ ብልቅጥ አለ፣ ቀይ ለምዱን ለብሶ።

29. በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣

    አረገዝኩኝ አለች ቀፈቷን ብታይ

30. በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣

    ፈነጠቀችበት ከመኝታው ላይ

31. በላች በላችና የወጡን ላይ ላይ፣

    ፈነጠቀችበት ከቆለጡ ላይ።

32. በላች በላችና ዱባና ድንች፣

    አረገዝኩኝ አለች አሯ ቢከማች።

33. በላች በላችና ገብሱን ከነአሰሩ፣

    አረገዝኩኝ አለች ቀለቤን ስፈሩ።

34. በሙጃሌ እግሯ አንዴ ብትረግጠኝ፣

    ይኸው ሦስት አመቴ እያንቀጠቀጠኝ።

35. በቀይ ማዘያ ቀይ ልጅ አዝላለች፣

    እከሊት አበሉ እርሷ ትሆናለች።

36. በትርትሪያ ብዬ ባምባየ ልመለስ፣

    አከሌ አበሉ የራሄሎ ፈረስ።

37. በእከሊት ጓሮ ምን ይሽከረከራል፣

    ሰፌድ ነው እያልኩኝ ለካስ አሯ ኖሯል።

38. በወር ትፈትላለች አንድ ሽልቃቂ፣

    እቴ አልሆነልሽም የሰው ቤት ልቀቂ።

39. በድንጋይ ላይ ድንጋይ በዛ ላይ ንብ አለች፣

    የእከልዬ ቂጧ ታነበንባለች።

40. በጀበና ጠንሳሽ በወንፊት ጠማቂ፣
ለቅቄልሻለሁ በይ ተጨማለቂ።
41. ባልሽን ስጭኝና ጨው ጭኜ ላምጣበት፣
ግጥብጥብ አድርጌ ዝንብ ይጫወትበት።
42. ባልሽን እሰሪው በውሃ ጠፍርሽ፣
የእናቴ ልጅ ነወይ የምተውልሽ።
43. ባልንጀራ ቢሉሽ በቁመት ነወይ፣
እከሊት አበሉ አብሮ አደጌ ነይ።
44. ባልንጀራ ብዬ ልቤ እያመናት፣
አታሎ ነዳፊ ቀጭን ፈታይ ናት።
45. ባናውቅ ነው እንጂ ቸርነትሽን፣
መች ታድሪ ነበረ ወገላት ብቻሽን።
46. ትርትሪያ ገበያ ይሸጣል ምስር፣
እምቧን ሽጣው መጣች በየውድማው ስር።
47. ትርትሪያ ገበያ ይሸጣል ቲማቲም፣
እምቧን ሽጣው መጣች በሰላሳ ሳንቲም።
48. ትርትሪያ ገበያ ይውላል በገፈጅ፣
ገድ ነው ትላለች እግሯን እየጋፈች።
49. ትርትሪያ ገበያ ይውላል ብረት፣
ግልብጥ አ'ርጋሽ ትደር ኪዳነ ምህረት።
50. ትርትሪያ ገበያ ይውላል አብሽ፣
አንቺን ማን ያገባል መሬት የሌለሽ።
51. ትርትሪያ ገበያ ይውላል እንቁላል፣
የጊዮርጊስ ያለህ ቂጧ ምን ያክላል።
52. ትርትሪያ ገበያ ይውላል ጥልቆ፣
አርባ ጋኔን ይብዳሽ ከመንገድ ጠብቆ።
53. ትርትሪያ ገበያ ይዘረጋል ቃሪያ፣
ደህና ምንጭር አለሽ የዝንብ መቃሚያ።

54. ንፍጧን አንጠልጥላ ከደረቷ ላይ፣
ባለድሪ መስቀል ማድረጓ ነወይ?
55. አመዳም ግርጣታም የተልባ ጥላይ፣
ደግሞ ካንቺው ብሶ ልትሰድቢኝ ነወይ።
56. አመድማዶ ከንፈር ግመሮ ደንደስ፣
አንቺንስ አውርዶ ቆላ ነው ማረስ።
57. አሻሻ ወልሻሻ ደባደቦ ከንፈር፣
አንቺም ታውቂያለሽ ወይ ና ብሎ ማሳፈር።
58. አሻሻ ወልሻሻ ክፉ ግጥም እግር፣
ሚስት አለችኝ ብሎ ለሰውም አይነግር።
59. አታሎ መንደፍስ የሴት ወጉ ነው፣
ቀጭን መፍተል እንኳ የሴት ወጉ ነው፣
እሷስ የምታውቀው ገንፎ በገል ነው።
60. አንቺ የኔ ጎባን መካከለኛይቱ፣
ማዞሪያ ሥሪልኝ ከነመግላሊቱ።
61. አንቺም የለበሽው የጥፍጥሬ ወንድም፣
እኛም የለበስነው የጥፍጥሬ ወንድም፣
አትበጣጠሽ ብጣሻም አልወድም።
62. አንዱ እጇ አምባር አላት፣ አንድ እጇ የላትም፣
እንደ ግሽን ማሪያም ሰው አይለያትም።
63. አከሊት አበሉ ባገባች በወሯ፣
ብሄድ በደጃፏ አንሻተተኝ አሯ።
64. አከሌ አበሉ ባሏ ይወዳታል፣
ከጋጥ አስገብቶ ውሻ ያስበዳታል።
65. አይቻልም ሲሉት ይቻላል መከራ፣
ወገላት አደርኩኝ ከቁንጫው ጋራ።
66. አገልግል ሰፍቼ ለማን ላበርክተው፣
ለእከሊት አበሉ ለምታነጉተው።

67. አጭር ናት ይሏታል እድሜያቸው ይጠር፣
እናቷ መጥነው የወለዱትን።
68. እርግብ እርግቦሽ ለማዳ፣
ምናበረረሽ አሸዋ ሜዳ? (2)
አበረረኛ ክፉ እረኛ! (2)
እኔን ያብርረኝ ያክንፈኛ (2)
የሆዱን ብሶት ሳይነግረኛ(2)
የሆዱን ብሶት ቢነግርሽ፣
ትሄጃለሽ ወይ ተሻግረሽ ?
ለምን አልሄድም ተሻግሬ?
ከናት ካባቴ ተማክሬ፤
የምወደውን አስከትዬ፣
የሴት እቃዬን አንጠልጥዬ።
69. እህት አደራሽን አትስደቢኝ በንጉሥ፣
አፍሽ ይሸተኛል ዶሮ ኩስ ዶሮ ኩስ።
70. እስኪቢርቶ ግዙ ደብተር ጨምሩበት፣
እከልዬ አበሉ የምትፈርምበት።
71. እባካችሁ ሰዎች መጫኛ አውሱኝ፣
ያቺ ሙጀሊያም ገደል ገብታብኝ።
72. እኔ ሰው መስለሽኝ ቁመትሽን ባይ፣
የኮሲ ባቄላ ቀውላሌ ነሽወይ?
73. እንሰዳደብ ካልሽ እኔ እበልጥሻለሁ፣
በጥርሶችሽ መሃል አር አይቻለሁ።
74. እንሰዳደብ ካልሽ እኔ እንመዳመድ፣
አንቺ የጅብ አቅማዳ መቋጠሪያ ሆድ።
75. እንሰዳደብ ካልሽ እንውጣ ደጌት፣
ቂጥሽ ተሸክሚል ቤዶ ሽረሪት።
76. እንሳደብስ ካልሽ እንሂድ ኮን አቦ፣

አርሽን አሽከሜ በሰባራ ገንቦ።

77. እንሳደብስ ካልሽ እንውጣ ተራራ፣
አርሽን አሽከሜ በሰባራ እንስራ።

78. እንቁላል ሰብሬ እንቁላል አልተካም፣
እክሊት አበሉ የጠቋራ መልካም።

79. እንቦቅም የወግ ነው ዘረጥም የወግ ነው፣
እንደኮዳ ውሃ መንደቅደቅ ምንድነው?

80. እንቧይ ኮለል ብላ ገባች ከማጀቴ፣
እክሊት አበሉ የብር ቀለበቴ።

81. እንዝርቱ ከማጀት ጥጡ ከጉስጉሻ፣
አንቺ የምታውቂው ቅልውጥ እንደውሻ።

82. እንዲህ ብለው ነወይ የሰው ባል ሲቀሙ፣
በየሙቀጫው ሥር አሻሮ እየቃሙ።

83. እንዲህ እንዳላችሁ እንዲህ እንዳለን፣
አመት ይድገማችሁ አመት ይድገመን።

84. እንዲህ ወደ እዚታች ኑግ ይለጠለጣል፣
የእክሊት እምቧ አሎሎ ይውጣል።

85. እንዲህ ወደ እዚታች አህያ ሞታለች፣
ያችው እክሊት ልትግጥ ወርዳለች።

86. እንዲህ ወደዚህ ታች የስንዴ ቡቃያ፣
ስረሩኝ ትላለች እንደቁብ አህያ።

87. እንዲህ ወደዚታች ወፍ ተንጠልጥልለች፣
የእክሊት እምቧ ብቅ እልም ትላለች።

88. እንዲህ ወደዚታች የቃርሚያ ልክስክስ፣
እክሊት አበሉ የሁሉም ፍርክስ።

89. እኛ አላየንም እንዳንቺ አይነት ሴት፣
ሹርባ ሲሰራ የሚያስጠላበት።

90. እክሊት አበሉ ላይ ላዩን እለፊ፣
ትወድቂብኛለሽ ስትንከራፈፊ።

91. እከሊት አበሉ ምጣድሽ አይውጣ፣
የጠገበው ሲሄድ የራበው ሲመጣ።

92. እከሊት አበሉ ሞሰበ ጎድጓዳ፣
የራበው ታውቃለች ጎኑ የተጎዳ።

93. እከሊት አበሉ ሰጋጋ ሰጋጋ፣
አንቺንስ አንስቶ የቤተስኪያን ሳጋ።

94. እከሊት አበሉ ባለመስታወት፣
ያየሽ አፈር ይብላ የጠላሽ ይሙት።

95. እከሊት አበሉ ባገባች በወሯ፣
ቤቷን ለቀለቀች በገዛ ቅዘኗ።

96. እከሊት አበሉ ቤቷ ፈርሶባታል፣
የመጣ የሄደው ይማግድባታል።

97. እከሊት አበሉ ብትዞር ከኋላዬ፣
ወርቅ የፈሰሰበት መሰለ ገላዬ።

98. እከሊት አበሉ ነውርሽን እወቂ፣
መቀነቱን ፈተሽ በሀር ታጠቂ።

99. እከሊት አበሉ ነይ እቴ ነይ እቴ፣
ታፋትይኛለሽ አልቋል መቀነቴ።

100. እከሊት አበሉ ነይ እቴ ነይ እቴ፣
የውስጥ ልብሴ ነሽ የላይ መቀነቴ።

101. እከሊት አበሉ አማርኩኝ ብለሻል፣
አመድ የነፋባት አህያ መስለሸል።

102. እከሊት አበሉ አማርኩኝ ብለሻል፣
ከባህር የወጣች ውርንጫ መስለሻል።

103. እከሊት አበሉ አብረን እንሙት፣
አንቺ አብሽሎ ሆነሽ እኔ ደረቆት።

104. እከሊት አበሉ እህቴ አደራሽን፣
እጁን ሳይታጠብ አይንካው ገላሽን።

105. እከሊት አበሉ እንደተጎለትሽ፣
እሹርቤሽ ላይ ቂራው አራብሽ።
106. እከሊት አበሉ የማነሽ ወዳጅ፣
አንገትሽ ይመስላል የማሰሮ ጉማጅ።
107. እከሊት አበሉ የሰራችው ሽሮ፣
ብዙ ሰው ገደለ እንደጠጅ አስክሮ።
108. እከሊት አበሉ የሰፋችው ሙዳይ፣
እሱ ሽከርካራ ወንድሟ ሰው ገዳይ።
109. እከሊት አበሉ የሴት ብልጫይቱ፣
ዘንከል ይመስላል የወጧ ቅላቱ።
110. እከሊት አበሉ የኔ የብቻዬ፣
ከጆሮዬ ላ'ርግሽ እንደ ጉትቻዬ።
111. እከሊት አበሉ የደፋችው በፍታ፣
ባምሳ መሰቅሰቂት ባምሳ ሰፌድ ወጣ።
112. እከሊት አበሉ የደፋችው በፍታ፣
አይኑን አፈጠጠ ቂሶቹን ሊማታ።
113. እከሊት አበሉ ያይኔ ኩል ያይኔ ኩል፣
የወገቧ ቅማል ዘጠኝ ቂና ተኩል።
114. እከሊት አበሉ ገበያ ወጥታለች፣
በኩታዋ ጫፍ ጫፍ ያር ቅመም ይዛለች።
115. እከሊት ጥርስሽን አኑሪው በዋንጫ፣
የኛ ይሆነናል ለእህል ማላመጫ፣
ያንቺ ይሆንሻል ያደባባይ መውጫ።
116. እከሊት ጥርስሽን አንቆርቁሪው በቅል፣
እንዘራዋለን አምሳያው ቢበቅል።
117. እከሊት ጥርሶችሽ እኒያ ነጫጮቹ፣
ከሆዴ ገቡና እንደወፍ ተንጫጩ።
118. እከሌ አበሉ ቤት ያለች ቀይ ውሻ፣

አላስቀምጥ አለች ዱቄት በጉስጉሻ።

119. እከልዬ አበሉ ልጅም አልወለደ፣
እንደ ጭዳ ዶሮ አዙሮ ባረደ።
120. እከልዬ አበሉ እኔነኝ ዘመድሽ፣
ጆሮሽን ሲነኩት ቡል ይላል አመድሽ።
121. እከልዬ አበሉ ጥግ ጥጉን እለፊ፣
አህያ ሞታለች ጨጓራ ዘርግፊ።
122. እጇን እሰሩልኝ በዝንጀሮ ጭራ፣
አላስቀምጥ አለች የሞሰብ እንጀራ።
123. እግሯ ወተርታራ ወገቧ ደጋን፣
ከወንዙ ዘፍዝፏት ትርስ እንደሆነ።
124. ኸረ ዝጉ ዝጉ ፣ ዝጉ በማረሻ፣
አሁን ትመጣለች የእከሌ ውሻ።
125. ኸረ የኔስ ጎባን ታማለች በጥና፣
እስኪ ጨርቁን ልጠብ ለቅሶ አልቀርምና።
126. ከመልኳ ጸባዩዋ የሚለሰልሰው፣
እከልየ አበሉ አየሠው አየሰው።
127. ከስንዴ መካከል ይዘራል አብሽ፣
እከሊት አበሉ የቀይ ድንቡሽቡሽ።
128. ከበተስኪያን ጓሮ ያለች ደረቅ ዋንዛ፣
ብበላ አ'ጠረቃ ብትቀባ አትወዛ።
129. ከተማሪ ጓሮ ኩበት ቀልለሻል፣
ተማሪ ክፉ ነው ይማግድብሻል።
130. ከእከሊት ጓሮ ዘልዬ ብገባ፣
ተከምሮ አየሁት አሯ እንደገለባ።
131. ከወደድከኝ አይቀር ፍቅራችን ከጠና፣
ሚስትህን ግደላት ግመሮ ጋትና።
132. ከድንጋይ ላይ ድንጋይ ከዚያ ላይ ቀርቀሮ፣

ሳይደርሱባት ደራሽ የማን ናት ደንቆሮ።

133. ከጨኸር ትርትሪያ የምትነግዱ፣

ከእከሊት ከንፈር መጫኛ ቅደዱ።

134. ወዲህ ማዶ ቀሮ ወዲያ ማዶ ቀሮ፣

እከሌን ሲበዱት ወንድሚ ታቅሮ።

135. ወዲህ ማዶ ጭቂኝ ወዲያ ማዶ ጭቂኝ፣

እከሊት አበሉ ሁሌም ጨቅጭቂኝ።

136. ወዲያ ማዶ ሳማ ወዲህ ማዶ ሳማ፣

እከሊት አበሉ የሰይጣን ውሽማ።

137. ወዲያ ማዶ እንቁላል ወዲህ ማዶ እንቁላል፣

የእከሊት ፊሷ ጋን ይፈነቅላል።

138. ወዲያ ማዶ ዋሻ ወዲህ ማዶ ዋሻ፣

እከሊት አበሉ የማንነሽ ጥንብ ውሻ።

139. ወዲያ ማዶ ገመድ ወዲህ ማዶ ገመድ፣

እከሌን ሲበዱት አሯ ጎመድ ጎመድ።

140. ወዲያ ማዶ ጤፍ ወዲህ ማዶ ጤፍ፣

እከሊት አበሉ የማነሽ ሙጢአፍ።

141. ወዲያ ማዶ ጫት ወዲህ ማዶ ጫት፣

እከሊት አበሉ የጅኒ እመጫት።

142. ወዲያ ማዶ ፎጣ ወዲህ ማዶ ፎጣ፣

እከሊት አበሉ የማነሽ ሸርሙጣ ?

143. ውሃ ለሰስ አድርገሽ እጠቢው ነቱን፣

ያ ገልቱ ባልሽ የሸናበትን።

144. ዘወር ዘወር አር'ጎ ይነፋል ወንፊት፣

ፍቅር የጋራ ነው ተይው ነፋፊት።

145. የማነው እንዝርት እመከታው ላይ፣

እከሊት አበሉ የቀጭን ፈታይ።

146. የሰፌድ ላይ አተር ኮለሌ ኮለሌ፣

እከሊት አበሉ የመንደር አለሌ።

147. የኔን ባል ወሰድሽው፣ አላየንም ቆንጆ፣
ከከንፈርሽ ዳር ዳር ይወጣል መናጆ።
148. የኛማ ጎባን የኛማ ጣውንት፣
ሽሮ ጣድኩ ብላ ዘንጋዳ ዱቄት፣
ቅቤ አረኩ ብላ ቀረሽችበት፣
ውሽቴን እንደሁ ባሏ ባለበት።
149. የእከሊት አባት ምንኛ ከበረ፣
ልጁ እያራችለት እሱ እየከመረ።
150. የእከሊት ጸጉር ሀይማኖተኛ ነው፣
ከፍ አይል ዝቅ አይል እዛው እቦታው ነው።
151. የእከሊትስ አባት ልጅም አልወለደ፣
በአጎዛ ጠቅልሎ ገደል በሰደደ።
152. የእከሊትን ቀሚስ ማንም አይዋሰው፣
የቂጧ ጠፈጠፍ እያረሰረሰው።
153. የእከሌ አበሉ እግር አትበል ወልቻ ወልቻ
አንተንስ ቆማምጦ የከበሮ መምቻ።
154. የእገሊት እግር ሞጋጋ ሰጋጋ፣
ያንንስ ቆማምጦ ለአሮጌ ቤት ሳጋ።
155. የዋድላ ደጋ ቤት ደጃፉ መለስ፣
ምን ምን ትይኛለሽ አንቺ ቋቁቻ ራስ።
156. የዋድላ ደጋ ቤት ደጃፉ ፊት ለፊት፣
ምን ምን ታሚኛለሽ አንቺ አመዳም ፊት።
157. የደጅሽን አጥር እጠሪው በኮባ፣
ያ ከርፋፋ ባልሽ ገደል እንዳይገባ።
158. የዳገት ላይ ፍየል ነይ እሪያ ነይ እሪያ፣
እከሊት አበሉ ተይዛለች ስሪያ።
159. የጅብ አባወራ ይሄዳል ሌሊት፣
እከሊት አበሉ ዓይነ ጎብላሊት።
160. የገደል ላይ ከሴ፣ መርግ የገረሰሰው፣

የእከሊትን እምስ እንሽላሊት ላሰው።

161. ያንን ማዶ ጋራ ምን አጎደጎደው፣

የእከልዬ ፈሷ ትናንት ያነጎደው።

162. ይሄ ነወይ ባልሽ ከምድጃ ያለው፣

በሦስቱ ስላሴ በጥፊ በይው።

163. ይሄ ነወይ ባልሽ ከምድጃ ያለው፣

ጀበና ነው ብዬ ላለቀልቀው።

164. ይሄ ነወይ ባልሽ ከጋጡ ያለው፣

አህያ ነው ብዬ ገበያ ልነዳው።

165. ይሄ የማነው ቀሚስ ታጥቦ የተሰጣው፣

የእከሊት ይሆናል ቅዘን ያገረጣው።

166. ይሄ የቆላ እንጨት አይነድም ይጨሳል፣

የእከሊት ፈሷ አንጀት ይበጥሳል።

167. ይጠመቃል በጋን ይጠጣል በዋንጫ፣

እከሊት አበሉ ሽለሽል አፍንጫ።

168. ደግሞ ያንችስ እናት ከኔናት በለጡ፣

ድንቅ አክስለውሻል እያገላበጡ።

169. ዳገት ላይ ሆና ታሽካካለች ቆቅ፣

እከሊት አበሉ ልቅም ያለች ወርቅ።

170. ጀምበር ዘወር ሲል ይጣዳል ሰላሱት፣

እከሊት አበሉ ነይ ፈሱት ነይ ፈሱት።

171. ጎተራ ላይ ሆና ታሽካካለች ዶሮ፣

እከሊት አበሉ ድልድል ወይዘሮ።

172. ጓደኞችሽ አስር አንቺ አስራአንደኛ፣

አንቺ የኩሬ ውሃ የሁሉም መዋኛ።

173. ጥልፍ ቀሚሱንስ ሁሉም ሰው ለብሶታል፣

የእከሊት አበሉ ወርቅ ፈሶበታል።

174. ፈትፍታ ፈትፍታ የማልበላውን፣

ታስጨንቀዋለች እከሊት ሆዴን።

## <u>አባሪ 2፡-</u> ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | ለጥያቄዎቹ ምላሽ የሰጡ ሰዎች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ትልልቅ ሰዎች | ከዋኞች | ባለሙያዎች |
| 1 | አበሹቴ ማለት ምን ማለት ነው? ኧሽይቦሌ ማለትስ? | ✓ | | ✓ |
| 2 | አበሹቴ ወይም ኧሽይቦሌ ለምን ይጨፈራሉ? | ✓ | √ | |
| 3 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ጨዋታ ክዋኔ (ሥርዓት) የትና በምን ሁኔታ ይካሄዳል? የሚመረጥ ቦታና ሠዓት አለ? | ✓ | | √ |
| 4 | የአበሹቴ ወይም የኧሽይቦሌ ጨዋታ ክዋኔ ምን ይመስላል? | ✓ | √ | |
| 5 | የአበሹቴ ወይም የኧሽይቦሌ ጨዋታዎች ሃይማኖታዊ ናቸው ወይስ ዓለማዊ ? | ✓ | | |
| 6 | የጨዋታዎቹ አከዋወን ሥርዓት በአሁኑና በዱሮው መካከል ለውጥ አለወይ? ካለ ምን? | ✓ | | |
| 7 | ጨዋታው በማንና እንዴት ይጀመራል? | ✓ | ✓ | |
| 8 | ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ምን ምን ድርጊቶች ይከናወናሉ? | ✓ | ✓ | |
| 9 | የአበሹቴ ወይም የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞች ለማን ይገጠማሉ? | | ✓ | |
| 10 | ገጣሚዎቹስ ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? | ✓ | ✓ | |
| 11 | ተሳታፊዎች ምን ይለብሳሉ? | ✓ | ✓ | |
| 12 | በጨዋታው የሚገጠሙ ግጥሞች ምን ምን ናቸው? | ✓ | ✓ | |
| 13 | ሴቶች ጨዋታውን የሚጀምሩበት ዕድሜ ስንት ነው? | ✓ | ✓ | |
| 14 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ግጥሞችን የምትገጥሙት በድንገት ነው ወይስ ተዘጋጅታችሁ? | | ✓ | |
| 15 | የምትገጥሙት በድንገት ከሆነ እንዴት ነው ፈጥራችሁ የምትገጥሙት? | | ✓ | |
| 16 | በግጥሙ የሚሰደቡት ወይም የሚሞገሱት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? | | ✓ | |
| 17 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ግጥሞችን መጫወት ልምድ ከየት አገኛችሁ? | | ✓ | |
| 18 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ጨዋታዎች ለምን ይዘፈናሉ? | ✓ | | ✓ |
| 19 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ጨዋታዎች ከሌላ አካባቢ ጨዋታዎች በምን ይለያሉ? | | | ✓ |
| 20 | የአበሹቴ እና የኧሽይቦሌ ቃል ግጥሞችን ለመቀረስ ምን አድርጋችኋል? | | | ✓ |
| 21 | የአካባቢው ማህበረሰብ ለአበሹቴ እና ለኧሽይቦሌ ጨዋታዎች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? | | | ✓ |

## አባሪ ሦስት ከመስክ የተነሱ ፎቶዎች




**የአካባቢው ባህላዊ አለባበስ (የባህል ቡድን)**




**የሴቶች ባህላዊ አለባበስ በገጠር አካባቢ**




**ከቤተክርስቲያን ግቢ ወጭ ተጫዋቾችና ታዳሚዎች ሲሰባሰቡ**




**ከፈትል የተሠራ ነጠላ የለብሱ እናቶች ኧሽይቦሌ ሲጫወቱ**




**የአበሹቴ ጨዋታ የአንድ ቡድን አባላት**




**የኧሽይቦሌ ጨዋታ እየደመቀ ሲሄድ ሁለት ሶስት ቦታ በመቧደን ጨዋታው ሲከወን**